ቁመኛው
ገጽ 11

ኀሽ ለልጇ ...
ገጽ 16

የተንጠልጣይ ድልድይ ግንባታ - ለገጠሩ ማኅበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ትስስር መኀልበት
ገጽ 18

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
84ኛ ዓመት ቁጥር 011 መስከረም 11 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!








# ኢትዮጵያን የማዳከም ስትራቴጂ እስከምን?

**አዲሱ ገረመው**



ግብፅ በቅርቡ ከሱማሌ እና ከኤርትራ ጋር ያደረገቻቸው ተደጋጋሚ ግንኙነቶች ኢትዮጵያን አጀንዳ ያደረጉ ስለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህ ተግባርም ኢትዮጵያን ከጎረቤት ሀገራት የመነጠል ዲፕሎማሲ እየተከተለች ስለመሆኑ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ለመሆኑ ግብፅ በአፍሪካ ቀንድ ባለው ውስብስብ ጂኦፖለቲካዊ ትግል ውስጥ ጠንካራ ኢትዮጵያ እንዳትፈጠር ስትራቴጂካዊ ርምጃዎችን አስፋፍታ የመቀጠሏ ዓለማቀፋዊ አንድምታው ምንድነው?

ዓለም አቀፉ የፖለቲካ ተንታኝ አቶ ሙሳ ሸኮ ግብፅ በታሪክ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ መረጋጋት እና የኢኮኖሚ እድገት ለመናድ ያላሰለሰ ጥረት ማድረጓንና ይህ ስልት ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ እንዳትጠቀምና ጠንካራ ቀጣናዊ የበላይነት እንዳይኖራት ከመፍራት የመጣ መሆኑን ይናገራሉ።

ከታሪክ አኳያ ግብፅ ቢያንስ ለግማሽ ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ ውስጣዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ መግባቷን በማንሳት፤ ለዚህ በአብዛኛው የምትሰጠው ሰበብ ደግሞ የዓባይ ወንዝን ከመቆጣጠር ስጋት ጋር የተያያዘ ነው ይላሉ።

ግብፅ የዓባይ ግድብ ግንባታ እንዳይከናወን በመቃወም ሰፊ ቀጣናዊ የበላይነት ስትራቴጂዋ የቅርብ ጊዜ መገለጫ ነው ያሉት አቶ ሙሳ፤ ግብፅ የህዳሴ ግድብን እንደ ስጋት ብታነሳውም ግድቡ የልማት ፕሮጀክት እንጂ የፖለቲካ ጉዳይ አለመሆኑን ይገልጻሉ።

ግድቡ የተገደበው የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ስለመሆኑ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንደሚያውቀው

ኢትዮጵያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# እሥራኤል ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት አጠናክራ ቀጥላለች

## - የእሥራኤል የሕክምና ልዑክ ለልብ ሕሙማን ሕክምና እየሰጠ ነው

**ዳግማዊት አበበ**


ፎቶ ሀዲስ አብርሀ

አዲስ አበባ፡- የእሥራኤል መንግሥት በሕክምናው ዘርፍ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ። የእሥራኤል የሕክምና ልዑክ ቡድን በኢትዮጵያ ለሚገኙ 200 የልብ ሕሙማን በትናንትናው እለት ሕክምና መስጠት ጀምሯል።

በኢትዮጵያ የእሥራኤል ምክትል አምባሳደር ቶመር ባርላቪ በወቅቱ ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ፤ እሥራኤልና ኢትዮጵያ በሕክምናው ዘርፍ መልካምና ለረጅም ጊዜ የቆየ ግንኙነት አላቸው። በአሁኑ ጊዜም ከተለያዩ ግብረ ሠናይ ድርጅቶች ጋር በመሆን በአዲስ አበባ እንዲሁም በሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች ሕክምና ለመስጠት የሕክምና ልዑክ አስገብቷል ብለዋል።

የሕክምና ልዑክ ቡድኑ በልብ ሕመም ለሚሰቃዩ ሕጻናት ብቻ ሳይሆን በአራት የሕክምና ዘርፍ ሕክምና እንደሚሰጥ ገልፀው፤ በቀጣይም የእሥራኤል መንግሥት

እሥራኤል ከኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ለአካባቢና አዕምሯዊ ስንቅ መፍትሔን የሻተው የምገባ ፕሮግራም

**አማን ረሺድ**

**ዜና ሐተታ**

የምገባ መርሐ ግብር የተማሪዎችን የትምህርት ማቋረጥ መጠን ከመቀነስ ባለፈ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ። መርሐ-ግብሩ የተማሪዎች ተሳትፎ፣ የመማር ምጣኔን ከማሻሻል፣ አካታችነትና ከሥርዓተ ምግብ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍተት የጎላ ሚና እንዳለው ይገለጻል።

ከምግብ ችግር ጋር በተያያዘ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጪ እንዲሆኑ አድርጓል። በዚህም በሰብዓዊ

ለአካባቢና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የካፊቾ የዘመን መለወጫ በዓል ''ማሽቃሬ ባሮ'' ከነገ ጀምሮ በቦንጋ ሻምቤቶ ይከበራል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የካፊቾ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ በዓል የሆነው "ማሽቃሬ ባሮ" የብሔረሰቡን ባሕላዊና ታሪካዊ ትውፊት በጠበቀ መልኩ በተለያዩ ሁነቶች መስከረም 12 እና 13 "በቦንጊ ሻምቤቶ" እንደሚከበር የካፋ ዞን ዋና አስተዳዳሪ እንዳሻው ከበደ ገለጹ።

የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ እንዳሻው ከበደ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በዓሉን አስመልክቶ የካፊቾን ብሔረሰብ የሚገልጹ ባሕላዊና ታሪካዊ ጨዋታዎችና ዘፈኖች ይቀርባሉ። እንዲሁም

የካፊቾ የዘመን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# በሌማት ትሩፋት ከ10 ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት ተመርቷል

## -ዘንድሮ ከ12 ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት ለማምረት ታቅዷል

ታደሠ ብናልፈው



አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር ከ10 ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት ከላምና ከግመል መመረቱን ግብርና ሚኒስቴር ገለጸ። በ2017 በጀት ዓመትም ከ12 ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት ለማምረት መታቀዱን ተናግሯል።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና የዓሣ ሀብት ልማት ዳይሬክተር ወይዘሮ ጽጌረዳ ፍቃዱ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት በሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር ከ10 ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት ከላምና ከግመል ተመርቷል።

በ2015 በጀት ዓመት በመጀመሪያው የሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር አምስት ነጥብ 6 ቢሊዮን ሊትር ወተት ከላም እንዲሁም አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ሊትር ወተት ከግመል መመረቱን አውስተው፤ በ2016 በጀት ዓመት ከ10 ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት ተመርቷል ብለዋል።

“በ2014 በጀት ዓመት በዓመት ለአንድ ሰው 60 ሊትር ወተት ይቀርብ ነበር፤ በ2016 በጀት ዓመት በሌማት ትሩፋት ሥራ ለአንድ ሰው በዓመት 80 ሊትር ወተት ማቅረብ ተችሏል” ያሉት ዳይሬክተሯ፤ በ2018 በጀት ዓመት በቀን የአንድ ሰው የወተት አቅርቦት 110 ሊትር ለማድረስ እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

በ2017 በጀት ዓመት ከላም 11 ነጥብ 6 ቢሊዮን ሊትር፤ ከግመል አንድ ነጥብ 6 ቢሊዮን ሊትር በአጠቃላይ ከ12 ቢሊዮን ሊትር በላይ የወተት ምርት ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፤ እቅዱን ለማሳካት እንስሳትን የማዳቀል፤ መኖን በስፋት የማልማት፤ ወጣቶችን በዘርፉ የማሠማራት፤ የገበያ ትስስር የመፍጠር ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በ2018 በጀት ዓመትም የሀገሪቱን የወተት ምርት ከ16 ቢሊዮን ሊትር በላይ ለማድረስ ከወዲሁ ታቅዶ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ወይዘሮ ጽጌረዳ አያይዘውም ከሌማት ትሩፋት በፊት በዓመት የአንድ ሰው የዓሣ አቅርቦት ዜሮ ነጥብ 5 ኪሎ ግራም ነበር፤ በ2016 በጀት ዓመት አንድ ነጥብ 2 ኪሎ ግራም ደርሷል ብለዋል።

የዓሣ ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ ባለው የሌማት ትሩፋት በ2016 በጀት ዓመት 138 ሺህ ቶን ተመርቷል፤ በ2017 በጀት ዓመት 260 ሺህ ቶን የዓሣ ምርት ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

በ2018 በጀት ዓመት በዓመት የአንድ ሰውን የዓሣ ምርት አቅርቦት ሦስት ነጥብ 36 ኪሎ ግራም ለማድረስና 391 ሺህ ቶን የዓሳ ምርት ለማምረት እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በተጠናቀቀው ዓመት ስድስት ነጥብ 2 ቢሊዮን እንቁላል ተመርቷል፤ በ2017ና 18 በጀት ዓመት 11 ነጥብ 7 ቢሊዮን እንቁላል ለማምረት እየተሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

በ2018 በጀት ዓመት በዓመት የአንድ ሰው የዕንቁላል አቅርቦት 100 ለማድረስ እየተሠራ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

2016 በጀት ዓመት 207 ሺህ ቶን ማር የማምረት ሥራ ተከናውኗል ያሉት ወይዘሮ ጽጌረዳ፤ በተያዘው በጀት ዓመትና በቀጣይ ዓመት 473 ሺህ ቶን ማር ለማምረት እንደሚሠራም አመላክተዋል።

# የተፈጥሮ ማዳበሪያ፤ በእጅ ያለ ወርቅ

በጋዜጣው ሪፖርተር



ባሕር ዳር፡- አርሶ አደር አስፋው ታደሰ በደቡብ ወሎ ዞን የሚኖሩ አርሶ አደር ናቸው። አርሶ አደሩ ከሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ይልቅ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ጥቅም እንዳለው እንደሚረዱ ይናገራሉ።

የማዳበሪያ እጥረት ብዙ ጊዜ ሲገጥም ይስተዋላል ያሉት አርሶ አደሩ "መፍትሔን በቀዬ" እንዲሉ በራስ አቅም ይህን ችግር ለመሸፈን ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸውን የአካባቢያቸውን ሁኔታ በማንሳት ነግረውናል።

አርሶ አደሩ የተፈጥሮ ማዳበሪያን በማዘጋጀት በቀያቸው ለሌሎች ምሳሌ ለመኾን እየሠሩ ስለመሆኑም ነው ያብራሩት።

ባለፈው ዓመት ግማሽ በግማሽ የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀማቸውን የሚናገሩት አርሶ አደሩ ወደፊት ሙሉ ለሙሉ የመሬታቸውን ደኅንነት በሚጠብቀው የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለመጠቀም ተግተው እንደሚሠሩ ነው የገለጹት።

የተፈጥሮ ማዳበሪያ ብዙ ጊዜ ብዛት እንጂ ጥራት ላይ ትኩረት ሳይደረግ በመቆየቱ በሚገባ እንዳልተጠቀሙበት ነው የተናገሩት።

አርሶ አደሩ በዚህ ዓመት ከብዛትም በተጨማሪ ጥራት ላይ ትኩረት አድርገው ለመሥራት የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ከግብርና ባለሙያዎች ምክረ ሃሳብ በመውሰድ ለመሥራት እየተዘጋጁ እንደሆነም ተናግረዋል።

በደቡብ ወሎ ዞን ልክ እንደ አርሶ አደር አስፋው ታደሰ ሁሉ ሌሎች አርሶ አደሮችም የእርጥበቱ ጊዜ ሳያልፍባቸው የተፈጥሮ ማዳበሪያ የሚያዘጋጁበት ግብዓት እያሠባሠቡ ነው።

8 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማዘጋጀት የእርጥበት ወቅቱ ሳይጠናቀቅ ለመሠብሠብ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ እንደሆነ ነው ዞኑ ያስታወቀው።

እስካሁንም 300 ሺህ ሜትር ኪዩብ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ግብዓት ስለመቀበሩም የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ የሰብል ልማት ቡድን መሪ ይመር ሰዒድ ተናግረዋል።

ለዚህ ተግባር ብቻ ዞኑ እስከ ቀበሌ ድረስ ባለሙያ መድቦ ድጋፍ እያደረገ ነው ያሉት የሰብል ልማት ቡድን መሪው፤ ይህ ወር ዋናው የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማዘጋጃ ወር በመሆኑ ክትትል እየተደረገ እየተሠራ ስለመሆኑም አብራርተዋል።

አቶ ይመር በዞኑ የተወሰኑ አካባቢዎች ባለው ወቅታዊ የሠላም እጦት ችግር መድረስ ያልተቻለባቸው ስድስት ወረዳዎች እንዳሉ ገልጸው፤ ከእነዚህ ውጭ ሁሉም ወረዳዎች የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማዘጋጀት ሙያዊ እገዛ እየተሰጠ ስለመሆኑ ነው ያብራሩት።

በዞኑ ውስጥ 462 ሺህ አባወራዎች እንደሚገኙ የተናገሩት ባለሙያው በተፈጥሮ ማዳበሪያ ዝግጅት ሥራው ላይ ሁሉም አባወራዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ እየተሠራ ነው ተብሏል። የግብርና ባለሙያዎች መድረስ በቻሉባቸው አካባቢዎችም ጥሩ እንቅስቃሴ እንደሚታይ ነው የነገሩን።

በዝግጅት ደረጃ በመጠን ቢለያይም ሁሉም አርሶ አደር እንዲያዘጋጅ ግን መግባባቱ እና የተግባር እንቅስቃሴው መጀመሩን ነው ያስረዱት።

የሚዘጋጀው የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከ200 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ሊሸፍን እንደሚችልም ያላቸውን ዕምነት ገልጸዋል።

አርሶ አደሮች በየዓመቱ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ያዘጋጁ ስለነበር የነበሩ የተፈጥሮ ማዳበሪያ መቅበሪያ ጉድጓዶችን የመጥረግ እና የሌላቸው ደግሞ አዲስ የማዘጋጀት ሥራ እያከናወኑ እንደሆነም ገልጸዋል።

ለተፈጥሮ ማዳበሪያ ዝግጅት የሚሆኑ አስፈላጊ ግብዓቶችን የአረንጓዴው ወቅት ሳያልፍ የማሠባሠብ ሥራ እየተከናወነ ስለመሆኑም አስገንዝበዋል።

በዘንድሮው የተፈጥሮ ማዳበሪያ ዝግጅት ላይ ከብዛት ባለፈ ጥራት ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራም ነው የነገሩን።

በተለይ በያዝነው ሳምንት መስከረም 11 ቀን 2017 ዓ.ም ዞኑ ለተፈጥሮ ማዳበሪያ ዝግጅት ትኩረት በመስጠት "በአንድ ቀን የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማዘጋጀት" በሚል አንድ ቀበሌ ተመርጦ የመሥራት ዘመቻ እንደሚካሄድም ተናግረዋል።

የተፈጥሮ ማዳበሪያ ዝግጅትን ልምድ ለማድረግ እና ሌሎች ተሞክሮ የሚወስዱበት እንዲሆን እየተሠራ ነው ብለዋል።

ከአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በክልሉ በ2017 የምርት ዘመን ከ66 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ በላይ መደበኛ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ በመሠራት ላይ ነው። እስካሁን ባለው መረጃ 6 ነጥብ 7 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ መደበኛ ኮምፖስት ተዘጋጅቷል።

በተጨማሪ 9 ሺህ 96 ኩንታል ቨርሚ ኮምፖስት እና 10 ሺህ 471 ሜትር ኩዩብ ባዮሳላሪ ኮምፖስት ተዘጋጅቷል። አርሶ አደሮች ከባለሙያዎች ባገኙት ሙያዊ ድጋፍ መሠረት በአሁኑ ወቅት የተፈጥሮ ማዳበሪያ የማዘጋጀት ሥራው በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ተጠናክሮ መቀጠሉን አሚኮ ዘግቧል።

# ስምምነቱ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ አገልግሎት በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከቪዛ ኢንተርናሽናል ጋር ያደረገው ስምምነት ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማትን አገልግሎት በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል መሆኑ ተገለጸ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደንበኞቹ ዓለም አቀፍ የቪዛ ካርዶች በስፋት መጠቀም እንዲችሉ የሚረዳ ስምምነት ከቪዛ ኢንተርናሽል ጋር ትናንትና ተፈራርሟል።

የባንኩ ፕሬዚዳንት አቤ ሳኖ እንደገለጹት፤ ንግድ ባንክ ከቪዛ ኢንተርናሽናል ጋር ለረጅም ዓመታት የዘለቀ አጋርነት አለው፤ የሚጠቀምባቸው ኤቲኤም ካርዶችም ከተቋሙ ጋር የተያያዙ ናቸው።

ስምምነቱ ስትራቴጂካዊ አጋርነትን የያዘ መሆኑን አንስተው፤ ወደ ውጭ ሀገራት የሚጓዙ የባንኩ ደንበኞች በተለያዩ ሀገራት ገንዘቦችን በስፋት በዓለም አቀፍ ደረጃ መጠቀም እንዲችሉ የሚረዳ ስምምነት መደረጉን አንስተዋል።

በተጨማሪም የቪዛ ካርዶች በብዛት እንዲቀርቡና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚያስችል ስምምነት መፈጠሩን አስረድተዋል።

ከዚህ ቀደም ለውጭ ተጓዦች ሲሰጥ የነበረውን የቪዛ ካርድ የተወሰነ የውጭ ምንዛሪን ብቻ እንዲጠቀሙ የሚረዳ መሆኑን አስታውሰው፤ የአሁኑ ስምምነት ደንበኞች በሒሳብ ደብተራቸው ያለውን የውጭ ምንዛሪ በዓለም አቀፍ ምንዛሪ ያለገደብ እንዲጠቀሙ የሚያስችላቸው መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በቅርቡ ያደረገችው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለስምምነቱ አንዱ ምክንያት መሆኑን ጠቁመው፤ መሰል ተቋማት በሀገሪቷ ለሚያደርጉት ተሳትፎ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥርና ብዙ አማራጮች እንዲፈጠሩም ዕድል የሚሰጥ መሆኑን አንስተዋል።

በኢትዮጵያ ካለው የፋይናንስ ዘርፍ ዕድገት ጋር ተያይዞ እንደ ቪዛ ካሉ ትልቅ ልምድ ካላቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር መሥራት ፋይዳው ጉልህ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ባንኩ ከፋይናንስ ተቋሙ ጋር ዘለቄታዊ አጋርነቱን እያጠናከረ መምጣቱ በተሻለ ውጤታማ ለመሆን የሚረዳ ነው ብለዋል።

አጋርነቱ ለባንኩ ደንበኞች እንዲሁም በአጠቃላይ ለፋይናንሱ ዘርፍ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑ የገለጹት ፕሬዚዳንቱ ፤ ስምምነቱ ውጤታማ እንዲሆን በትኩረት እንደሚሠራም ገልጸዋል።

የቪዛ ኢንተርናሽናል ምክትል ፕሬዚዳንትና የምሥራቅ አፍሪካ ጀነራል ማናጀር ቻርድ ፖሎክ በበኩላቸው፤ ቪዛ ኢንተርናሽል በአፍሪካ ብሎም በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ያለውን አቅም እየተጠቀመ መሆኑን ተናግረዋል።

ሁለቱ ተቋማት በጋራ መሥራታቸው በልምድ ልውውጥ፣ በሰው ሀብት፣ በቴክኖሎጂ፣ በግብይትና መሰል ጉዳዮች የተሻለ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያግዛቸው መሆኑን አመላክተዋል።

ስምምነቱ ለአምስት ዓመታት የሚተገበር ሲሆን፤ የጋራ ዓላማዎችን ለማሳካት ቪዛ ኢንተርናሽናል ለንግድ ባንክ የተለያዩ ድጋፎችን እንደሚያደርግ ተገልጿል።



አቶ መስፍን ቃሬ

# ከሲዳማ ክልል ከ36 ሺህ ቶን በላይ የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ይቀርባል

**አምሳሉ ፈለቀ**

አዲስ አበባ፡- በምርት ዘመኑ ከ36 ሺህ ቶን በላይ የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ መታቀዱን የሲዳማ ክልል ቡና፣ ፍራፍሬና ቅመማቅመም ባለሥልጣን አስታወቀ። ዘንድሮ ወደ ውጭ ከሚላከው የቡና ምርት 200 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ይገኛልም ተብሏል።

የክልሉ ቡና ፍራፍሬና ቅመማቅመም ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መስፍን ቃሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በ170 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ቡና በስፋት ይለማል። ከዚህ ውስጥ 142 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሚለማው ምርት የሚሰጥ ነው።

የቡና ምርታማነት የሚጨምሩ ፓኬጆችን በአግባቡ መጠቀም በተቻለበት በ1 ሄክታር 11 ኩንታል የቡና ምርት ይገኛል ያሉት አቶ መስፍን፤ በዘንድሮው የምርት ዘመንም 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል የቡና ምርት ለመሰብሰብ መታቀዱን ተናግረዋል።

ከሚሰበሰበው ምርትም 36 ሺህ 100 ቶን በላይ የታጠበ ቡና ለማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን፤ ይህንን ለማድረግም አስቀድሞ 204 ሺህ ቶን እሸት ቡና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ እንዲሰበሰብ ይደረጋልም ብለዋል።

ወደ ውጭ ከሚላከው የቡና ምርት 89 በመቶው የታጠበ ሲሆን 11 በመቶው ደግሞ ደረቅ ቡና ነው።

ጥራቱን የጠበቀ የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ በመላክ ረገድ በተለይም ከ2014 ዓ.ም እስከ 2016 ዓ.ም ተከታታይ የምርት ዘመናት የተሻለ አፈጻጸም መመዝገቡንና ዘንድሮም የሲዳማ ቡና በዓለም ገበያ ደረጃውን ይዞ እንዲቀጥል ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግ ተጠቁሟል።

ዘንድሮ ከሚላከው የታጠበ የቡና ምርትም 75 በመቶው 1ኛ ደረጃን፣ 24 በመቶው 2ኛ ደረጃን እንዲሁም 1 በመቶው ብቻ 3ኛ ደረጃን እንዲይዝና ደረጃው ከዚያ በታች እንዳይሆን ለማድረግ መታቀዱንም ገልጸዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ዘንድሮ ወደ ውጭ ከሚላከው የቡና ምርት 200 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት ታቅዷል። ይህም ክልሉ በዘርፉ የሚጠበቅበትን አስተዋፅዖ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲያበረክት ያደርጋል።

የዓለም የቡና ዋጋ የሚወሰነው በእንግሊዝና አሜሪካ ሀገራት በሚገኙ የቡና ገበያ ማዕከላት እንደሆነ ያስረዱት አቶ መስፍን፤ በተለይ በ2014 የምርት ዘመን በግል ኢንዱስትሪዎች የዓለምን የቡና ዋጋ ባላማከለ ሁኔታ የምርት ዋጋ ከፍ ብሎ መሸጡንና በ2015 ደግሞ በዝቅተኛ ዋጋ መሸጡን ተከትሎ የተፈጠረውን ክፍተት ለማጥበብ በ2016 ዓ.ም ምርቱን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገዙ መደረጉን አስታውሰዋል።

በተያዘው የምርት ዘመንም የዓለምን የገበያ ዋጋ በተከተለ ሁኔታ ግብይት እንዲፈጸምና አርሶ አደሩም ሆነ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችና ማኅበራት ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በትኩረት እንደሚሠራም ተጠቁሟል።

ቡና ለክልሉም ሆነ እንደ ሀገር የተሻለ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ ዘርፍ እንደመሆኑ እንደ ትልቅ ሀብት የሚታይ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተለይ አምራች አርሶ አደሮች የቡና ዛፎችን በመትከልና ኮምፖስት መጠቀምን ጨምሮ የቡናን ጥራትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ፓኬጆችና ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ እየተደረገ መሆኑን ይናገራሉ።

ምርታማነትን የሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ብቻም ሳይሆን በክልሉ ቡና በኩታ ገጠም የማልማቱ ሥራ በትኩረት እየተሠራ እንደሆነም ተነግሯል።

በክልሉ በአሁኑ ወቅት በግል፣ በኅብረት ሥራ ማኅበራትና በአክሲዮን የተደራጁ 450 የእሸት ቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪዎች የሚገኙ ሲሆን፤ ለነዚሁ ኢንዱስትሪዎች ኃላፊዎችን በየወረዳው ለሚገኙ ልማት ባለሙያዎች የቡና ጥራትን ማስጠበቅ በሚያስችሉ ሂደቶችና ቅድመ ጥንቃቄዎች ዙሪያ ሰሞኑን ሥልጠና መሰጠቱንም ዋና ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

# አስተማማኝ የሠላም ዋስትና ለማረጋገጥ የምክክር ባሕልን ማዳበር ይገባል

**ማሕሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ አስተማማኝ የሠላም ዋስትና ለማረጋገጥ የምክክር ባሕልን ማዳበር እንደሚገባ የሠላም ሚኒስትር አስታወቀ።

"የሠላም ባሕልን ማዳበር" በሚል መሪ ሃሳብ የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የሠላም ቀን ምክንያት በማድረግ በትናትናው ዕለት የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

በመድረኩ ላይ በሠላም ሚኒስትር የሠላም ግንባታ ሥራ አስፈፃሚ አወቀ አጥናፉ (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ የሠላም ዋጋ በምንም ሊተመን የማይችል ለሰው ልጆች ሁሉ አስፈላጊ የሆነ መሠረታዊ ነገር በመሆኑ በኢትዮጵያ ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ አስተማማኝ የሠላም ዋስትና ለማረጋገጥ የምክክር ባሕልን ማዳበር ይገባል።

የአንድ አካባቢ የሠላም እጦት ለሌላው አካባቢ ሠላም እጦት ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚፈጥር መሆኑን ያነሱት አወቀ (ዶ/ር)፤ ሠላም የአንድ ወገን ብቻ ባለመሆኑ ለዘላቂ ሠላም ግንባታና ፅናት ሁሉም በባለቤትነት መሥራት አለበት ብለዋል።

በሠላም ማጽናት ሂደትም ምክክር የማይተካ ሚና እንዳለው ገልፀው፤ በሀገሪቱም የምክክር ኮሚሽን በየአካባቢው የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል እንደሚሆን እና እስካሁን ባለው ሂደትም በየአካባቢው መሠረታዊ ችግሮች እንዲፈቱ ለውጥ እያመጣ መሆኑን አስታውቀዋል።

በመሆኑንም በዚህ የምክክር ሂደት ላይ በተለይም የሠላም እጦት ዋነኛ ተጠቂ ሴቶችና ወጣቶች በንቃት መሳተፍ እንዳለባቸውና የምክክር ባሕልን በማዳበር ለዘላቂ ሠላም የበኩላቸውን እንዲወጡ አወቀ (ዶ/ር) አሳስበዋል።

አወቀ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ሚኒስትሩ በሠላም ጉዳይ ተዋናይ ኃይሎችን በማካተት በሠላም ግንባታ ላይ ሊሠሩ የሚገባቸው ጉዳዮችና አካላትን በማሳተፍ የማኅበረሰቡን አቅም ለማሳደግ የሚያስችል የሠላም ፖሊሲ በቅርቡ በመንግሥት ይፀድቃል ተብሎ ይጠበቃል።

ፖሊሲው የሀገር በቀል ዕውቀቶችን ለመጠቀም ሠላምን ለማስፈን የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ጨምሮ ያካተተ ነው። እንደፀደቀም የሥራ መመሪያ በማድረግ ማኅበረሰቡ የሠላም መፍትሔው በእጁ እንዳለ በማመላከት አስተማማኝ የሠላም ዋስትና ለመስጠት ያስችላል ብለዋል።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ ዋና ተጠሪን በመወከል የተመድ የልማት ፕሮግራም ዋና ኃላፊ ሳሙኤል ዱኤ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበረው የሠላም ቀን ስናከብር ሠላም ማለት ግጭት የሌለበት ማለት ብቻ ሳይሆን የሁሉንም ጥረትና ርብርብ በዘላቂነት የሚጠይቅ ሂደት መሆኑን መረዳት አለብን ብለዋል።

በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የሀገራዊ ምክክር ግጭቶችን በንግግርና ውይይት በመፍታት የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ ሀገሪቱ ለሠላም ያላትን ቁርጠኝነት የሚሳይ መሆኑንም አስታውቀዋል።

ሴቶችና ወጣቶችን በማብቃትም ለሀገር እድገት ብሎም ሠላምን ማጽናት የማይተካ ሚና እንዳላቸው ገልጸው፤ ወጣቶችና ሴቶችን በሠላምና ፀጥታ ግንባታ ላይ ያላቸው ተሳትፎ ለማሳደግና ለማብቃት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በጋራ የሚሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

# ኢትዮጵያ በንግድና ኢንቨስትመንት የምታካሂዳቸው ሕጋዊ አሠራሮች የሀገርን ጥቅም ያስከበሩ ናቸው

**ዘላለም ግዛው**




አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የምታካሂዳቸው የንግድ፣ የኢንቨስትመንት እና መሰል ሕጋዊ አሠራሮች የሀገርን ጥቅም ባስጠበቀ፣ ተወዳዳሪነትን በሚጨምርና በአፍሪካ ያላትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በሚያስከብር መልኩ እንዲተገበር ትኩረት መሰጠቱን የፍትሕ ሚኒስቴር ገለጸ።

በ11ኛው የምሥራቅ አፍሪካ የግልግል ዳኝነት ኮንፍረንስ ላይ ንግግር ያደረጉት የፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ ኤርሚያስ የማነብርሃን (ዶ/ር)፤ የግልግል ዳኝነት የግጭት መፍቻ ዘዴ በኢትዮጵያ እንዲያድግ ፍትሕ ሚኒስቴር ትኩረት መስጠቱን አመልክተዋል።

የግልግል ዳኝነት ውስብስብ እና ግዙፍ የንግድ ልውውጦች የሚዳኙበት የግጭት መፍቻ ዘዴ ሲሆን፤ አካሄዱ ያልተወሳሰበ፣ ወጪ ቆጣቢና ጊዜ የማይወስድ የንግድ ውል ስምምነት እንዲቀጥል የሚያስችል በመሆኑም በመሠረታዊነት ከመደበኛው ፍርድ ቤት ይለያል ብለዋል።

በመደበኛው ፍርድ ቤት የሚታዩ ጉዳዮች በአብዛኛው ቀጣይ ግንኙነትን በሚያጠናክር መልኩ አይዳኙም። በተለይ ከንግድ ሁኔታ አንጻር ሲታይ አሸናፊና ተሸናፊ የሚኖርበት ሁኔታ ስለሚኖረው ተመካሪ አይደለም።

የግልግል ዳኝነት አሠራር እንዲስፋፋ አዋጅና ደንቦች ተዘጋጅተዋል። ባለሙያዎች የግልግል ዳኝነት ሥልጠና እንዲወስዱ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

መንግሥት ሃገርን በሚጠቅም ሁኔታ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም በማውጣት የተለያዩ ርምጃዎችንም ወስዷል ያሉት ኤርሚያስ (ዶ/ር)፤ በፊት ዝግ የነበሩ የንግድና የፋይናንስ ዘርፎችንም ክፍት ማድረጉን ገልጸዋል። በትግበራው ምክንያትም የኢንቨስትመንት ፍሰቱ እየጨመረ እንደሚቀጥልም እምነታቸውን ተናግረዋል።

ኤርሚያስ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ በቅርቡ የተወሰደው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ኢትዮጵያን ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ማዕከል እንደሚያደርጋት ይጠበቃል።

ኢትዮጵያ ከሰሐራ በታች ካሉ ሀገራት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የምታስመዘግብ ሀገር ናት። በማዕድን፣ በኢነርጂ፣ በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ፣ በመሠረተ ልማት ዝርጋታ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶች ይሠራሉም ነው ያሉት።

በዚህ ሂደት ያለመስማማቶችና ግጭቶች ሲኖሩ ቦታዎች እና አስማሚዎች ወይም ገላጋዮች በብዛት ከአፍሪካ ውጭ ለንደን፣ ሲንጋፖር፣ ሆንግኮንግ ወይንም አሜሪካ ለመሄድ በመገደዳችን ምክንያት ከፍተኛ ገንዘብ ይወጣል። ሀገር በቀል አሸማጋዮችም ስለማያድጉ እነዚህን ችግሮች መቅረፍ ያስፈልጋል ብለዋል።

ኮንፍረንሱ ልምድና ተሞክሮ ለመቅሰም ይረዳል፣ አዲስ አበባ የዓለማቀፍ ዲፕሎማቶች መቀመጫ ከመሆኗ ባሻገርም የኢኮኖሚ የቱሪዝም ማዕከል፣ የኮንፍረንስ ማዕከል ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል ብለዋል።

ፍርድ ቤቶች የሚመሩበት የሕግ ሥርዓት አለ። የሚፈጀው ጊዜ እና ከሚወጣው ገንዘብ አንጻርም በመደበኛው ፍርድ ቤት ከሚታየው ጋር ሲነጻጸር በግልግል የሚዳኙት ዝቅ ይላል ሲሉም ተናግረዋል።

የግልግል ዳኝነት ክርክር ያላቸው አለመስማት ያጋጠማቸው ወገኖች በስምምነት ወይም በውላቸው መሠረት እንዲፈጸምላቸው የሚፈልጉትን አስማሚ፣ ገላጋይ ወይንም ዳኛ መርጠው የሚከራከሩበት፣ ማስረጃ የሚያቀርቡበት ነው።

አሠራሩ በኢትዮጵያ ሲሠራበት የኖረ እና በፍትሐብሔር ሕጉም እውቅና የተሰጠው መሆኑንም አመልክተዋል።

የማሊ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ታሕቦ ቻካካ ኒይሬንዳ እንዲህ አይነትና መሰል ኮንፍረንሶችን ማድረግ የግልግል ዳኝነት ልምድ እንዲዳብር፣ እውቀትና ተሞክሮ ለማወቅ እና ለመረዳት ያስችላል ብለዋል። ከሌሎች ሃገራት ጋር ለመገናኘት ዕድል እንደሚፈጥርም ተናግረዋል።



## ለአካላዊና አዕምሯዊ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሀብት ልማት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳረፉም በላይ የዜጎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ሚዛን አዛብተዋል።

ይህንንም መነሻ በማድረግ መፍትሔ ለመሻትም በአሁኑ ወቅት በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመተግበር ላይ የሚገኘው የትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሽ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ስንታየሁ ማሞ እንዳሉት፤ ከተማ አስተዳደሩ በተማሪዎች ላይ የሚደርሰውን ተፅዕኖ ለማቃለል በ2012 ዓ.ም የምገባ ኤጀንሲ በማቋቋም ወደ ሥራ ገብቷል።

በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ የቅድመ አንደኛ፣ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በምገባ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ በመሆናቸው በተማሪዎች ውጤት መሻሻል ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከቱን ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ይገልጻሉ።

በፕሮግራሙ የሚካተቱ ተማሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ጠቅሰው፤ ኤጀንሲው በ2017 በጀት ዓመት የምገባ አገልግሎቱን በአዲስ አበባና አዲስ አበባ ዙሪያ በሚገኙ አንድ ሺ 106 ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ 800 ሺ 34 ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ የቁርስና የምሳ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ አቅዷልም ይላሉ።

በዚህም ከተማ አስተዳደሩ ከዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ በጀት መበጀቱን አውስተው፤ ኤጀንሲው ለፕሮግራሙ የሚያስፈልጉ የግብዓትና የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን አጠናቆ መስከረም ስድስት ቀን ፕሮግራሙን በይፋ አስጀምሯል ብለዋል።

ተማሪዎች አካላዊና አዕምራዊ እድገታቸው የተሻለ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የምገባ ፕሮግራሙ ትልቅ አስተዋፅዖ እያደረገ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

ፕሮግራሙ ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎች በአግባቡ ትምህርታቸውን እንዳይከታተሉና ከትምህርት ገበታ ውጪ እንዲሆኑ እንዳደረጋቸው የሚገልጹት ም/ዋና ዳይሬክተሯ፤ ከምገባ ፕሮግራሙ መጀመር በኋላ በተማሪዎች ውጤት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ማሳየቱንም ያክላሉ።

በተጨማሪም ተማሪዎች ደስተኛ ሆነው ተመግበው ትምህርታቸው ላይ ትኩረት አድርገው እንዲማሩና ወላጆች ምግብ ለመቋጠር የሚያወጡትን ድካምና ወጪ በመቀነስ ረገድ ጉልህ ሚና ተጫውቷል ብለዋል።

በምገባ ፕሮግራሙ የተካተቱ ተማሪዎች ጤናማና በትምህርታቸው ውጤታማ ስለሚሆኑ ይህም ትምህርት የሚያቋርጡና ክፍል ደጋሚ ተማሪዎችን ለመቀነስ በእጅጉ እንደሚያግዝ አስረድተዋል።

የተማሪ ቁጥር ከመጨመር ባሻገር አገልግሎቱን ጥራት ባለው መንገድ ለማከናወን በበጀት ዓመቱ አዳዲስ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋቱን አውስተው፤ ለዚህም ምግቦች በሥርዓተ ምግብ ጥናት ላይ የተመሠረተ እንዲሆኑ የምግብ አበሳሰል የመቆጣጠሪያ ደረጃ የተዘጋጀ ሲሆን ለልጆች አካላዊና አዕምሯዊ እድገት የሚጠቅሙ እንደ እንቁላል፣ ጥቁር ጤፍ፣ ጨጨብሳ፣ ገብስ፣ ቅንጬ ያሉ ምግቦች በመዘርዝሮች የማካተት ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

በዘንድሮ የምገባ ፕሮግራም የአዕምሮ ውስንነትና መሰል ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ለብቻቸው የምግብ መዘርዝር መዘጋጀቱን ጠቁመው በተጨማሪም ለ16ሺ እናቶች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን ይናገራሉ።

የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም በሁለቱም ፆታ ተማሪዎች ተረጋግተው ትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ማስቻሉን አመላክተዋል። ፕሮግራሙ ትውልድ ላይ የሚሠራ ሥራ በመሆኑ ጥራት ባለው ሁኔታ ለማስቀጠል ወላጆች፣ መምህራንና የትምህርት ማኅበረሰብ ማገዝ እንደሚጠበቅባቸውም ምክረ-ሃሳባቸውን አቅርበዋል።

## የካፌች የዘመን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከበዓሉ አንድ ቀን ቀደም ብሎ የቋንቋና የባሕል ሲምፖዚየም የሚካሄድ ይሆናል።

ኮሚቴ ተዋቅሮ በዓሉ የሚከበርበት ስፍራ የደመቀ እንዲሆን የቦታ ዝግጅት፣ መንገድ የማመቻቸትና ለአካባቢው ተወላጆችና ወዳጆች ጥሪ የማድረግ ሥራ መሠራቱን የጠቆሙት አቶ እንዳሻው፤ "ማሽቃሬ ባሮ" የአደባባይ በዓል እንደመሆኑ መጠን ዜጎች ሃይማኖት፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ብሔርና በሌሎች መስኮች የሚታዩ ልዩነቶች ሳይገድቧቸው እንደሚያከብሩት ገልጸዋል።

እንደ አቶ እንዳሻው ገለጻ፤ "ማሽቃሬ ባሮ" የዜጎች የአንድነትና አብሮነት መገለጫ በመሆኑ ከባሕላዊነቱ አልፎ የአካባቢውን ሠላምና ፀጥታ የበለጠ ማጠናከር የሚቻልበት ነው። እንዲሁም የአካባቢው ልማት ይበልጥ እንዲፋጠንና የካፌቾ ብሔረሰብ ባሕላዊና ታሪካዊ ትውፊት ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያግዝ ነው።

በቀድሞ ጊዜ "ማሽቃሬ ባሮ" ሲከበር የቆየው ነገሥታቱ ያለፈውን ዓመት አጠቃላይ ተግባራትን ገምግመው የተሻለ ለሠሩት ሽልማት የሚሰጡበትና በአፈጻጸማቸው ጉድለት ያሳዩትን በመገሰጽ ሌሎችን በመሾም ነበር። እኛም ልምዶችን በመውሰድ በገጠርና በከተማ የተከናወኑ የልማት ሥራዎችን ማስቀጠልና የጎደሉትን ማሟላት የሚያስችል አቅጣጫ አስቀምጠናል ብለዋል።

የጥንት የካፋ ነገሥታት መናገሻ በሆነው "በቦንጊ ሻምቤቶ" በዓሉ እንደሚከበር በመግለጽ፤ ስፍራው ታሪካዊ በመሆኑ ከልማት ጋር በማስተሳሰር ለአካባቢው እድገት አስተዋፅዖ ማበርከት የሚችሉ የባሕል ማዕከላትን በመገንባት ገቢ የሚገኝበት ሁኔታ ለመፍጠር ጅምር ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን አውስተዋል።

በዓሉ የተጣሉ የሚታረቁበት፣ ዘመድ አዝማድ የሚገናኝበት፣ የአካባቢው ተወላጆች የጋራ ሥነልቦና ይዘው ዞኑን የበለጠ በልማት ማሻገር የሚቻልበት ነው ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት የጋራ ቁርጠኝነትና ኃላፊነት የሚወሰድበት መሆኑን ተናግረዋል።

በዓሉ የአካባቢው ባሕልና ቋንቋ የሚተዋወቅበት፣ ዜጎች እንዲቀራረቡና ልማትን የጋራ አጀንዳቸው



አቶ እንዳሻው ከበደ

በማድረግ በአንድ ላይ ሆነው እንዲነሱ የሚያስችል ነው። የአካባቢው ማኅበረሰብ የዞኑን ልማት ለማደናቀፍና ወደኋላ ለመመለስ ለሚፈልጉ አካላት ቦታ ሳይሰጥ በዓሉን በአንድነት ማክበር ይጠበቅበታል ነው ያሉት አቶ እንዳሻው።

"ማሽቃሬ ባሮ" ከማይዳሰሱ ቅርሶች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ይህንን በማጠናከር በዩኔስኮ ላይ ለማስመዝገብ ባለፈው ዓመት የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ያሉት አስተዳዳሪው፤ ለበዓሉ አከባበርም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የአስተዳደርና ፖለቲካ መቀመጫ የሆነችው የቦንጋ ከተማ እንግዶቿን በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ትገኛለች ብለዋል።

አካባቢው የቡና መገኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብሔራዊ የቡና ሙዚየም፣ የ18ቱ የከፋ ነገሥታት የቀብር ቦታ "ሾሻ ሞጎ"፣ የእግዜር ድልድይ፣ ታሪካዊ ገዳማትና መስጊዶች፣ ፏፏቴዎች፣ የጥንት የከፋ ነገሥታት መናገሻ፣ ጥቅጥቅ ደን እና ሌሎች ቅርሶች እንደሚገኙበት አመላክተው፤ አካባቢው ለቱሪዝምና ኢንቨስትመንት ምቹ በመሆኑ አልሚዎች ወደዞኑ በመምጣት በልማት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል።

## ኢትዮጵያን የማዳከም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በማንሳት፤ ይህ ደግሞ ውሃው ተገድቦ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደማይቀር የሚያሳይ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

በአንፃሩ ግብፅ ግድቡ ከተሠራ በኋላ ዓመቱን ሙሉ ተመሳሳይ የሆነ ተጨማሪ የውሃ ፍሰት የምታገኝ መሆኗን ያስረዳሉ።

ሆኖም ግብፅ ይህንን በትክክል እያወቀች የኢትዮጵያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ኢትዮጵያን ስለሚጠቅም ብቻ ፖለቲካዊ ጉዳይ በማድረግና ከብሔራዊ ደኅንነቷ ጋር አያይዛ ዓለምን በመዞር የተለያዩ ጫናዎችን ለማሳደር ጥራለች ነው ያሉት።

እንደ አቶ ሙሳ ማብራሪያ፤ ግብፅ የግድቡን አሞላል እና ሥራ ለመገደብ ዓለማቀፋዊ እና አሕጉራዊ ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎችን ለመጠቀም ጥረት አድርጋለች። ይህም የዓረብ ሊግን፣ የአፍሪካ ኅብረትን ማግባባት እና ጉዳዩን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ፊት ማቅረብን ያካትታል። የግብፅ አመራር ግድቡ የሕልውና ጉዳይ መሆኑን ደጋግሞ ሲያስጠነቅቅ ውዝግቡን የልማት ብቻ ሳይሆን የሕልውና ጉዳይ አድርጎታል።

ይህ ደግሞ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ልማት ለመገደብ እና የግብፅን የጂኦፖለቲካዊ የበላይነት በዓባይ ተፋሰስ ላይ ለማስቀጠል ትልቁ ስትራቴጂ አካል ስለመሆኑ ማሳያ ነው ብለዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የግብፅ መሪዎች "ሁሉም አማራጮች በጠረጴዛ ላይ ናቸው" ሲሉ በተደጋጋሚ አስጠንቅቀዋል። ይህም የተከደነ ወታደራዊ ርምጃ ወይም የበለጠ ድብቅ የማተራመስ ዘዴዎችን ስለማካተቱ ሰሞናዊ እንቅስቃሴዋ በይፋ የሚናገር ነው ባይ ናቸው።

ቢቢሲን ጨምሮ የውጭ ሚዲያዎች በዘገባቸው እንዳመላከቱት፤ ግብፅም በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለመፍጠር ከኢትዮጵያ ቀጣናዊ ተቀናቃኞች ጋር ጥምረት ለመፍጠር እየሞከረች ትገኛለች። ይህም ከኤርትራ ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነት እንዲሁም የግብፅ ወታደራዊ አባላትን እንደ ሶማሊያ ባሉ ሀገራት ማሰማራትን ያጠቃልላል። እነዚህ እርምጃዎች ግብፅ የኢትዮጵያን አለመረጋጋት በቀጥታ በመጋፈጥም ይሁን በክልላዊ የውክልና ግጭቶች ጠንካራና በኢኮኖሚ የበለፀገች ኢትዮጵያን ስጋት ለመመከት እንደ አንድ አዋጭ ስልት መመልከቷን ቀጥላለች ሲሉ አቶ ሙሳ ያብራራሉ።

ሆኖም ይላሉ አቶ ሙሳ፤ የዓባይ ግድብ ለእነዚህ ውጥረቶች መነሻ ይሁን እንጂ፤ ግብፅ ኢትዮጵያን ለማተራመስ የምታደርገው ጥረት ግን ከግድቡ የዘለለ ሆኗል ሲሉ ያስረዳሉ።

ግብፅ በቅርቡ በሶማሊያ እና በኤርትራ የምታደርገው እንቅስቃሴ ታሪካዊ የጣልቃ ገብ ፖሊሲዋ መቀጠሉን ያሳያል ያሉት አቶ ሙሳ፤ በእነዚህ ጎረቤት ሀገራት ወታደሮቿን በማሰማራት እና ልዩ ሥራዎችን በመሥራት ግብፅ በኢትዮጵያ ድንበሮች ዙሪያ አለመረጋጋት ለመፍጠር ጥረት እያደረገች መሆኗን ይጠቅሳሉ።

አቶ ሙሳ፤ ግብፅ ኢትዮጵያን ለማተራመስ ወደኢትዮጵያ ጎረቤት ሃገራት የገባችበት አካሄድ እንዲሁም ጎረቤት ሀገራትን መሠረት አድርጎ ስትራቴጂ መንደፍና ቀጣናውን ለማተራመስ መሞከር አዲስ አይደለም። ይህ የግብፅ ታሪካዊ የሆነ የዲፕሎማሲ ስህተት ጠላትነትን ይፋ የማድረግ አካሄድ ራሷን ግብፅን አደጋ ላይ የሚጥልና የሚያዋርድ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ግብፅ በሶማሊያ የሚገኙ አንጃዎችን በመደገፍ በኢትዮጵያ ላይ በጠላትነት የሚፈረጁ ቡድኖችን በመደገፍ፣ ኢትዮጵያ በቀጣናው የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት አቅምን የሚገድብ አለመረጋጋት ለመፍጠር መጣሯ አግባብነት የጎደለው ነው ይላሉ አቶ ሙሳ።

አንዳንድ ጎረቤት ሀገራትም በግብፅ ስትራቴጂ ውስጥ ቁልፍ ተዋናይ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ የጎረቤት ሀገራት መንግሥታት ግብፅ ጥምረት ለመፍጠር የምታደርገው ሰፊ ጥረት አካል ሊሆኑ አይገባም ሲሉ አሳስበዋል።

ይህንን ለመቀልበስ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ጋር ያላትን ዲፕሎማሲና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን ማጠናከር እንደሚገባ፤ የመከላከያ ሪፎርሙን ተከትሎ ወታደራዊ ዝግጁነቱም ሊጠናከር እንደሚገባ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባል የሆኑት መብራቱ ዓለሙ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የምሥራቅ አፍሪካ ጂኦፖለቲካ አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱን ይናገራሉ።

በተለይም የዓባይ ግድብ እየተጠናቀቀ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ግብፅ ዓባይ ወንዝ የኛ ነው የሚል ታሪካዊ ትርክት በመያዝ ቀጣናውን ለማተራመስ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ መሆኗን ጠቅሰዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ በቅርቡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሱማሊላንድ ጋር ወደብን አስመልክቶ ያደረገውን ስምምነት ለማስጨህ ከሱማሊያ ጋር ግንኙነት በመፍጠር፤ ቀጥሎም ከኤርትራ ጋር ግንኙነት በመፍጠር አጠቃላይ ቀጣናው ላይ ችግር እንዲፈጠር ግብፅ ፍላጎቷን እያሳየች ነው።

ግድቡ ከተሠራ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ የበላይነት ይኖራታል፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነቷ እያደገ ይመጣል በሚል ስጋትና፤ ይህንን ለማስቆም በሚደረግ ጥረት ውስጥ ኢትዮጵያ ሠላም እንዳትሆን፣ አንድነቷ እንዳይረጋጋ እየሠራች ትገኛለች ነው ያሉት።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኤርትራ የግብፅ የጦር ሰፈሮች መቋቋማቸውን የሚገልጹ ዘገባዎች እየወጡ መሆኑን አስመልክቶ አቶ ሙሳ በዚህ ዙሪያ እንዳሉት እነዚህ እንቅስቃሴዎች ከዚህ ቀደምም የነበሩ መሆናቸውን ጠቅሰው ግብፅ ኢትዮጵያን በጠላት ለመከበብ የምታደርገውን ታሪካዊ ጥረት ቀጣይነት ያመለክታሉ ይላሉ።

እርሳቸው እንደሚገልጹት፤ ግብፅ ኢትዮጵያን ለማተራመስ የምታደርገው ጥረት የረዥም ጊዜ የጣልቃ ገብነት አካል ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ፅናት እንደሚያሳየው ግን አሁንም ከእነዚህ ፈተናዎች በላይ እንደምትወጣ ነው።

ሁለቱም ሀገሮች በዚህ ውስብስብ ጂኦፖለቲካዊ ምኅዳር ሲጓዙ፣ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ዲፕሎማሲ የበለጠ ተባብሶ እንዳይከሰት ለመከላከልና ዓባይ ከግጭት ይልቅ የትብብር ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል መሥራት እንደሚገባም ተገልጿል።

## እሥራኤል ከኢትዮጵያ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በሕክምናው ዘርፍ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

እሥራኤል ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እያለፈች እንደምትገኝ የገለጹት ምክትል አምባሳደሩ ሆኖም እሥራኤል የዜጎቿን ደኅንነት ከመጠበቅ ጎን ለጎን እነዚህን የመሰሉ ንቅናቄዎች ላይ የመሳተፉን ሥራ አጠናክራ እየቀጠለች ሲሆን ይህ ንቅናቄም በኢትዮጵያና በእሥራኤል መካከል ያለውን ግንኙነት ይበልጥ የሚያጠናክር መሆኑን ጠቁመዋል።

የሴቭ ዘ ቺልድረን ተወካይ ሪኪ ሮዘንቤል በበኩላቸው፤ ግብረሠናይ ድርጅቱ ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለ200 ከፍተኛ የልብ ችግር ላለባቸው ሕጻናት ሕክምና ለመስጠት አቅዷል ብለዋል።

የሕክምና ልዑክ ቡድኑ በትናትናው እለት የሕክምና ሥራውን መጀመሩን ገልጸው እስካሁንም 50 የልብ ችግር ያለባቸውን ሕጻናት መለየት መቻሉን ተናግረዋል።

የሕክምና ልዑክ ቡድኑ 200 ከፍተኛ የልብ ችግር ያለባቸው ሕጻናትን ለይቶ ሕክምና ካደረጉ በኋላ ብዙዎቹን ወደ እሥራኤል ሃገር ወስዶ ለማከም እቅድ እንዳለው የገለጹት ተወካዩዋ አምስት የቀዶ ሕክምና ማሽን ይዘው መግባታቸውን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዳይሬክተር ፕሮፌሰር አንዱዓለም ደነቀ፤ በኢትዮጵያና እሥራኤል መካከል በሕክምናው ዘርፍ የቆየ ወዳጅነትና ትብብር እንዳለ ገልጸው በተለይም የእሥራኤል መንግሥት ላለፉት ዓመታት የልብ ታማሚዎችን ወደ እሥራኤል ሀገር በመውሰድ እንዲሁም በሀገር ውስጥ በማከም ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የሕክምና ልዑክ ቡድኑ የልብ ሕክምናን እንዲሁም ሌሎች ሕክምናዎችን ለማድረግ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ ለብዙ ታማሚዎች እፎይታ የሚሆን ነው። በቀጣይም ከውጪ የሚመጡ ድጋፎች እንዲጠናከሩ በመሥራት ለታካሚዎች የተሻለ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

# ነፃ ሃሳብ

# በአዲሱ ዓመት መተሳሰቡም ቁጥጥሩም ይጠናከር

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

የኑሮ ውድነት ጉዳይ እየጨመረ ይሄዳል በሚል ስጋት ሕዝቡ መጨነቅ ከጀመረ ውሎ ማደሩ የአደባባይ ምስጢር ነው። በተለይም በቅርቡ መንግሥት ካደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ጋር በተያያዘ ሕዝቡ ብዙ ስጋት እንደገባው ይታወቃል። ዘይት ይጨምራል... ጤፍ ጣራ ይነካል .... ወዘተ የሚሉት ጉዳዮች ከማህበራዊ ሚዲያ እስከ ሰፈር ወሬ ቦታ ይዘዋል።

መስከረም ደግሞ የዓመቱ ፍላጎት ሁሉ ተጠረቃቅሞ የሚመጣበት ወቅት ነው። መስከረም ላይ ከወጪ የማይካተት ሸቀጥ አልያም ጉዳይ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። የበዓላት መደራረብ ለአቅመ ትምህርት የደረሱ ልጆች ካሉ የትምህርት ቤት ክፍያ፤ የመማሪያ ቁሳቁስ፤ ዩኒፎርም.... ብቻ ብዙ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ የሚነገሩና የማይነገሩ ወጪዎች ይኖራሉ። ይህ እንግዲህ የሚሰራበት፤ የሚጠጣበት የሚከሰስባት ባጠቃለይ የሚኖርባት ነገር ግን ለወር ደመወዝተኛው ክፍያ የማይሰጥባት ጳጉሜን ወር ጨምሮ ማለት ነው።

በርግጥ አንድ ሕዝብ የኑሮ ውድነት፤ የዋጋ መጨመር በዚህ ደረጃ ስጋት ቢሆን የሚገርም አይደለም። ምክንያቱም ባለፉት ዓመታት የተለያዩ ምክንያቶችን መነሻ በማድረግ የጨመሩ የሸቀጥና የአገልግሎት ዋጋዎች ወደነበሩበት ሲመለሱ ታይቶ አይታወቅም። ይልቁንም በሰበብ ባስባቡ ምክንያት እየፈለጉ ጨመረ እኮ ማለት ለነጋዴው ማህበረሰብ የዘወትር መዝሙር እየሆነ መጥቷል።

መንግሥትም በበኩል የንግዱን ዘርፍ ሥርዓት ለማስያዝ በሕገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ ከሚካሄዱ የቁጥጥርና የቅጣት ርምጃዎች ጀምሮ በመሠረታዊ ፍጆታዎች ላይ ከፍተኛ የሚባል ድጎማ እየተደረገ መሆኑን እናውቃለን። ነገር ግን ጥያቄው ሊቆም የሚችለው እንደ ሀገር የተረጋጋ የገበያ ሥርዓት ሲፈጠርና ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኘውም ሠራተኛ በልቶ የሚያድርበት ሁኔታ ሲመቻቻ ነው። በመሠረቱ በየትኛውም ዘርፍ ቢሆን ሥርዓት የመቆጣጠር ጉዳይ ለመንግሥት የሕግ አስከባሪ አካላት ብቻ ተሰጥቶ የሚፈለገው ውጤት ይገኛል ማለት ዘበት ነው። የህብተረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን የግድም ነው።

ይህም ሆኖ የንግዱ ማህበረሰብ ከትርፉ በላይ ለዜጎቹ ክብርና አገልጋይነት እንዲኖረው ይጠበቃል የሚል ጽኑ አቋም አለኝ። ይህንን ስል ነጋዴ የንግድ ሥራን የሚሰራው ለትርፍ እንጂ ለጽድቅ አለመሆኑንም እገነዘባለሁ። ነገር ግን ዛሬ ላይ በስፋት እየተተገበሩ ያሉ በሕግም፤ በሞራልም፤ በእምነትም የተከለከሉ ነገሮች አሉ። ከእነዚህ ነገሮች መካከልም የሚከተሉትን ልንጠቅስ እንችላለን። የመጀመሪያውና ብዙዎችን ያሰለቸው ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ የጤና ችግሮች እየዳረገ ያለው ባእድ ነገሮችን በምግብ ፍጆታዎች ላይ የመቀላቀል እርኩስ ተግባር ነው።

ሙዝ ከቅቤ፤ ማር ከቀለጠ ስኳር ፤ የጀሶ እንጀራ .... እነዚህን እንግዲህ በባሕላዊ መንገድ የሚከናወኑ የጥፋት ሥራዎች ልንላቸው እንችላለን። ምክንያቱም ዘመናዊ የጥፋት ምረዛዎችም ስላሉ ነው። ዘመናዊ የጥፋት ምረዛዎች የሚባሉት ከኩላሊት እስከ ካንሰር ላሉ አሰቃይቶ ገዳይ በሽታዎች መነሻ ይሆናሉ ተብለው የሚታሙት ጊዜያቸው ያለፈና የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸው የታሸጉ ምግቦች ናቸው።

የታሸጉ ምግቦች መነሻቸው ከሀገር ውስጥም ይሁን ከውጭ ጥፋታቸው የከፋና ሁላችንንም የሚነካ ነው። የከፋ የሚሆነው ብዙ ሰው ማሸጊያዎችን በመመልከት አለፍ ካለም የአገልግሎት ዘመንን በማየት በእምነት የሚጠቀማቸው በመሆኑና ከእነዚህ ውስጥም ለሕፃናት ምግብነት የሚውሉት ከፍተኛ ቁጥር ስላላቸው ነው። በዚህ በኩል መንግሥት ችግር

> **በየትኛውም ዘርፍ ቢሆን ሥርዓት የመቆጣጠር ጉዳይ ለመንግሥት የሕግ አስከባሪ አካላት ብቻ ተሰጥቶ የሚፈለገው ውጤት ይገኛል ማለት ዘበት ነው። የህብተረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን የግድም ነው**

እንዳለባቸው የደረሰባቸውን የምግብና የመጠጥ ዓይነቶች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ በዝርዝር ሲያሳውቅ እንደነበር ማስታወስ ይገባል።

ማስታወቂያዎቹ የተነገሩት ግን ምርቶቹ ወደ ገበያው ገብተው ከመሰራጨታቸው በፊት ሳይሆን በውል ላልታወቀ ጊዜ በገበያ ውስጥ ከቆዩ በኋላ ነው። ይሄ ማለት ደግሞ አነሰም በዛ የተፈጸመ ስህተት ወይንም ጥፋት መኖሩን ያመለክተናል። ይህም ሆኖ እነዚህ በዓይነትም በተደራሽነትም ሰፊ የሆኑ ጥፋቶች ሊቀንሱ የሚችሉት በመንግሥት ቁጥጥር ብቻ ሊሆን አይችልም። ይልቁንም የሕዝብ ተሳትፎና ህሊና ያለው ነጋዴና አምራች መፍጠር ይጠበቃል።

መተሳሰብና ህሊና እንዲኖረን የሚያስፈልገው ክቡር የሆንን የሰው ልጅ ከመሆናችን ባሻገር በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ይሄ የጥፋት መንገድ ራሳችንንም የሚነካ በመሆኑ ነው። ጉዳዩን እንደ አንድ ነጋዴ ወይንም አምራች ብናየው እንዲህ ሆኖ እናገኘዋለን። ሁኔታዎች ተመቹኝ ብሎ ለውዝ ውስጥ ባዕድ ነገር ጨሮ የፈጨው አልያም ቅቤ ውስጥ ሙዝ የጨመረው አባት እግር ጥሎት ለልጁ መድኃኒት ሊገዛ ፋርማሲ ቢገባ ጊዜው ያለፈበት የሚያድን ሳይሆን የበለጠ የሚያሳምም ወይንም ጊዜ ጠብቆ የሚገድል ነገር ሊሰጠው እንደማይችል ምን ማረጋገጫ ይኖረዋል።

አንድ ነጋዴ የእቃ መጥፋትን አልያም እጥረት መከሰትን ተገን አድርጎ አላግባብ ዋጋ ሲጨምር ሌላ አገልግሎት ለማግኘት አንድ ቦታ ሲሄድ ተመሳሳይ ምላሽ እንደማይገጥመው ምን ማረጋገጫ ይኖረዋል። ለዚህ ነው መተሳሰቡ ለህሊና መገዛቱ ከምንም ይቅደም የሚል ሃሳብ ያነሳሁት። ካልሆነማ ሁሉም አቅሙና ሁኔታዎች በፈቀዱለት አጋጣሚ የጥፋት አለንጋው ከሰነዘረ እውነተኛውም የመጠፋፋት መንገድ ጀምረናል ማለት ነው። የዚህ ውጤት ደግሞ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት የሚገድ አይመስለኝም።

በርግጥ የሰው ልጅ በባህሪው ለስሜቱና ለፍላጎቱ ቅድሚያ መስጠቱ አይቀርምና ብዙ ሥራ የሚጠበቀው ከተቆጣጣሪው አካል ነው። እንደ ሀገር እነዚህ ችግሮች ለመቆጣጠር የተለያዩ ተቋማት መኖራቸው ይታወቃል። ደረጃዎች ኤጀንሲ፤ ንግድ ቢሮ ፤ ገቢዎች፤ የደንብ ማስከበር ... ። እነዚህ አካላት ከሞላ ጎደል መዳረሻ አላማቸው አንደ ቢሆንም በተናጥል የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ። ቅንጅቱ ላይ ገና ብዙ ሥራ እንደሚቀር በቂ አመላካች ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ገቢዎች ቢሮ ከግብር ጋር በተያያዘ የሚሰራቸው ሥራዎች በቀጥታ ወደማህበረሰቡ ከሚቀርቡት ምርቶች ጋር ሲያያዙ አይተናል።

ወሬውን የሰማሁት ከስድስት ወር በፊት ይመስለኛል አንዲት እናት ወርቅ ለመግዛት ትፈልግና ወደ ፒያሳ ታቀናለች የተወሰኑ ሱቆች ከገባች በኋላ አንድ ቦታ ላይ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያጎናጽፍ ሃሳብ ያቀርቡላታል። እሱም ደረሰኝ የማትጠይቂኝ ከሆነ የተወሰነ አስተያየት እናደርጋለን የሚል ነው። እሷም ምንም ሳታመነታ ትስማማና እቃዋን ገዝታ አመስግና ትሄዳለች።

ከቀናት በኋላ የተደረገው የተጋነነ የዋጋ ቅናሽ ያላማራት ጓደኛዋ «ግን ይሄ ነገር የእውነት ወርቅ መሆኑን አረጋግጠሻል ወይ ስትል ትጠይቃታለች»። «አሉኝ እንጂ አላረጋገጥኩም እኔኮ ወርቅ አይቼና ነክቼ መለየት አልችልም» የሚል ምላሽ ስትሰጣት ጓደኛዋ እስኪ ለሁሉም እናስመርምረው ብላ ይዛት ትሄዳለች። ገንዘባቸውን ከፍለው ሲያስመረምሩ ነገሩ እንደፈሩት ይሆን የወርቅ ሀብል የተባለው የአንገት ጌጥ በአረብ ሀገራት የተለመደ አንደ የብረት ዓይነት ሲሆን፤ የገዛቻቸው ሁለት የጣት ቀለበቶች ደግሞ ሀያ አንድ ካራት ሳይሆኑ አስራ ስምንት ሆነው ይገኛሉ።

በኋላ እንደሰማሁት ለካ እንደዚህ ዓይነት ወንጀሎች በተደጋጋሚ የሚፈጸሙና ብዙዎችን መና ያስቀሩ ናቸው። አንዳንዶቹ ካለ አንዳች እፍረት ደረሰኝ ቆርጠው የሚሸጡትን ወርቅና ብር ሳይቀር ያጭበረብራሉ። ይህን ካደረጉ በኋላ አጣርቶ መጥቶ የሚጠይቃቸው ካለ ምላሻቸው የሚሆነው «በርግጥ ከእኔ ጋር ይህን እቃ ገዝቷል፤ አሁን ያመጣው ግን ከእኔ የተወሰደ ሳይሆን ሌላ ነው» የሚል ይሆናል።

ይሄን ጉዳይ ያነሳሁት በአንድ ወገን ምን ያህል የተወሳሰቡና አስቸጋሪ ማጭበርበሮች እንደሚፈጸሙ ለማመላከት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ከሕግ አስከባሪ አስጠባቂ አካላት ምን እንደሚጠበቅም ለማመላከት ነው። የወንጀልና የማጭበርበር ተግባራት በየጊዜው የሚለዋወጡና አዳዲስ አካሄዶችን የሚከተሉ ናቸው። በመሆኑም በተለመደው አሰራር እነዚህን ለመቆጣጠር መሞከር የትም የሚያደርስ አይመስለኝም።

በመሆኑም የድንገቴ ቁጥጥርና ፍተሻ ከየትኛውም አካሄድ በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል የሚል እምነት አለኝ። የሕጉ ነገር ምን ያህል እንደሚደግፈው ባላውቅም ለንግድ ሥራ የተከፈቱ ሱቆች ማምረቻ ማዕከላት ላይ ፤ በየመንደሩ ሃያ አራት ሰዓት ዝግ ሆነው የሚቀመጡ መጋዘኖች ላይ፤ በተደጋጋሚ ፍተሻ ቢካሄድ።

በተለምዶ ዳማስ በሚባሉ አነስተኛ መኪናዎችና ሌሎች ተሽከርካሪዎችም ለችርቻሪ ነጋዴዎች የሚበተኑ ምግብ ነክ፤ የመዋቢያ ቅባት ሳሙናና ምርቶች ላይ መኪኖቹን ከዚህ ከዚህ ሂዱ ከማለት በዘለለ ከሚመለከታቸው አካል ሳይለዩ የስልክ ግንኙነትም ሳያደርጉ ምርቶቹን ከየት እንዳመጡ እንዲጠቁሙና እንዲያሳዩ ቢደረግ። በርግጠኝነት ብዙ ሕዝብን የሚጎዱ ተግባር የሚፈጽሙ ግብር ከመክፈል የታቀቡ አጭበርባሪ ነጋዴዎችና አምራቾችን መቆጣጠር ይቻላል የሚል ሃሳብ አለኝ።

በርግጥ በገበያ ውስጥ የሚሰሩ አሻጥሮችን መከላከል ድንች እንደመላጥ ቀላልና በአንድ ወቅት ዘመቻ ብቻ የሚከናወን አለመሆኑን ጠንቅቄ አውቃለሁ። ምክንያቱ ደግሞ ሁለት ነው። የመጀመሪያው ጥቂት ነጋዴዎችና በስውር የድለላ ሥራ የተሰማሩ አካላት ሰው ሠራሽ የዋጋ ንረት ከመፍጠር ጀምሮ የሚሰሯቸው ወንጀሎች በየወቅቱ የሚለዋወጡ መሆናቸው ነው።

አካሄዶቹ ለተወሰነ ጊዜ ከሕዝቡም፤ ከመንግሥትም ስውር ሊሆኑ ይችላሉ እንጂ ዘላቂ አይሆኑም። በመሆኑም እነዚህ አካላት በቅድሚያ በጣም በተጠና መልኩ በቁጥጥር ረገድ ያለውን ክፍተት የሚያጠኑ፤ በአንድ ወቅት የተጠቀሙበትን አካሄድ ሌላ ጊዜ ዞር ብለው አያዩትም። ይልቁንም አዲስ ያልተበላበት ያልተነቃበት የስውር መስመር ይዘረጋሉ። ለዚህም እኮ ነው የሆነ ማጭበርበር ሲከሰት «ደግሞ እንደዚህም ተጀመረ ?» እንደ ቀልድ የሚታለፈው።

ሁለተኛውና ዋናው ምክንያት ግን በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ይህንን ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ተግባር ነው። እነዚህን አካላት በተመለከተም ሁለት ዓይነት መስተካከሎች ይጠበቃሉ። የመጀመሪያው የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ነው። ይህንን ስል አንዳንድ ሠራተኞች ለቁጥጥር በአንዳንድ ተቋማት ውስጥ ሲገኙ ከሙስናና ጥቅማ ጥቅም ባለፈ ባላየ የሚያልፏቸው ነገሮች አሉ።

ይህም በመሆኑ ተመሳሳይ ጥሰት እያለ ተመሳሳይ ርምጃ ሳይወሰድ ሲቀር እናያለን። ሁለተኛው ጉዳይ ከጊዜ ጋር የመራመዱ ነገር ነው። አንዳንድ ማጭበርበሮች በስፋት በከተማው ውስጥ እየተወሩ ያንን ተከትሎ ፈጣን ርምጃ ሲወሰድ አይስተዋልም። የየተቋማቱ ሠራተኞች በመደበኛ ጥቆማ ያለው ችግር ባይደርሳቸው እንኳን እንደ ሕዝብ የሚሰሙት ነገር በመኖሩ ያንን በመጠቀም ብዙ ከመጥፋቱ በፊት ርምጃ ሊወስዱ ይገባል እላለሁ። መልካም ዘመን ለመላው ኢትዮጵያዊ ይሁን።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «የእብድ ውሻ በሽታ መቶ በመቶ ገዳይ ነው»

- ተመራማሪና የምርምር አማካሪ አሰፋ ደሬሳ (ዶ/ር)

አመለወርቅ ከበደ

የእብድ ውሻ በሽታ በቫይረስ አማካኝነት በበሽታው ከተለከፈ እንስሳ ወደ ሌላ ጤነኛ እንስሳ ወይም ወደ ሰው በንክሻ የሚተላለፍ በሽታ ሲሆን ውሻን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ደመ ሞቃት እና አጥቢ የሆኑ እንስሳት እንዲሁም ሰዎችን የሚያጠቃ በሽታ ነው። ነገር ግን በሽታው በአብዛኛው በውሾች ላይ ስለሚታይና ሰዎችም የሚያስተውሉት ይሄንኑ ስለሆነ የእብድ ውሻ በሽታ የሚል ስያሜ አሰጥቶታል።

እ.አ.አ ከ2018 እስከ 2022 የተሰራ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ በዓመት ከ37 ሺህ በላይ ሰዎች በበሽታው የሚጠቁ ሲሆን ሁለት መቶ 97 ሰዎች በበሽታው ምክንያት እንደሚሞቱ ያሳያል።


በሀገራችን በሽታውን ሊያስተላልፉ ከሚችሉ እንስሳት ውሻ በዋናነት በሽታውን የሚያስተላልፍ እንስሳ መሆኑ በተለያዩ ጊዜያት በተሰሩ ጥናቶች ተመላክቷል።

በአብዛኛው በሀገሪቱ ከተሞች ከቤታችን ወጣ ስንል ባለቤት አልባ የሆኑ በርካታ ውሾች በየመንገዱ ማየት የተለመደ ነው። እነዚህ ውሾች ኃላፊነት ወስዶ ቫይረሱን ለመከላከል የሚሰጠውን ክትባት እንዲከተቡ የሚያደርግ እና ንጽህናቸውን የሚጠብቅ ባለቤት ስለሌላቸው ለቫይረሱ የተጋለጡ ናቸው።

እንደ ሀገር በሽታውን በተመለከት ለማኅበረሰቡ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ የውሻ ንክሻ ሲያጋጥም ወደ ህክምና ተቋም ሄዶ ከመታየት ይልቅ ንቆ የመተው ወይም ባሕላዊ መድኃኒቶች የመጠቀም ሁኔታ ይታያል።

በገጠሪቱ የሀገሪቱ ክፍል ካለው የመረጃ እጥረት አንጻር የግንዛቤ እጥረቱ የሚሰፋ ይመስላል። በገጠር አካባቢ አብዛኛው ማህበረሰብ በግብርና ሥራ የሚተዳደር እንደመሆኑ ከውሻ ውጭ ከተለያዩ በሽታውን ሊያስተላልፉ ከሚችሉ እንስሳት ጋር የሚኖርበት ሁኔታ ስላለ ጉዳቱ የከፋ ሊሆን ይችላል።

በእብድ ውሻ ንክሻ በሽታ ዙሪያ በሽታው ከምን እንደሚመጣ፣ በሽታውን ለመከላከል በሚያስችሉ መፍትሔ ሃሳቦች በተመለከተ እና ሌሎች ከበሽታው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በህብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት ተመራማሪና የምርምር አማካሪ ከሆኑት አሰፋ ደሬሳ (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ።



**አዲስ ዘመን፡- የእብድ ውሻ በሽታ የሚመጣው ከምንድነው ?**

**ዶክተር አሰፋ፡-** ውሻን የሚያሳብደው በሽታ በእንግሊዝኛ(ጥራውሬሪስ) ተብሎ ይጠራል፡፡ በአማርኛ የእብድ ውሻ በሽታ ነው የምንለው፡፡ በሽታው የሚመጣው ከቫይረስ ሲሆን (አር.ኤን.ኤ ቫይረስ) ይባላል፡፡ ቫይረሱ ውሻን ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ደመ ሞቃት የሆኑ ወይም የጀርባ አጥንት ያላቸውን እንስሳት ሁሉ የሚያጠቃ ነው፡፡

በእኛ ሀገር ግን የተለመደው የውሻ እብደት በሽታ ተብሎ ነው፡፡ ምክንያቱም በሽታው ከመቶ 90 እጅ በአብዛኛው ውሾች ላይ የሚከሰት ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ማኅበረሰቡ ሁሌ ውሻ አብዶ ሲቅበዘበዝ ስለሚያይ ይሄ የውሻ እብደት ነው በሚል በተለምዶ ስያሜ አውጥቶለታል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሽታው ምን ዓይነት ጉዳት ያስከትላል?**

**ዶክተር አሰፋ፡-** የእብድ ውሻ በሽታ መቶ በመቶ ገዳይ ነው፡፡ በዚህ በሽታ የተያዘ ሰው ድኗል የሚል ሪፖርት እስካሁን ዓለም ላይ የለም። ምናልባት አንዳንድ ጥናቶች ላይ እንደሚታየው፤ በጣም ጥንቃቄ የሚደረግበት አያያዝ እና እንክብካቤ ተደርጎ እድሜውን ማራዘም የሚቻል ይሆናል እንጂ፤ በዚህ በሽታ ተይዞ የዳነ ሰው የለም፡፡

በሽታው በጣም አደገኛ፣ ገዳይ እና አስፈሪ ነው፡፡ ለእንስሳትም ሆነ ለሰው ምንም ዓይነት ልዩነት ሳያደርግ እኩል ገዳይ የሆነ በሽታ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ጥሩ ነገር ይህን በሽታ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል መሳሪያ ክትባት አለ፡፡

ችግሩ ክትባቱን እንደሚፈለገው መጠን የአለማግኘት ችግር አለ፡፡ ለበሽታው ሁለት ዓይነት ክትባት ነው ያለው፡፡ በሀገር ውስጥ የሚመረት እና ከውጭ ሀገራት የሚገባ፡፡ ከውጭ ሀገራት የሚገባው ትንሽ ምቾት ስላለው ብዙ ሰው በስፋት እሱን ነው የሚፈልገው፡፡ ነገር ግን እሱ ደግሞ ዋጋው የሚወደድበት ሁኔታ ስላለ በሚፈለገው ደረጃ ለማግኘት ያስቸግራል፡፡

ይህ በሽታ የእብድ ውሻ በሽታ የተባለበት ምክንያት በሽታውን በአብዛኛው የሚያሰራጩት ውሾች ስለሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ በውሾች ላይ ቁጥጥር ያስፈልጋል፡፡

እንደ ሀገር ጤናን የሚያስተባብር ኮሚቴ አለ፡፡ ይህ ኮሚቴ ጤና ሚኒስቴርን፣ ግብርና ሚኒስቴርን እና የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣንን በማስተባበር፤ በሽታውን በዋናነት በሚያሰራጩት ላይ የቁጥጥር ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

በሽታው ዱር እንስሳት እና ውሾች ላይ በስፋት የሚገኝ ከሆነ ቁጥጥሩ በሽታውን በዋናነት በሚያስተላለፉት ላይ ነው መሆን ያለበት፡፡ በኢትዮጵያ በውሻ ላይ ቁጥጥር ቢደረግ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር በጣም ይቀንሳል፡፡

አሁን ላይ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በዓለም አምስት ሺህ ሰዎች በእብድ ውሻ በሽታ ይሞታሉ። ከዛ ውስጥ አንድ ሶስተኛ የሚሆነው ከሰሃራ በታች ባሉት ሀገራት ላይ ነው፡፡

በእኛ ሀገር በተሰራ ጥናት ደግሞ ከ100 ሺህ ሰው ከአንድ እስከ ሁለት ሰው በየዓመቱ በበሽታው አማካኝነት ይሞታል፡፡ ስለዚህ ይህ በ120 ሚሊዮን ሕዝብ ቢወሰድ ብዙ ሰው ይሞታል ማለት ነው፡፡

ይህን ያህል ሰው ይሞታል የሚል መረጃ ባለበት እና 90 በመቶ በሽታውን የሚያስተላልፉት ውሾች እንደመሆናቸው በውሻ ላይ ቁጥጥር ቢደረግ፤ የሚሞተው ሰው ቁጥር ይቀንሳል፤ የክትባት ፍላጎት መጠንም እየቀነሰ ይመጣል፡፡

ውሻ የመኖር መብት አለው፡፡ ነገር ግን የውሻ ባለቤት ውሻን የሚያረባ ሰው በሕግ ማዕቀፍ መመራት አለበት፡፡ ውሻ ያለው ግለሰብ ንጽህናውን በመጠበቅ፤ የሚበላውን ምግብ በሥርዓት በማቅረብ እና መጠለያ እንዲኖረው በማድረግ በእራሱ ግቢ ውስጥ እንዲዝናና ማድረግ ይቻላል፡፡

ምክንያቱም ውሻ በጣም ለሰው ልጅ ቀረቤታ ያለው እና እንደ ቤተሰብ የሚታይ እንስሳ ስለሆነ በዚህ ልክ ከውሻ ጋር አብሮ መኖር ይቻላል። ነገር ግን አሁን በእኛ ሀገር የሚስተዋለው ነገር ውሻ በየቦታው ሜዳ ላይ ነው የሚታየው፡፡ ይሄ በሕግ ማዕቀፍ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፤ ውሾች በየዓመቱ መከተብ አለባቸው፡፡

አንድ ውሻ ከተወለደ በሶስት ወር የእድሜ ክልል ክትባት መውሰድ ይኖርበታል፡፡ በየዓመቱ ደግሞ የማጠናከሪያ ክትባት ይወስዳል፡፡ በዚህ ልክ እየታየ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ ይህን ተከታትሎ የማያደርግ የውሻ ባለቤት በሕግ አግባብ መጠየቅ አለበት፡፡ አሁን እዚህ ላይ ነው ክፍተቱ የሚታየው፡፡ ይሄ ወደ ሥራ ከገባ እና በየከተማው እንደዚህ ዓይነት ቁጥጥር ካለ እ.አ.አ በ2030 የተቀመጠውን ሰዎችን ከእብድ ውሻ በሽታ የመታደግ ጥረት ግብን ማሳካት ይቻላል፡፡

ግቡን ለማሳካት ትልቅ ማነቆ የሆነ ውሻን አለመቆጣጠር ነው፡፡ ይህን ለመቆጣጠር የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተቸገርነው ከሆቴሎች እና ከተለያዩ ተቋማት በሚደፉ ተረፈ ምግቦች ነው። በስፋት ባለቤት አልባ ውሾች የሚራቡት በእነዚህ አካባቢዎች ነው፡፡ ምግብ ከሌለ ሊራቡ አይችሉም፡፡ እንደ ሀገር ተረፈ ምግብ ለውሻ ተብሎ ነው የሚጣለው፡፡

እንደዚህ ዓይነት ልማዳዊ አሰራር ሊቀየር ይገባል፡፡ ውሻም እንደማንኛውም በጀት ኖሮት የሚመግበው ቤተሰብ ነው የሚፈልገው፡፡ እዚህ ሀገር የሕግ አሰራር ስላልተዘረጋ፤ ሰው በልማድ ነው ውሻን የሚይዘው፡፡ በልማዳዊ አሰራር ይህን በሽታ ለመቆጣጠር በጣም ያዳግታል፡፡

ችግሩን ለመቅረፍ የሁሉም ዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ተቀናጅተው የሚሰሩት ሥራ ነው፡፡ የሚሞተው ሰው እንደመሆኑ ጤና ሚኒስቴር ይመለከተዋል፤ የውሻውን ጤንነት የሚከታተለው ግብርና ሚኒስቴር ነው፤ የአ.አ ከተማ አስተዳደር፤ የእንስሳት ጤና ዘርፍ ናቸው፡፡ እነዚህን ሁሉ ዘርፎች ይመለከታቸዋል፡፡

ስለዚህ የእነዚህ ሴክተሮች አመራር አንድ ላይ ተረባርቦ የውሻ ቁጥጥር ካደረገ፤ በ2030 አንድም ሰው በእብድ ውሻ ተነክሶ መሞት የለበትም የሚለውን መርህ ማሳካት ይቻላል፡፡

**በአብዛኛው በሀገሪቱ ከተሞች ከቤታችን ወጣ ስንል ባለቤት አልባ የሆኑ በርካታ ውሾች በየመንገዱ ማየት የተለመደ ነው። እነዚህ ውሾች ኃላፊነት ወስዶ ቫይረሱን ለመከላከል የሚሰጠውን ክትባት እንዲከተቡ የሚያደርግ እና ንጽህናቸውን የሚጠብቅ ባለቤት ስለሌላቸው ለቫይረሱ የተጋለጡ ናቸው**

**አዲስ ዘመን፡- 90 በመቶ በሽታውን የሚያስተላልፈው ውሻ መሆኑን ገልጸውልናል፤ ከሌሎች እንስሳት በተለየ መልኩ ውሻ ለዚህ ቫይረስ ተጋላጭ የሆነው ለምንድነው?**

**ዶክተር አሰፋ፡-** ውሻ አመጣጡ ከዱር እንስሳት ቢሆንም ተላምዶ ከሰዎች ጋር የሚኖር እንስሳ ነው፡፡ ከሌሎች እንስሳት እና ከሰዎች ጋር ያለውም ቀረቤታ ትልቅ ነው፡፡

ሥጋ በሊታ እንደመሆኑ በተለያየ ቦታ ከተለያዩ እንስሳት ጋር ያለው ግንኙነቱ የበዛ ነው። የበሽታው መራቢያ መንገድም የውሻም ሆነ የሌሎች እንስሳት አንድ ነው፡፡ የበሽታው ቫይረስ የሚራባው አንጎል ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው እግሩ ላይ ቢነከስ በሽታው ቀስ እያለ ነው ወደ ነርቭ ውስጥ የሚገባውና አንጎሉን የሚያጠቃው፡፡

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## «የእብድ ውሻ በሽታ...

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

ግን የውሻ የመራባት መጠን ሲታይ አንድ እናት ውሻ እስከ ዘጠኝ ነው የምትወልደው። በኢትዮጵያ ሁኔታ ደግሞ ማህበረሰቡ ውሻን የሚያሳድገው ወንድ ወንዱን ነው፡፡ ዘጠኝ ከተወለዱት ሁለቱ ብቻ ቢወሰድ ሰባቱ ይጣላሉ። እነዚህ የተጣሉ ውሾች ከሌሎች ውሾች ጋር ሲገናኙ አንድ በበሽታው የተያዘ ካለ በመነካከስ እና በሌሎች መንገዶች ሊተላለፍ ይችላል፡፡ በእነዚህ ምክንያት የውሾች በሽታውን የማሰራጨት መጠን ጎልቶ ሊታይ ችሏል፡፡

በስፋት ሰዎችም በበሽታው ሊጎዳ የቻለው፤ ከሌሎች እንስሳቶች ይልቅ ለውሻ ያለው ቀረቤታ ከፍ ያለ ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ እስካሁን ባደረግነው ጥናት ስርጭቱ ውሻ ላይ ነው ጎልቶ የሚታየው፡፡

በተጠቀሱት ምክንያት ነው እንጂ ቫይረሱ የተለየ ውሻን የወደደበት ምክንያት የለም። ቫይረሱየሚባዛበትም መንገድ አንድ ዓይነት ነው፡፡ ሆኖም ግን ሊሰመርበት የሚገባው የውሻ አያያዛችን ነው ተጋላጭነታችንን ያሰፋው፡፡ ሌላ ሀገር የሌሊት ወፍ ነው በሽታውን በማሰራጨት የሚታወቀው፡፡ ደቡብ አፍሪካ ላይ ለምሳሌ (አንቲሎፒ) የሚባል የድኩላ ዘር ነው በሽታውን የሚያስተላልፈው፡፡

በእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ግን ውሻ የሚኖረው በዘልማድ ነው፣ የሚሰጠውም ምግብ ተረፈ ምርት ነው፡፡ አያያዛችን ውሻ ላይ በሽታ እንዲበዛ አድርጓል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከውሻ ውጭ በሽታውን የሚያስተላልፍ እንስሳ አለ?**

**ዶክተር አሰፋ፡-** ከተሰራው ጥናት አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ ዋነኛ የበሽታው አስተላላፊ ውሻ ነው፡፡ ሁለተኛ ድመት ናት፡፡ እነዚህ እንስሳት የቤት እንስሳት ስለሆኑ እና ከሰው ጋር ቅርበት ስላላቸው ያስተላልፋሉ እንጂ፤ ቀበሮ፣ አንበሳ፣ ነብር እና ሌሎችም ደመ ሞቃት የሚባሉ እንስሳት የእብድ ውሻ በሽታ አስተላላፊዎች ናቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አንድ ሰው በበሽታው ከተያዘ መዳን እንደማይችል ገልጸዋል፤ አንዳንዴ ውሻ ነክሷቸው ሐኪም ቤት እየሄዱ ህክምና የሚወስዱ አሉ። ይሄስ ህክምና የምንድነው?**


**ዶክተር አሰፋ፡-** በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። መዳኛው ክትባትና ክትባት ብቻ ነው፡፡ ሰው የማይድነው ካልተከተበ ብቻ ነው፡፡ ምን ማለት ነው ይሄ? እኛም ሀገር ክትባቱ አለ እናመርታለን። መርፌ አሰጣጡ ከውጭ ሀገራት ከሚገባው ክትባት ዓይነት በርከት ይላል እንጂ ነፍስ፤ ያድናል ሲያድንም አይተናል፡፡

እንደ ሌሎች በሽታዎች ቫይረሱን ሊገል የሚችል የሚዋጥ መድኃኒት የለውም እንጂ፤ አንድ ሰው በተነከሰ በ24 ሰዓት ውስጥ ቫይረሱ እንዳይራባ የሚያደርግ ክትባት ከወሰደ ቫይረሱ አይራባም፡፡

የበሽታው የመደራጃ ጊዜ አንድ ሰው ከተነከሰ ከሶስት ሳምንት እስከ አንድ ዓመት እንደሆነ ነው ሳይንሱ የሚገልጸው፡፡ በሽታውን አስቸጋሪ ያደረገው የመደራጃ ጊዜው ረጅም መሆኑ ነው። ሌሎች ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር በርካታ ሥራዎች ተሰርተው እኮ በሽታውን ቁጥጥር ስር ማዋል ተችሏል፡፡

ሌላው ደግሞ ማህበረሰቡ ለበሽታው ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ አንድ ሰው በውሻ ሲነከስ የውሻ ቁስል ነው ተብሎ ዝም ብሎ ይተወዋል፡፡ ስለዚህ በባሕላዊ መድኃኒት ወይም በሌሎች መንገዶች ለመዳን ይሞክራል፡፡

ዘግይቶ ወደ ህክምና ሲመጣ ተጎድቶ እናያለን። መሆን ያለበት በ24 ሰዓት ውስጥ በራሱም ሆነ በሌላ ውሻ የተነከሰ ሰው ሐኪም ቤት ሄዶ መናገር አለበት፡፡ ሐኪሙ አይቶ ክትባት የሚያስፈልገው ከሆነ ህክምና እንዲከታተል ያደርገዋል፡፡ ክትባት ስላለው መድኃኒት አለው ማለት ነው፡፡ ችግር



የሆነው ነገር ግን የሰው ግንዛቤ ስላላደገ ሐኪም ቤት ሄዶ ክትባቱን በአግባቡ አለመውሰዱ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አንድ ሰው በውሻ ሲነከስ የባሕል መድኃኒቶችን የመጠቀም ሁኔታ አለ። የመድኃኒቱ አስተማማኝነት ምን ያህል ነው?**

**ዶክተር አሰፋ፡-** በሀገራችን ሰፊ የሆነ የባሕል መድኃኒት ሀብት አለ፡፡ በእውነቱ ለሌሎች በሽታዎች ፍቱን የሆኑ የባሕል መድኃኒቶች አሉን። ከእብድ ውሻ በሽታ ጋር ተያይዞ ባደረግነው ጥናት ብዙ ሞክረን ሁለት ችግሮች ገጥመውናል፡፡ አንደኛ የባሕል መድኃኒት የሚቀምሙት ትክክለኛ መረጃ ሰጥተው ወደሚሰሩበት ቦታ ገብተን እንድንፈትሽ አይፈቅዱም፡፡

ለምን እንደማያስገቡ ምክንያታቸው ሲጠየቅ መድኃኒቱ በሶስተኛ ሰው ከታየ ይረክሳ የሚል ምክንያት ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ችግር ምክንያት ያለው የባሕል መድኃኒት ፈዋሽነት በጥናት አልተረጋገጠም፡፡ ነገር ግን ጥናቱ ወደፊትም ይቀጥላል፡፡

ሌላኛው ከባሕል መድኃኒት ጋር ተያይዞ ያለው ችግር፤ በውሻ የተነከሰ ሰው የባሕል መድኃኒቱን ከወሰደ በኋላ መድኃኒቱ ይረክሳል ተብሎ ስለሚታሰብ፤ መድኃኒቱን የወሰደው ግለሰብ ለ40 ቀን ያህል ወንዝ እንዳይሻገር ይደረጋል፡፡

በዚህ ሁኔታ በውሻ የተነከሰው ሰው ክትባት ለመውሰድ ወደ ህክምና ተቋማት አይመጣም። አንድ ሰው በሽታው ከተደራጀበት በኋላ በዛ ቢባል በሕይወት ሊቆይ የሚችለው ከ55 እስከ 60 ቀን ነው፡፡

አንድ ሰው 40 ቀን ቆይቶ ለህክምና ከመጣ ለሞት ከተቃረበ በኋላ ነው፡፡ የሚሰጠው ክትባት በሽታው ምልክት ካሳየ በኋላ ቢሰጥ ምንም ፋይዳ የለውም፡፡

ክትባቱ የሚያገለግለው ምንም ዓይነት ምልክት ከመታየቱ አስቀድሞ ነው፡፡ በውሻ መነከስ የሚያጋጥም ነገር ነው፡፡ ከተነከሱ በኋላ ቫይረሱ ተደራጅቶ የማበድ ምልክት ከታየ በኋላ ክትባቱ ስለማይሰራ ቀደም ብሎ መምጣት መፍትሔ ያለው ነገር ነው፡፡

በህብረተሰቡ ዘንድ በግንዛቤነት መያዝ ያለበት፤ በሽታው ምልክት ካሳየ በኋላ ለምሳሌ ለሀጭ የማዝረብረብ፤ ብዙ ማውራት፣ ለመዋጥ መቸገር ፣ ውሃ መጥላት፣ የማቃጠል እና ሌሎች ምልክቶች የሚታዩበት ደረጃ ከደረሰ ክትባቱ አይሰራም፡፡ ክትባቱ የሚሰራው ወዲያው በውሻ

> **ከተሰራው ጥናት አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ ዋነኛ የበሽታው አስተላላፊ ውሻ ነው። ሁለተኛ ድመት ናት። እነዚህ እንስሳት የቤት እንስሳት ስለሆኑ እና ከሰው ጋር ቅርበት ስላላቸው ያስተላልፋሉ እንጂ፤ ቀበሮ፣ አንበሳ፣ ነብር እና ሌሎችም ደመ ሞቃት የሚባሉ እንስሳት የእብድ ውሻ በሽታ አስተላላፊዎች ናቸው**

እንደተነከሱ ከተወሰድ መሆኑ ግንዛቤው ብዙም ማህበረሰቡ ጋር የለም፡፡ ይህንን በመገናኛ ብዙሃን እና በተለያዩ መንገዶች ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሽታው የሚተላለፈው በንክሻ ብቻ ነው። ወይስ ሌሎች መተላለፊያ መንገዶች አሉ?**

**ዶክተር አሰፋ፡-** ምንድነው መሰለሽ፤ በአብዛኛው በጥርስ መነከስ ሲያጋጥም፤ ዞሮ ዞሮ በሽታው የሚገባው በምራቅ አማካኝነት ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ሲነከስ ውሻው ታማሚ ከሆነ ቫይረሱ በምራቅ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ጭንቅላት ውስጥ ተራብቶ ወደታች ሲመለስ እጢዎችን ነው የሚበክለው፡፡ የሚወጣው ፈሳሽ በሙሉ የቫይረሱ ምንጭ ነው፡፡

ጥናቶች እንደሚሉት የቫይረሱ ምልክት አንዳንዴ ያስተፉል ይላል፡፡ ለምሳሌ እኔ በሽታው ኖሮብኝ በየቦታው ብተፋ በምራቅ አማካኝነት ይተላለፋል፡፡ በንክሻ ብቻ አይደለም ማለት ነው። አንዳንድ ጥናቶች ደግሞ እንደሚሉ በጭረት አማካኝነት እንደሚተላለፍ ያስረዳሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች በውሻ ሲቧጨሩ «አልነከሰኝም ዝም ብሎ ጫር ያደረገኝ » ብለው ችላ የሚሉበት ሁኔታ አለ፡፡ ሆኖም በጭረት ብቻ በሽታው ሊተላለፍ ይችላል፡፡

ጭረቱ በሚፈጠርበት ወቅት ቆዳችን ስለሚቆጣ ቫይረሱ ሊገባ ይችላል፡፡ በርግጥ ቆዳ ሲቆረጥ ነው ቫይረሱ የሚገባው፡፡ እኛ ግን እንደ ባለሙያ እንደተቆረጠ ነው የምናየው፡፡ ስለዚህ ይሄ ችግር አለው ይሄ ችግር የለውም ብሎ ምላሽ የሚሰጠው ሐኪም ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሽታው በላብ አማካኝነት ይተላለፋል?**

**ዶክተር አሰፋ፡-** እንግዲህ እስካሁን ባለን መረጃ፤ በላብ ይተላለፋል፣ በመጨባበጥ እና በመሳሳም ይተላለፋል የሚሉ ጥያቄዎች አሉ፡፡ ነገር ግን አይተላለፍም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ይህን በሽታ ለመቆጣጠር ከማን ምን ይጠበቃል?**

**ዶክተር አሰፋ፡-** አሁን እኔ እየሰራሁ ያለሁበት ተቋም ለረጅም ዘመን ክትባት ሲያመርት ኖሯል፡፡ ለውሻም ለሌሎች እንስሳትም፡፡ አሁን ላይ ቢሾፍቱ ብሔራዊ እንስሳት ተቋም በስፋት አምርቶ እያሰራጨ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ኢንስትቲዩት በውሻ ለተነከሱ ሰዎች የሚሆን ክትባት ሲያመርት ቆይቷል፡፡ አሁን የማምረት ሥራ ወደ አርምን ሃንሰን ምርምር ኢንስትቲዩት ተላልፏል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ ተቋማት ክትባት በማምረት ኃላፊነት አለባቸው ማለት ነው፡፡

በሌላ ዘርፍ ደግሞ በግብርና እና በከተማ አስተዳደር የእንስሳት ጤና የሚከታተሉ ዘርፎች አሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ የውሻ ባለቤቶች በአግባብ ውሾቻቸውን እንዲያስከትቡ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

ተከታትሎ ውሻውን የማያስከትብ አካል በሕግ አግባብ እንዲጠየቅ ማድረግ ይኖርበታል። ከባለሙያውም ሆነ ይህንን ዘርፍ የሚመራው ተቋም በዚህ ልክ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ ሆኖም በዚህ ረገድ ክፍተት አለ፡፡

በሀገር ደረጃ ደግሞ የውሻ በሽታን የሚከታተል አንድ የጤና ጽሕፈት ቤት አለን። ጽሕፈት ቤቱ ባደረገው ጥናት በሽታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ ሊመጣ የቻለው በውሾ ላይ የሚደረገው ቁጥጥር አነስተኛ በመሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ አሁን ስትራቴጂውን ለመከለስ ታስቧል፡፡ ውሾችን ለመቆጣጠር በሁሉም ሴክተር ምን መደረግ አለበት? የሚል የባለሙያ ምክክር በሁሉም ደረጃ ባሉ መዋቅሮች እየተደረገ ነው፡፡ በቀጣይ በሚሰራው ሥራ በበሽታው አንድም ሰው እንዳይሞት የተቀመጠውን ግብ ማሳካት ይቻላል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

በሽታውን በማስቀረት ረገድ የመጀመሪያው ባለድርሻ አካል የውሻ ባለቤት ነው፡፡ የውሻ ባለቤቶች ቢተባበሩን እና ውሾቻቸውን በአግባቡ ቢይዙ በሽታውን ከ50 በመቶ በላይ እንዳይዛመት ማድረግ ይቻላል፡፡

ከዛ ውጭ የሚሆን ከሆነ ደግሞ የሕግ ማዕቀፍ መኖር አለበት፡፡ እስካሁን ትልቁ አድምተን ያልሰራነው፤ መሬት አልወርድ ያለው እሱ ነው። አንዳንዴ አንዳንድ በሽታዎች ክትባት ወይም መድኃኒት ስለሌላቸው ነው ሰው የሚሞተው። ይሄ እኮ በእጃችን ላይ ያለ ነገር ሆኖ በትክክል መሥራት ባለመቻላችን ችግሩ እየከፋ ሄዷል፡፡

ለሁሉም ባለድርሻ መሥሪያ ቤቶች የተሰጣቸው ኃላፊነት አለ፡፡ እሱን አንድ ላይ አቀናጅቶ የሚሰራ መሥሪያ ቤት ነበር እስካሁን ክፍተት የነበረው፡፡ አሁን ግን የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት በአዋጅ ጸድቆ ተቋሙ እንዲመሰረት ተፈቅዷል፡፡ ስለዚህ በቀጣይ ለውጥ ይኖራል ብዬ አስባለሁ፡፡

# ፈጣን ህክምና አደጋን ለመከላከል

አስናቀ ፀጋዬ

በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት በየዓመቱ 4 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሰዎች እንደሚሞቱ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ አሃዝ ወባ፣ ሳምባና ኤች አይ ቪ ኤድስ ተዳምረው በየዓመቱ ከሚያስከትሉት ሞት የበለጠ ነው፡፡ ይህም አደጋዎች ከሌሎች በሽታዎች የበለጠ የሰው ልጆችን ሕይወት በመቅጠፍ ረገድ ወደር እንዳልተገኘላቸው ያመላክታል፡፡

በኢትዮጵያም አደጋ የሰዎችን ሕይወት በመቅጠፍና ከፍተኛ የአካል ጉዳት በማድረስ የመሪነቱን ቦታ ይወስዳል፡፡ እያደረሰ ያለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስም ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ተላላፊና ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ቀጥሎ በሶስተኛ ደረጃ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ጫና እያስከተለ የሚገኝም ነው፡፡

እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት ከሆነ አደጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ 10 ከመቶ የሚሆነውን ሞት ያስከትላል፡፡ ቲቢ፣ ወባና ኤች አይ ቪ ኤድስ በጋራ ሆነው ከሚያስከትሉት 32 ከመቶ ሞት በላይ በአደጋ ምክንያት ይከሰታል፡፡ በኢትዮጵያ ደግሞ ከ65 እስከ 85 በመቶ አደጋ የደረሰባቸው ሰዎች በሪፈራል ሥርዓት መዘግየት፣ በትራንስፖርት እጦት፣ በፋይናንስ እጥረትና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት ዘግይተው ሆስፒታል እንደሚደርሱ ይነገራል፡፡

ከዚህ አንፃር አደጋ በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያየ መልኩ ከፍተኛ ጫና እያደረሰ ስለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተለይ ኢትዮጵያን በመሰሉና ደህንነትና ጥንቃቄ ትኩረት በማይሰጥባቸው ብሎም አደጋ ከተከሰተም በኋላ ለተጎጂዎች በቂ ምላሽ የሚሰጥ የድንገተኛ አደጋ ህክምና ማዕከል እንደልብ በሌለባቸው ሀገራት እያደረሰ ያለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የጤና እክል ጫና ከፍተኛ ነው፡፡

አደጋ አምራቹንና ወጣቱን የህብረተሰብ ቁጥር በመቀነስ፣ ብዙዎችን ለሞት በመዳረግ፣ ለአካል ጉዳት በማጋለጥ፣ በህመምተኞች፣ በቤተሰቦቻቸውና በማህበረሰቡ ላይ ከባድ ተፅእኖ በማሳደር፣ ለከፍተኛ የህክምና ወጪና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በመዳረግ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል፡፡

ዶክተር ስንታየሁ ቡሳ በሞያቸው የአጥንት ቀዶ ሐኪምና የአጥንትና መገጣጠሚያዎች ንዑስ ስፔሽያሊስት ናቸው፡፡ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ የአጥንት ህክምና ትምህርት ክፍል ዲን ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ አሁን ደግሞ ቦሳድ /Bone Setting Associated Disability/ በተሰኘው ሀገር አቀፍ የጥናትና የምርምር ቡድን አማካኝነት በኢትዮጵያ በአጥንትና መገጣጣጠሚያ ጉዳቶች ዙሪያ በተሰራው የሦስት ዓመት ጥናት ውስጥ አባልና መስራች ናቸው፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፣ አደጋ በኢትዮጵያ የሞትና የአካል ጉዳት በማድረስ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በማድረስ ረገድም ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑና በሽታዎች ተወጥራ ትገኛለች፡፡ ከነዚህ በሽታዎች ቀጥሎ ደግሞ ሀገሪቱ በከፍተኛ አደጋ ጫና ውስጥ ነው ያላችው፡፡ በየእለቱ አደጋዎችን መስማት እየተለመደ መጥቷል፡፡

በኢትዮጵያ 10 ከመቶ ያህሉ ሞት የሚከሰተው በአደጋ ምክንያት ነው፡፡ ይህም ቲቢ፣ ወባና ኤች አይ ቪ ኤድስ ተደምረው ከሚያደርሱት ሞት በ32 ከመቶ ከፍ ይላል፡፡ በኢትዮጵያ አስፈላጊውን ህክምና በማድረግ አብዛኞዎቹ ጉዳቶችን መከላከል ይቻላል፡፡ ይሁንና እስከ 85 ከመቶ ያህል የሚሆኑ አደጋ የደረሰባቸው ታማሚዎች ሆስፒታል ዘግይተው በመድረሳቸውና አፋጣኝ ህክምና ባለማግኘታቸው ለከፋ አካል ጉዳትና ለሞት ይዳረጋሉ፡፡

አብዛኛዎቹ ሪፈር ተፅፎላቸው ወደ ሆስፒታል የሚላኩት ዘግይተው ነው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ትራንስፖርት በማጣት፣ በገንዘብ እጥረትና ባሕላዊ ህክምናን እንደ መጀመሪያ አማራጭ በመውሰድ ዘግይተው ወደ ሆስፒታል ይመጣሉ፡፡ በነዚህ ምክንያቶች ለከፋ አካል ጉዳትና ለሞት ይዳረጋሉ፡፡

ዶክተር ስንታየሁ እንደሚያብራሩት፣ በአሁኑ ጊዜ አደጋ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ለአደጋ የሚያጋልጡ ተገቢ ላልሆኑ ባህሪያትም አሉ፡፡ አብዛኛው ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ የጭንቅላት መከላከያ



ስንታየሁ ቡሳ ዶ/ር፤

ቆብ አያደርግም፡፡ መኪና አሽከርካሪዎችም ከትራፊክ ለመሸሽ እንጂ ራሳቸውን ለመጠበቅ አይደለም ቀበቶ የሚያደርጉት። በአንድ የትራንስፖርት መጓጓዣ ላይ ለምሳሌ ሞተር ሳይክል የሚጠቀሙ የሰው ቁጥርም ከመጠን በላይ ነው፡፡

በፍጥነት ማሽከርከር፣ ጠጥቶ ማሽከርከር፣ ጫት ቅሞ ማሽከርከር፣ በግንባታ ቦታዎች ላይ በቂ የደህንነት መሳሪያዎችና መመሪያዎች አለመኖርና ቢኖሩም ተግባራዊ አለመሆን ፣ የመንገድ ላይ ደህንነት በሚፈለገው ልክ አለመኖር፣ ጦርነትና ግጭቶችም ለአደጋዎች መከሰት ቁልፍ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

በኢትዮጵያ አደጋዎች የሚከሰቱት በሁለት ዓይነት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው ሳይታሰብ ሁለተኛው ደግሞ ታስቦበት ነው፡፡ ሳይታሰቡ የሚያጋጥሙ ጉዳቶች ሰዎች በሥራ ላይ እያሉ የሚገጥማቸው፣ የትራፊክና መሰል አደጋዎች ናቸው፡፡ ታስበው የሚጋጥሙ አደጋዎች ደግሞ ሰዎች ራሳቸውን ለመጉዳትና ለማጥፋት የሚያደርጓቸው ሙከራዎች፣ በግለሰቦች መካከል ያለ ፀብና ሌሎችም ናቸው፡፡

በአደጋ ምክንያት አብዛኛው ሞት የሚከሰተው ሰዎች በጭንቅላታቸው ላይ ጉዳት ሲደርስባቸው ነው፡፡ ለዛም ነው ሰዎች በግንባታ ቦታዎች ላይና ሞተር ብስክሌት ሲያሽከረክሩ የጭንቅላት ቆብ ማድረግ አለባቸው የሚባለው፡፡ በተመሳሳይ ወድቀው አደጋ የሚደርስባቸው ሰዎች ቁጥርም ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሰው አደጋ ከደረሰበት በኋላ መቼና የት ነው የሚሞተው የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

አደጋ ከሚደርስባቸው ውስጥ 50 ከመቶዎቹ የሚሞቱት እዛው አደጋው የደረሰባቸው ቦታ ላይ ነው። 30 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ አደጋ ደርሶባቸው ወደ ሆስፒታል ከመጡ በኋላ በሰዓታት ውስጥ የሚሞቱ ናቸው፡፡ 20 ከመቶዎቹ ሆስፒታል ከመጡ በኋላ ከሶስትና አራት ሳምንት ቆይታ በኋላ የሚሞቱ ናቸው፡፡ 50 ከመቶ ያህሉን የአደጋ ሞት ማንኛውም ሐኪም ሊከላከለው አይችልም፡፡ ይህን ሞት መከላከል የሚቻለው አደጋው እንዳይደርስ የመከላከል ሥራ አስቀድሞ ከተሰራ ብቻ ነው፡፡

30 ከመቶ በአደጋ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ሞት በህክምና መከላከል ይቻላል፡፡ እነዚህ 30 ከመቶ የሚሆኑ ሞቶች ሊከሰቱ የሚችሉት በቂ የአምቡላንስ አገልግሎት አለመኖር፣ አደጋው በደረሰበት ቦታ ላይ የሚሰጠው ህክምና በቂ አለመሆን፣ ወደ ህክምና ቦታ ከመጡ በኋላ በቂ ህክምና ባለማግኘት ነው፡፡

ስለዚህ አደጋው በደረሰበት ሊሰጥ የሚችለውን ህክምና በደንብ በማስተካከል፣ አምቡላንሶችን በመመደብ አደጋ የደረሰባቸው ሰዎች ወደ ሆስፒታል የሚመጡበትን ሁኔታ በመፍጠርና በሆስፒታል የሚሰጠውን ህክምና በማስተካከል ሊከሰት የሚችለውን ሞት መቀነስ ይቻላል። ከዚህ ባለፈ አደጋ ለደረሰባቸው ሰዎች በሆስፒታሎች ተገቢ ህክምናዎች በማድረግ 20 ከመቶ በአደጋ ሊከሰት የሚችለውን ሞት መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በነዚህ መንገዶች 50 ከመቶ ያህሉን በአደጋ ምክንያት የሚከሰተውን ሞት መከላከል ይቻላል፡፡

ለምሳሌ በሀዋሳ ከተማ በተጠና ጥናት ወደ 1 ሺ 920 የሚሆኑ አደጋዎች ደርሰዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ 80 ከመቶ የሚሆኑት ወንዶች ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ደግሞ በአማካይ በ28 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ይህም በአደጋ ምክንያት እየተጠቃ ያለው አምራቹና ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል እንደሆነ ያሳያል፡፡ አደጋ በወጣቱ ላይ የአካል ጉዳት ሲያስከትል በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይም ተዘዋዋሪ ተፅእኖ የሚያሳድር ነው፡፡

እንደ ዶክተር ስንታየሁ ገለፃ በኢትዮጵያ በአብዛኛው ለአደጋ ዋነኛ መንስኤ የሚሆነውና 53 ከመቶ ድርሻ የሚወስደው የትራፊክ አደጋ ነው፡፡ 18 ከመቶ ያህሉ ደግሞ በሥራ ላይ በአብዛኛው በመውደቅ መንስኤ የሚከሰት ነው፡፡ ከመጡት አደጋዎች 86 ከመቶ ያህሉ የጭንቅላት፣ የእጅና የእግር አደጋ ያጋጠማቸው ናቸው፡፡ በሆስፒታል ውስጥም እስከ 78 ቀን ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ በሆስፒታል ቆይታቸው የምግብ፣ ህክምና፣ የአልጋ ወጪዎች አሉባቸው፡፡ ከቤተሰብ ተነጥለው መምጣታቸውና ከሥራ መስተጓጎላቸውም ትልቅ የኢኮኖሚ ጫና አለው፡፡

በአንድ ዓመት ውስጥ ከአደጋ ጋር በተያያዘ 26 ሰዎች ሞተዋል፡፡ ቁጥሩ ትንሽ ቢመስልም ሁልጊዜም ቢሆን ሰነድ ያለው በሆስፒታሎች ብቻ ከመሆኑ አኳያ አደጋው በደረሰበት ቦታ ላይ የሚሞተው ሰው ቁጥር ሲጨመር ከዚህ በላይ ይሆናል፡፡ ይህ አሃዝ ወደ ሀገር አቀፍ ነባራዊ ሁኔታ ሲቀየር አደጋ በብዛት የሚያጠቃው ወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ ይህም ለቤተሰብ፣ ለማህበረሰብና ለሀገር ከፍተኛ ተፅእኖ አለው፡፡

አንድ ሰው አደጋ የሚደርስበት አስቦ አይደለምና ድንገት አደጋ ሲደርስበት ለህክምና ከሚያወጣው ወጪ ጀምሮ በሕይወት እስከሚለይበት ድረስ የሚያመጣው ትልቅ የኢኮኖሚ ቀውስ አለ፡፡ ስለዚህ አደጋ ይህን ያህል ተፅእኖ የሚያስከትል ከሆነ አደጋን አስቀድሞ ለመከላከልና ከተከሰተም በኋላ በአፋጣኝ አክሞ ለማዳን ብዙ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

**‹‹ኢትዮጵያ አደጋ ከተከሰተ በኋላ አደጋውን ለማከም የሚያስችል የተሟላ አቅም የላትም። በተለይ ከፍተኛ የጭንቅላት አደጋ ሲያጋጥም ህክምና የሚደረገው ከውጭ ተገዝተው በሚገቡ እቃዎች ነው። እቃዎቹም በአብዛኛው ውድ ናቸው። ስለዚህ ከሁሉ በፊት መሰራት ያለበት ሥራ አደጋን አስቀድሞ መከላከል ነው። ሰዎች ከተጎዱ በኋላ በተጎዱበት ቦታ ላይ ከሚሰጠው ህክምና ባሻገር ዋናው ህክምና የሚሰጥበት ቦታ ላይ የሚደረጉትን ህክምናዎች ማጣመር ያስፈልጋል። የሪሃብሊቴሽን ህክምናም እንደዚሁ ያስፈልጋል››**

ኢትዮጵያ አደጋ ከተከሰተ በኋላ አደጋውን ለማከም የሚያስችል የተሟላ አቅም የላትም፡፡ በተለይ ከፍተኛ የጭንቅላት አደጋ ሲያጋጥም ህክምና የሚደረገው ከውጪ ተገዝተው በሚገቡ እቃዎች ነው፡፡ እቃዎቹም በአብዛኛው ውድ ናቸው፡፡ ስለዚህ ከሁሉ በፊት መሰራት ያለበት ሥራ አደጋን አስቀድሞ መከላከል ነው፡፡ ሰዎች ከተጎዱ በኋላ በተጎዱበት ቦታ ላይ ከሚሰጠው ህክምና ባሻገር ዋናው ህክምና የሚሰጥበት ቦታ ላይ የሚደረጉትን ህክምናዎች ማጣመር ያስፈልጋል፡፡ የሪሃብሊቴሽን ህክምናም እንደዚሁ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ረገድ የሚዲያ ተቋማትም የራሳቸው ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በተለይ በሥራ ቦታ ላይ የሥራ ላይ ደህንነት እንዲኖርና በዚህ ላይ የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል። አንድ ሰው አደጋ ሲደርስበት ሆስፒታል ከመድረሱ በፊት ሊሰጠው በሚችለው ህክምና ዙሪያ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ማስተዋወቅ ከተቻለም ግንዛቤ መፍጠር ይገባል፡፡ ይህን ማድረግ የሚቻል ከሆነ በአደጋ ምክንያት የሚከሰቱ አብዛኛዎቹን ሞቶች መቀነስ ይቻላል፡፡

ከዚህ ባሻገር በጤና ተቋም ውስጥ በአብዛኛው የሚታየው ችግር ተጎጂዎች ዘግይተው ወደ ህክምና ተቋም መምጣት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ጤና ጣቢያዎች ላይ የሚሰጠው ህክምና በቂ አለመሆንም ተጨማሪ ችግር ነው፡፡ ይህንን ክፍተት በማየትም ነው አብዛኛዎቹ ታካሚዎች የባሕላዊ ህክምናን መርጠው ወደ ወጌሻ የሚሄዱት፡፡

ስለዚህ በመጀመሪያ ደረጃ ጤና ጣቢያዎች ላይ የሚሰጠውን ህክምና ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ ታማሚዎች ለህክምና የሚሆናቸው በቂ ገንዘብ አለመኖርም በአደጋ ምክንያት የሚከሰት ሞትን ከሚጨምሩ ምክንያቶች ውስጥ ይጠቀሳል፡፡ ስለዚህ አደጋ የማህበረሰብ ትልቅ የጤና ችግር መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለይ አስቀድሞ መከላከል ላይ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## በቁጭት የተገባበት የጤፍ ዱቄት ፋብሪካው ስኬት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የጤፍ እንጀራ ከአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ማዕድ ላይ የማይጠፋ የምግባቸው ሁሉ ቁንጮ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከጤፍ ለሌሎች የተለያዩ የምግብ አይነቶችን መሥራት ተጀምሯል፡፡ ጤፍ በሌሎች ሀገሮችም ተፈላጊ እየሆነ መጥቷል፡፡

ጤፍ እንጀራ ለመሆን ከማምረቱ ሥራ ጀምሮ ብዙ አድካሚ ሂደቶችን ያልፋል፡፡ ምርቱ ተበጥሮ፣ ተነፍቶና ተንገዋሎ ይፈጫል፡፡ የመፍጨቱ ሥራም በባህላዊም በዘመናዊ መንገድ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ አሁን ደግሞ እንደ ስንዴና ሌሎች ምርቶች ሁሉ በፋብሪካ ደረጃ በጥራት ተዘጋጅቶ ለገበያ መቅረብ ጀምሯል፡፡

የኢትዮጵያውያን የዕለት ተዕለት ምግብ የሆነው የጤፍ እንጀራ ዱቄት እንደ ስንዴ ሁሉ በፋብሪካ ደረጃ ለምን አይዘጋጅም፤ ያለችው ብርቱ ኢትዮጵያዊት ጤፍን በፋብሪካ ደረጃ በጥራት ማዘጋጀት ከጀመረች ዓመታትን ተቆጥረዋል።

ጤፍን በፋብሪካ ደረጃ ማዘጋጀት እምብዛም ባልተለመደበት ወቅት ፣ የዕለቱ የስኬት እንግዳችን ለጤፍ ካላት ስስት የተነሳ ግን ሞክራዋለች፤ መሞከር ብቻም አይደለም ሙከራዋን ወደ ተግባር ለውጣ ውጤታማ ሆናበታለች፡፡

ለዚህም ጤፍን ብቻ መፍጨት የሚችል ማሽን ራሷ ዲዛይን በማድረግ በቻይና አስመርታ ጤፍ የሚፈጭ ፋብሪካ ገንብታለች፡፡ የጤፍ ዱቄቱ ሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍን በፋብሪካ ደረጃ በጥራት አዘጋጅታ ለገበያ ማቅረብ በመቻሏ ዕውቅናን አትርፋለች፡፡

በንግድ ሥራ ስመ ጥር ከሆነ ቤተሰብ የተገኘችውና ይህን የጤፍ ዱቄት በፋብሪካ በማምረት ላይ የምትገኘው የዕለቱ እንግዳችን ሙና መሀመድ ትባላለች። የፋብሪካ ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ ሙና መሀመድ ፤ ምንም እንኳን በነጋዴ ቤተሰብ ውስጥ ለንግድ ሥራ ቅርብ ሆና ብታድግም ንግድ ውስጥ ዘው ብላ አልገባችም፡፡ ከዛ ይልቅ የቀለም ትምህርቷን ተምራ፤ የንግድ ሥራንም እንዲሁ ተምራ የገበያ ባለሙያ በመሆን ጭምር ከስር ከመሰረቱ ተለማምዳ፤ ልምድና ዕውቀትን ቀስማ ነው ወደ ግል ሥራዋ የገባችው፡፡

የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን በተለይም የፋብሪካ ማሽኖችን በመሸጥ ብዙ ሠርታለች፡፡ ከብዙ ጥረትና ትጋት በኋላም ሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍ ፋብሪካን በመገንባት በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ጥራትና ጥንቃቄ በፋብሪካ ደረጃ የጤፍ ዱቄትን አዘጋጅታ ለገበያ እያቀረበች ትገኛለች፡፡

አዲስ አበባ ከተማ አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አካባቢ ተወልዳ ያደገችው ሙና፤ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በሀገር ውስጥ ተከታትላለች፤ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ በውጭ ሀገር ነው የተከታተለችው፡፡

በአሜሪካ የሒሳብ ትምህርትን በኮሌጅ ደረጃ አጠናቅቃ ወደ ሀገር ቤት ስትመለስም እንዲሁ በቤተሰብ ቢዝነስ ውስጥ ዘው ብላ አልገባችም፡፡ እንደ ማንኛውም ሰው ተቀጥራ ሠርታለች፡፡ በዚህም ቤተሰቦቿ እንደ አለቃም እንደ አባትና ወንድም ሆነው ብዙ አስተምረዋታል፡፡ የንግድ ሥራን ከታች የጀመረችው ሙና፤ በወቅቱ ወጣትነት ሳያታልላት ለሥራ ትልቅ ፍቅርና አክብሮት እንዲሁም ጥረትና ትጋት ነበራት። ይህን የተረዱት ቤተሰቦቿም እምነት ያሳድሩባታል። «ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል» እንዲሉ ከፍ ያሉ የንግድ ሥራዎችን በኃላፊነት መሥራት እንድትችል ፈቅደውላታል፡፡

ቤተሰቡ በስፋት በተሠማራባቸው የአስመጪና ላኪ ንግድ ሥራዎች ውስጥ ትልቅ ተሳትፎ የነበራት ሙና፤ በተለይም ማሽኖችን በማስመጣት ለፋብሪካዎች በማቅረብ እና ወደ ሥራ በማስገባት በኩል ሰፊ ድርሻ ነበራት፤ በወቅቱ የዱቄት፣ የዘይት፣ የፕላስቲክና ሌሎች ፋብሪካዎች ማሽኖችን ከውጭ በማስመጣት ትሸጥ ነበር፡፡ ከሀገሪቱ ፋብሪካዎች የአብዛኞቹን ማሽኖች በመሸጥ እንዲሁም በሥራ ላይ የሚገጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ከቴክኒሻኖች ጋር ክትትል በማድረግ በርካታ ሥራዎችን ሠርታለች፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ጭምር ማሽኖቹ በትክክል መሥራት እንዲችሉ ድጋፍ አደርግ ነበር የምትለው ሙና፤ በዚህ አጋጣሚ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ክፍል የማየት ዕድል አግኝቻለሁ ትላለች፡ ፡ ፋብሪካ ማቋቋም ፈልጎ ማሽን የገዛ ማንኛውም ደንበኛ የትም ይሁን የት ባለበት ሆኖ አገልግሎት ማግኘት እንዲችል የተቻላትን ሁሉ ታደርግም ነበር፡፡ ከደንበኞቿ ጋር ያላት ግንኙነት ለአንድና ለሁለት ዓመት ሳይሆን እስከመጨረሻው እንደሆነም አስረድታለች፡፡

በዚህ መልክ የንግድ ሥራን በተለይም በማሽን ሽያጭ፣ ተከላና ጥገና ሥራ ላይ ዓመታትን የሠራችው ሙና፤ ከብዙ



**የሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍ ፋብሪካ ባለቤት ሙና መሀመድ ፤**

ትጋትና ጥረት በኋላ የራሷን ፋብሪካ ማቋቋም እንደቻለች ትናገራለች፡፡

አስመጪዎች በርካታ ማሽኖችን ሲያስመጡ የተከታተለችው ሙና፣ አንድም ጊዜ የጤፍ ማሽን የሚያስመጣ ሰው ሳታስተውል ትቀራለች፡፡ «ጤፍን እና ኢትዮጵያውያንን መነጣጠል አይቻልም፤ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው» በማለት የኢትዮጵያውያን እራትና ኩራት በሆነችው ትንሿ ጤፍ ላይ ሙሉ ትኩረቷን በማድረግ የጤፍ ዱቄት ማምረት ሥራን ዛሬ ላይ ከትልቅ ቦታ ማድረስ ችላለች፡፡

ትንሿ ጤፍ እንጀራ ሆና ለምግብነት መቅረብ የምትችለው ብዙ ሂደቶችን አልፋ ሲሆን፤ ሂደቶቹም ቀላልና ዘመናዊ አይደሉም፡፡ ስለዚህ የጤፍ ዱቄትን በዘመናዊ መንገድ አዘጋጅቶ ማቅረብ አዋጭና ተመራጭ መሆኑን ሙና ትገነዛበለች፡፡ ይህ እውን ሲሆን ሴቶችን በብዙ መልኩ ያግዛል ያለችው ሙና፤ የጤፍ ዱቄት በፋብሪካ አዘጋጅታ ለማቅረብ ብዙ ጥረት አድርጋለች፡፡

ጤፍን እንጀራ ለማድረግና ከእርሻ ሥራው ባለፈ ማዕድ ላይ ለማቅረብ ከመግዛት ጀምሮ ማበጠሩ፣ መንፋቱ፣ ማስፈጨቱ፣ ማቡካቱና መጋገሩ የሴቷ ኃላፊነት ሆኖ መቆየቱን ጠቅሳ፣ የእሷ ውጥን የሴቷን ድካም ያቀላል የሚል ጽኑ ዕምነት ያድርባትናም ፋብሪካውን እውን አደረገችው። ጤፍን በቀላሉ ከመጠቀም ባለፈ የኢትዮጵያ ብቻ እንደመሆኑ በዓለም በአቀፍ ገበያ ጭምር እንዲታወቅና በተለያየ መንገድ ለመጠቀምም ከፍተኛ ጥረት እያደረገች ትገኛለች፡፡

«ጤፍ ለኢትዮጵያውያን የዕለት ተዕለት ምግብ እንደመሆኑ ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ በቀላሉ መዘጋጀት አለበት» የምትለው ሙና፤ ለዚህም በፋብሪካ ደረጃ መዘጋጀቱ ወሳኝ ነው ትላለች፡፡

እሷ እንዳለችው ሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍ በፋብሪካ ደረጃ ሲዘጋጅ አንድ ጊዜ ፋብሪካ ውስጥ ከገባ በኋላ ማንም አይነት የሰው ንክኪ አይደርስበትም፡፡ ፋብሪካው ከእጅ ንክኪ ነጻ በሆነ መንገድ ሂደቱን ጠብቆ ጤፉንና ሌሎች ባእድ ነገሮችን ይለያል፡፡ ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ መስመሮች ከማበጠር ጀምሮ በቅደም ተከተል እብቅና አፈር ድንጋዩን ለይቶ ጤፉን በጥራት ፈጭቶ ያሽጋል፡፡

እንደ ስንዴ ሁሉ ጤፍስ ለምን ማሽን ውስጥ አትገባም፤ ለምን በፋብሪካ ደረጃ አትዘጋጅም በማለት ወደ ሥራው የገባችው ሙና፤ የጤፍ መፍጫ ማሽኑን ዲዛይን በማድረግ ወደ ሥራ ለመግባት ብዙ ጊዜ እንደወሰደባትም ትገልጻለች። ፋብሪካው በጥሩ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ የማምረት አቅሙም በቀን 600 ኩንታል ያህል ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የሚመረተውን ጤፍ ከአርሶ አደር ሰብሳቢዎች ጋር ትስስር በመፍጠር እንደምታገኝ ያነሳችው ሙና፤ ጤፍ በሰፊ ማሳ ላይ የሚመረት ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ ምርቱን በሚፈለገው መጠን ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነም ገልጻለች፡፡

አርሶ አደሩ በትናንሽ ማሳዎች ላይ ጤፉን እንደሚያመርትና የግብርና ሥራውም በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ትናገራለች፡፡ እሷ እንዳለችው፤ እስካሁንም እንደ ስንዴና ሌሎች ምርቶች ሰፋፊ በሆነ የእርሻ መሬት ላይ ጤፍን ማልማት የቻለ የለም፡፡ ምክንያቱም የጤፍ ሥራ በጣም አድካሚና ሳርን ተከታትሎና ተንከባክቦ ለፍሬ እንደማብቃት ይቆጠራል ትላለች፡፡

«የጤፍ ሥራ እጅግ ከባድና አስቸጋሪ ነው» የምትለው ሙና፤ ከአመራረቱ ባለፈም እንደ ቡና ሁሉ ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ ሥራውን ከባድ እንዳደረገው ጠቁማለች፡፡ ለአብነትም አንደኛ ደረጃ ነጭ ጤፍ ተብሎ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚሰበሰበው ጤፍ፣ ጥራቱ የተለያየ ሆኖ እንደሚገኝ ገልጻ፣ ጤፍም እንደ ቡና አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ተብሎ ደረጃ ሊወጣለት ይገባል ባይ ናት፡፡ ይሁንና እስከዚያው ከተለያዩ ጤፍ አምራቾች ጤፉን እየገዛች በፋብሪካ ደረጃ በጥራት አዘጋጅታ እያቀረበች ትገኛለች፡፡

«ጤፍን ከእንጀራ ውጭ እሴት በመጨመር በተለያየ መንገድ በማዘጋጀት መጠቀም ስንችል ፋይዳውን በብዙ ከፍ ማድረግ ይቻላል» የምትለው ሙና፤ በአሁኑ ወቅት ጤፍ በዓለም ደረጃ ዋና ምግብ (ሱፐር ፉድ) ተብሎ ተፈላጊነቱ እየጨመረ ስለመምጣቱም ትናገራለች፡፡

እሷ እንዳለችው፤ ጤፍ በውስጡ የያዘው ንጥረ ነገር በርካታ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ በአሁኑ ወቅት መላው ዓለም የሚፈልገውና እያመረተው ያለም እንደሆነም ተናግራለች፡፡ «ስለዚህ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም በስፋት አምርቶ ከእንጀራ ውጭ በተለያየ መንገድ ለመጠቀም ብዙ ሥራ ይቀራል» በማለት ጤፍን ከሀገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ጭምር ከቡና ያልተናነሰ ገቢ ማምጣት እንደሚቻል ገልጻለች፡፡

እሷ እንዳለችው በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ብቻ ሆኖ የኖረው ጤፍ የመላው ዓለም እየሆነ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ብዙ ሊሠራበት ይገባል፡፡ አሁን ላይ ጤፍ በተለያዩ ሀገራት መመረት ጀምሯል፤ ምርትና ምርታማነቱን በማስፋት ዘመናዊ በሆነ መንገድ ማዘጋጀትና ከእንጀራ ውጭ በተለያየ አግባብ ዘመናዊ በሆነ መንገድ መጠቀም የግድ ይሆናል፡፡

ለዚህም ሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍ የራሱን ሚና ለመወጣት በሚያደርገው ጥረት ደረጃውን የጠበቀ ንጹህ የጤፍ ዱቄት በጥራትና በጥንቃቄ አዘጋጅቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሀገር ውስጥ ገበያ ከሚያቀርበው ባለፈ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ማቀዱንም ጠቁማለች፡፡

ሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍ በአሁኑ ወቅት በሀገር ውስጥ ገበያ በስፋት መግባቱን ገልጻ፣ በቀጣይም በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን አቅዳ እየሠራች መሆኑን ሙና አስታውቃለች፡፡ ሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የኢትዮጵያ በሆነው ጤፍ የኢትዮጵያን ስም ማስጠራት የግድ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥታ ተናግራለች። ለዚህም ፋብሪካው አስፈላጊዎቹን የጥራት ደረጃዎች በሙሉ ማለፍ መቻሉን ጠቅሳ፣ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ካላቸው አይኤስኦ 9001 እና ኤፍኤስሲ 22000 ድርጅቶ ዕውቅና አግኝቷል ብላለች፡፡

የገበያ ተደራሽነትን በሚመለከት ሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍ ከግለሰብ ጀምሮ ለሱፐርማርኬቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ሆቴሎችና ሌሎችም ተደራሽ እየሆነ ይገኛል፡፡ በተለይም ሥራ የሚውሉ እናቶችን ማሳረፍ የቻለ ስለመሆኑ ያነሳችው ሙና፤ ፋብሪካው መቶ በመቶ ጤፍ ብቻ የሚያመርት መሆኑን ገልጻለች፡፡ ይህንንም ስታብራራ ብዙዎች ዱቄቱን ምርጫቸው ያደረጉት «ፋብሪካው ውስጥ ጤፍ ብቻ ገብቶ ጤፍ ብቻ ስለሚወጣ ነው» ብላለች፡፡

ሙና እንዳለችው፤ በ2009 ዓ.ም ወደ ሥራ የገባው ሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍ በአሁኑ ወቅት 78 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል፤ በቀጣይም ማስፋፊያ በማድረግ ተጨማሪ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ይዟል፡ ፡ በቀጣይ ዕቅዱም ከጤፍ ዱቄት በተጨማሪ እሴት በመጨመር እንጀራ ወደ ማምረት ሥራ ይገባል። ለዚህም አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ በመሥራት ወደ ተግባር ሊሸጋገር ከጫፍ ደርሷል። ድርጅቱ ሌሎች በርካታ የሥራ እቅዶች ያሉት በመሆኑ በሥራ ዕድል ፈጠራ ረጅም ርቀት ይጓዛል፡፡

ሶርስ ወይም ቱሬ ጤፍ አሁን በተለያየ አይነትና መጠን ምርቱን ለገበያ እየቀረበ ነው፤ በአይነት ነጭና ቀይ ጤፍ በመጠን ደግሞ በ10 እና በ25 ኪሎ ግራም ያቀርባል።እነዚህም ቀይ ጤፍ ባለ 10 እና ባለ 25 ኪሎ ግራም እንዲሁም ነጭ ጤፍ ባለ 10 እና ባለ 25 ኪሎ ግራም መጠን ያላቸው ናቸው፡፡

ምርቱ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባሉት ሰባት ቅርንጫፎች አማካኝነት ከተማ ውስጥ ለሚገኙ የማህበረሰብ አካላት ተደራሽ መሆን ችሏል፡፡ ይሁንና በቀጣይ ከከተማ ውጭ ለሚገኙ የማህበረሰብ አካላት እና ለውጭ ገበያ የማድረስ ዕቅዱን ተግባራዊ ያደርጋል።

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ የተለያዩ ድጋፎችን እንደምታደርግ የገለጸችው ሙና፤ በተለይም ለሴቶች እንደምታደላ ነው የገለጸችው፡፡ ይህም ሲባል የሥራ ዕድል ቅድሚያ ለሴቶች ከመስጠት ጀምሮ ሴቶችን ማብቃትና ከታችኛው የሥራ ክፍል ከፍ ወዳለው የሥራ ክፍል ታሳድጋለች፡፡

ለሠራተኞቿ ጋር ያላት መልካም አቀራረብም ጠንካራ የሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነት የፈጠረላት መሆኑን ጠቅሳ፣ ድርጅቱ ሲቋቋም ጀምሮ የተቀጠሩ ሠራተኞች ዛሬም ድረስ አብረዋት እንዳሉ ተናግራለች፡፡ ይህም በመልካም ግንኙነት የተገኘ ስኬት በመሆኑ አብረውኝ አድገዋል ትላለች፡፡ ሠራተኞች ምግብ በነጻ እንደምታቀርብም ገልጻለች፡፡

ሀገራዊ ለሆኑ ማንኛውም ጥሪዎች በአቅሟ ምላሽ የምትሰጠው ሙና፤ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ጤፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ የማስተዋወቅ ትልቅ ህልም እንዳላትም ተናግራለች፡፡

# ተናጋሪው ዶሴ

## ቂመኛው

አስመረት ብስራት



ትዳር ሀ ተብሎ የተጀመረ ሰሞን ሙቀቱ የኤርታሌን ወላፈን ያስንቃል። የሕይወቴ ሕይወት አንቺ በመሆንሽ፣ ብለው የጀመሩት ትዳር ቀናት በሄዱ ቁጥር ሲቀዘቅዝ ማየት በአብዛኛው የተለመደ ነው፡፡ እንደ ቅዝቃዜው ልቆ ሙቀቱ የጠፋ ጊዜ 'ዓይንሽን ላፈር'፣ 'ዓይንህን ላፈር' ተባብሎ መለያየት የተለመደ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። ትዳር ዓለም አቀፋዊ እውነት እንደሆነ ሁሉ፣ ፍችም እንዲሁ አይቀሬ እጣ ይመስላል።

የሶስት ጉልቻው መሠረት የተናጋበት ትዳር፣ ቋንቋቸው የተደበላለቀባቸው ጥንዶች፣ ጉንጫቸውን ልሳምሽ ሳይሆን ለንክሻ የሚፈላለጉ ባልና ሚስቶች እዚህም እዚያም መኖራቸው ደግሞ ምነው ይሄን ያህል ሳያሰኝ አይቀርም።

ኢትዮጵያ ለትዳር ትልቅ ስፍራ ከሚሰጡ ሀገራት መካከል አንዷ ብትሆንም በተለያዩ ምክንያቶች በእልልታ የተጀመሩ ትዳሮች በፍቺ የመደመደም ሁኔታቸው የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ሰነባብቷል።

የአዲስ አበባ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ በ2014 በጀት ዓመት ከ14 ሺህ በላይ ጋብቻ፣አንድ ሺህ 623 የፍቺ ምዝገባዎችን ማከናወኑን አሳውቆ ነበር። ይህንን ቁጥር በ2010 ዓ.ም ብናየው ደግሞ በ2010 አንድ ሺ 923 የሚሆኑ ጥንዶች ፍቺ መፈጸማቸውን የአዲስ አበባ ወሰኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ መረጃ ያሳያል።

ታዲያ የዚህ በአሳሳቢ ደረጃ ቁጥሩ እየሻቀበ ነው የተባለለት ፍቺ መንስኤ የሌሎች ጣልቃ ገብነት መሆኑን ይህ መረጃ ያመለክታል። ስለ ፊቺ አሳሳቢነት ያነሳነው በዛሬው ተነጋሪው ዶሴ ዓምዳችን በትዳሬ ጣልቃ ገብታ ከባለቤቴ ጋር አለያይታኛለች በሚል ቂም በቀል የተፈፀመ ወንጀል ታሪክን ልናካፍላችሁ ስለሆነ ነው። መልካም ቆይታ።

### ጥንዶቹ

"ሳየው ልቤ ደነገጠ" "ሳያት ልቤ ትርክክ አለብኝ" ተባብለው ነበር የተጋቡት። ፍቅራቸው ንፋስ የሚገባው አይመስልም ነበር። "ፍቅርና ገንፎ ትኩስ ትኩሱን ነው" ያሉት ጥንዶች የፍቅራቸው ግለት ሳይበርድ ወደ ቁም ነገር አሸጋግረው ሶሰት ጉልቻ መሰረቱ። የቁልምጫ አጠራራቸው እንኳን እርስ በእርሳቸው የሰሚያቸውንም ልብ ያቀልጣሉ።

እንዲህ እንዲህ እያሉ የጫጉላ ጊዜያቸው አልቆ ሁሉም ወደ እንጀራ ፍለጋው ሲሯሯጥ ነገር ቀስ እያለ ብቅ ማለት ጀመረ። በፍቅር ተሸሽገው የቆዩ አመሎች ከየጎሪያቸው ብቅ አሉ። በውሀ ቀጠነ ፀብ ነገሰ። ከፀብ በኋላ እርቅ፤ እንደገና ከእርቅ በኋላ ፀብ እየደጋገመ እየደጋገመ የቤታቸውን ደጃፍ አንኳኳ።

በዚህ መካከል ብርቱካን አበራ የተባለች የሙሽሪት ጓደኛ ቤታቸው እየመጣች ለማስማመት ሙከራ ታደርግ ነበር። እንዲታረቁ እየመከረች ካስማማች በኋላ ጓደኛዋን ለብቻዋ እስቀምጣ ትመክራት ነበር። ባል ሚስቱን ለብቻዋ ምን እንደምትነግራት ባለመረዳቱ ሁልጊዜ ይናደዳል።

አልፎ ተርፎ እቤታቸው እንዳትመጣ እስከ መከልከል ደረሰ። ቀናት ቀናትን እየተኩ በመጡ ቁጥር የፍቅራቸው ሁኔታ መሻሻልን ከማሳየት ይልቅ ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ መጣ። ቋንቋቸው ተደበላልቆ ቢነጋገሩም የማይግባቡበት ደረጃ ደረሱ። ተነጋግረው ችግሮቻቸውን ለመፍታት ቢሞክሩም በእልኸኝነትና በቁጣ ሰላማዊ ንግግር ሳያደርጉ ትትውት ይነሱ ነበር።

### አቶ ባል

አገኘሁ ገድይሁን አጋሉ ይባላል። እንደዛ እሷን ካጣሁ ሞቴ ዛሬ ይሁን ብሎ ካገባት ሴት ጋር ለምን መግባባት እንዳቃተው እንቆቅልሽ ሆኖበታል። ውስጡን ሲያዳምጥ አሁንም ይወዳታል። ደግሞ በአንድ በኩል ነገረ ሥራዋ ሁሉ አልጥም እያለው ይቸገራል። የሚወዳት ሚስቱን በፍቅር አቀፎ አብሯት ሊያመሽ አስቦ ቤቱ ገብቶ በኩርፊያ ጀርባ የመሰጣታቸው ነገር አልዋጥልህ ብሎታል።

ለአጭር ጊዜም ቢሆን ሰማይ ሰማያትን አልፎ በገነት በር ላይ ወከ ያደረገ እስኪመስለው ድረስ በደስታ የተንሳፈፈበትን ፍቅር የማሳለፋቸውን ነገር ትዝ እያለው ምን ነከቶን ነው እያለ ብቻውን ይብሰከሰካል። ለደግ ያለው ሁሉ ለክፉ እየሆነበት፤ እሷን ያስደስታል ብሎ የሞከረው ነገር በሙሉ እሷን አስከፍቶ ፀብ የሚፈጠር ጉዳይ የሆነበትን ውትብትብ ለመፈታተ ቢሞክር ውሉ አልጨበጥ እያለው አስቸግሮታል።

ከብዙ ከራስ ጋር ምክክር በኋላ የጓደኛዋ ብርቱካን ሴራ መሆኑን ድምዳሜ ላይ ይደርሳል። በፍቅራቸው መካከል እየገባች የምትበጠብጣቸው ብርቱካን እንደሆነች በማመን ከባለቤቷ እንደትርቅ ያደርጋታል። ብርቱካንም ካልተፈለኩማ በማለት እግሯን ትሰብስባለች። ይህ ጉዳይ ግን ሙሽሪትን ያስደሰታት ጉዳይ አልነበረም።

### ብርቱካን አበራ

የሙሽሪት ጓደኛ የሆነችው ብርቱካን ጓደኛዋ የምትወደውን ሰው አግኝታ ትዳር መያዟ እጅግ በጣም ካስደሰታቸው የሙሽሪት ጓደኞች መካከል አንዷ ናት። ጓደኛዋ ቁም ነገር አስባ ሶስት ጉልቻ ስትመሰረት ከደገፉት መካከል ግንባር ቀደሚም እሷው ነበረች። በሞቀው የሙሽርነት ጊዜ እንደ ጓደኛ አንደኛ ሚዜ ሆና ቤቷን ሲቀና የሙሽሪት ደጋፊ ረዳት ሆናላት ነበር።

በግጭታቸውም ቋሚ ተጠሪ በመሆን ለማስማማት የበኩሉን ጥረት ስታደርግ ቆይታለች። ተቆጥታ ካስማማቻቸው በኋላ ጓደኛዋ በትእግስት ነገሮችን ማለፍ ለትዳር ዋና ቁልፍ ነገር መሆኑን ለብቻዋ ተመክራታለች። ነጋ ጠባ ፀብና ጭቅጭቅ ፍቅር የሚያቀዘቀዝና ቤት የሚያፈርስ ጉዳይ መሆኑን እየነገረች ወዳና ፈቅዳ የገባችበትን ትዳር እንድትጠብቅ ጓደኛዋን ዘወትር ትመክራት ጀመር።

ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ሆነና ነገሩ ብርቱካን ለበጎ ብላ ያስበችው ነገር በሙሉ አባወራውን እያስቀየመው፤ ከጓደኛዋ ቤት ያለ ፍላጎት እንድትቀር አደረጋት።

ሙሽሪትም ወትሮም ፀብና ጭቅጭቅ አሰላችቷት ትዳሯን ልትተው ጫፍ ደርሳ በነበረበት ወቅት የጓደኛዋ ቤት አለመምጣት ያናድዳታል። እሷ እዚህ ቤት የማትመጣ ከሆነ እኔ እወጣለሁ ብላ ጓዟን ሸክፋ ትዳሯን ትታ ከቤት ትወጣለች።

ይህ ጉዳይ የከነከነው ባል ቤቴን ትዳሬን እንዳጣ ምክንያት የሆነችው ጓደኛዋ ብርቱካን ናት በማለት ቂም ይዞ ለማጥቃተ ይፈልጋት ጀመር።

### አሰቃቂው ማታ

በ8/10/2015 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 3፡30 ነበር። በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ጎሮ አፍሪካ ክሊኒክ በመባል በሚጠራው አካባቢ አድብቶ እየተጠባበቃት ነበር። ከባለቤቴ ጋር አለያይታኛለች በሚል ቂም ቋጥሮ ብርቱካን ከርቀት ወደ ቤትዋ አቅጣጫ ስትሄድ ተመለከታት። በአካባቢው ሙብራት አለመኖሩንና ጭር ማለቱን ወዶታል። ብርቱካን ሀገር ሰላም ብላ ቤትዋ ስትሄድ ዛፍ ስር ተደብቆ ጫፉ ስለት ያለው ፌሮ ብረት ይዞ ይጠባበቃት ጀመር።

ልክ አጠገቡ ስትደርስ ጫፉ ስለት ባለው ፌሮ ብረት የተለያየ የሰውነት አካልዋ ላይ በመውጋት ይጥላታል። መውደቋን አየቶ እንደመሸሽ ፈንታ ደጋግሞ በወደቀችበት ሕይወትዋ እስኪያልፍ ድረስ ደጋግሞ ይወጋታል። በዚህ ድርጊቱም ብርቱካን ዳግም ላትነሳ በወደቀችበት ትቀራለች።

ልክ መሞቷን ሲያረጋግጥ በወደቀችበት ጥሏት ለማምለጥ ሙከራ ለማድረግ ሲሞክር በአጋጣሚ በአካባቢው ሲያልፉ የነበሩ ሰዎች ሰውዬው በጭካኔ እያደረገ የነበረውን ተግባር በመመልከት ሰፈሩን በጩኸት ያደባልቁታል፡፡ የሰራውን ሰርቶ እግሬ አውጪኝ ሲል የነበረው ጥፋተኛ የጩኸት ድምፅ ሰምተው ሲሮጡ ከነበሩ ፖሊሶች ጋር ፊት ለፊት ይገጣጠማል።

ፖሊሶቹም የሮጠበትን ምክንያት ባያወቁም እንዳያመልጥ በማሰብ ይዘው ጩኸት ወደሰሙበት አካባቢ ይደርሳሉ። በአካባቢውም መሬት ላይ የወደቀ የሴት አስከሬን በድንጋጤ የሚጮሁ ሁለት ሰዎችን በመመልከታቸው ተጨማሪ ኃይል ይጠራሉ።

አምቡላንስ ጠርተው አስከሬኑን ካሰነሱ በኋላ የዓይን ምስክሮችንም ሆነ ወንጀለኛውን በመያዝ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ ቃላቸውን ተቀበሉ።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ የዓይን እማኞችን ቃል ከተቀበለ በኋላ በሰላም ወደቤታቸው ያደርሳቸዋል፡፡ የአስክሬን ምርመራ ውጤትም እጁ እንደገባለት የተከሳሽን የእምነት ክህደት ቃል ይቀበላል። መጀመሪያ ላይ ወንጀሉን እንዳልፈፀመ ለመካድ ቢሞክርም እየቆየ ግን ምርመራው መጠናከሩን ሲረዳ "ከባለቤቴ ጋር እንድንለያይ ትመክራት ነበር" በማለት ወንጀል መፈፀሙን ያምናል።

ይህ ሰው ሆን ብሎ በቂም በቀል ተነሳስቶ የሰው ሕይወት እንዲያልፍ በማድረጉ ምክንያት በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በመላክ ክስ እንዲመሰረትበት ያደርጋል።

### የዓቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር

ወንጀሉ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዓቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በወ/ህ/አ 539/1/ሀ መሠረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ የሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ክስ ቀረበበት።

የዓቃቤ ሕግ ክስ ዝርዝር እንደሚያመለክተው አገኘሁ ገድይሁን አጋሉ የተባለ ተከሳሽ በ8/10/2015 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 3፡30 ሲሆን በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ጎሮ አፍሪካ ክሊኒክ በመባል በሚጠራው አካባቢ ከባለቤቴ ጋር አለያይታኛለች በሚል ሟች ብርቱካን አበራ ወደ ቤትዋ ስትሄድ ዛፍ ስር ተደብቆ ጫፉ ስለት ባለው ፌሮ ብረት የተለያየ የሰውነት አካልዋ ላይ በመውጋት ሕይወትዋ እንዲያልፍ በማድረጉ ምክንያት በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዓቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በወ/ህ/አ 539/1/ሀ መሠረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ የሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቦበት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል፡፡

### ውሳኔ

በክርክሩ ሂደትም የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ሶስት የመከላከያ ምስክሮች በማቅረብ ያሰማ ቢሆንም የቀረበበትን ክስ ሊከላከል ባለመቻሉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ የሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ባስቻለው ችሎት በተከሳሽ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠት ተከሳሽ በ19 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኖበታል፡፡

# የትምህርት ቤቶችና የንግድ ቤቶች ጉዳይ

**ኤልያስ ከቢሾፍቱ**

ሰሞኑን የዓመቱ የትምህርት ሥራ በመላው ኢትዮጵያ ተጀምሯል፡፡ በመላው ኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ተቀብለው ማስተናገድም ጀምረዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ከሁለት ዓመት በፊት በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚከናወኑ አዋኪ ድርጊቶችን በመከላከል በሥነ-ምግባር የታነጸ ትውልድ ለማፍራት በትኩረት እንደሚሠራ አሳውቋል፡፡ በዚህም በቂ ነው ባይባልም ተጨባጭ ለውጦችም ታይተዋል፡፡ ይህ የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ መግለጫ በመላው ኢትዮጵያ በሚገኙ ከተሞች ውስጥ ባሉ ትምህርት ቤቶች ግን አሁንም አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ይገኛል፡፡

የትምህርት ቤቶች አካባቢ ፀጥታ አንገብጋቢ ከሆነው የትምህርት ጥራት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ በመሆኑ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም በከተሞች አካባቢ ይህ ሁኔታ በጣም አሳሳቢ ነው፡፡ እንዴት ተደርጎ ወደ ተግባር ሊቀየር እንደሚችልም ለማወቅ ከባድ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ትምህርት ቤቶች ከሁከት የፀዱ መሆን አለባቸው የሚለው ጉዳይ አከራካሪ አይደለም። ዛሬም ድረስ በከተሞች በትምህርት ቤት ዙሪያ ከትምህርት ሥራው ጋር የሚቃረን ሌላ በርከት ያለ የንግድ ተቋም ይፈለፈላል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በትምህርት ቤቱ ፊት ለፊት ባር፣ ከጀርባው ሺሻ ቤት፣ ከጎኑ ጭፈራ ቤት፣ ከፍ ብሎ ጫት ቤት፣ እልፍ ብሎ ማሳጅ ቤት፣ ከዛ ደግሞ ፔኒስዮን ወዘተ እያለ ይቀጥላል፡፡ እነዚህ የንግድ ተቋማት ተማሪዎችን ወደ ደንበኝነት ከመሳብ አንስቶ ለሌሎች ሱሶች (ሲጋራ፣ ጫት፣ ሺሻ) እስከማለማመድ ብሎም ሴት ተማሪዎችን ለወሲብ ንግድ እስከ መመልመል የሚደርሱ ናቸው፡፡ ለእነሱ ትምህርት ቤቱ የገበያ ምንጭ ነው፡፡ ለትምህርት ቤቱና በአጠቃላይ በመማር ማስተማሩ ሂደት ግን እነዚህ የንግድ ቤቶች አደጋዎች ናቸው፡፡

እስኪ በዓይነ ልቡናችን የምናውቃቸውን ትምህርት ቤቶች እናስታውስ፡፡ በርካታ ትምህርት ቤቶች በዙሪያቸው ከ10 የሚበልጥ መጠጥ ቤት 500 ሜትር በማይሞላ ርቀት ውስጥ ይዘው ልናስታውስ እንችላለን፡፡ ተማሪው እነዚህን መጠጥ ቤቶች፣ የሚከፍቱትን ሙዚቃ፣ የሚያወጡትን ጠረን እና ሌሎችም ሳቢ ሁኔታዎች ተቋቁሞ ነው ወደ ትምህርት ገበታው የሚገባው፡፡ ይህን ስበት መቋቋም የሚችሉ ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን ብዙው ተማሪ ወጣት ነውና ከእድሜም ከብስለት ማነስም ሰንብቶም ቢሆን በዚህ ወጥመድ ውስጥ መግባቱ አይቀርም፡፡ ለዚህ ብዙ ምሳሌዎችን እና ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡

እንዲያው ብዙ ርቀት ሳንሄድ ከጥቂት ዓመት በፊት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለወጣት ጥፋተኞች ማረሚያ የሚሆን አዲስ ዘመናዊ ተቋም ማዘጋጀቱ ችግሩ ምን ያህል እንደደረሰ አመላካች ነው፡፡ ተቋሙ የተስፋፋበት ዋነኛ ምክንያት እድሜያቸው 18 ዓመት ሳይሞላ ከባድ ወንጀል ውስጥ ተሳትፈው የሚገኙ ወጣቶችን ለማረም ተብሎ ነው፡፡ አብዛኞቹ ወጣቶች ወደዚህ የገቡበት አንደኛው ምክንያት ትምህርት ቤት ብለው በወጡበት ወቅት የለመዱት ሱስ ገፊ ምክንያት ሆኖባቸው ነው፡፡ ስለዚህም በነዚህ ልጆች ወንጀል ላይ በትምህርት ቤቶቻቸው ዙሪያ ያሉ መጠጥ ቤቶች፣ ጫት ቤቶች፣ ሺሻ ቤቶች እና ሌሎች ድርሻ አላቸው ማለት ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ ዛሬ ላይ በተለያዩ የግል፣ የመንግሥት እና የሃይማኖት ተቋማት በወጣቶች ላይ የሚሠራው ሥራ መነሻ ምክንያቱ ወጣቶች በሱስ እየተጠለፉ እንደሆነ መታየቱ ነው፡፡

በአንድ ወቅት በአንድ የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚሠራ የተማሪ ማማከር ባለሙያን ባናገርኩበት ወቅት የተረዳሁት እውነታውም እነዚህ በትምህርት ቤት ዙሪያ ያሉ አዋኪ ተቋማት ቁጥራቸው እየጨመረ እና በተማሪዎች ላይ ያላቸው ተፅዕኖም እያየለ እንደመጣ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ትምህርት ቤት ብለው ወጥተው ሺሻ እና ጫት ቤት የሚውሉት ተማሪዎች ቁጥር እየበረከተ እንደመጣ፣ ብዙ ተማሪዎች እዚያው ትምህርት ቤት በር ላይ የትምህርት ቤት የደንብ ልብሳቸውን እንደሚቀይሩ እና ወደነዚህ ቦታዎች እንደሚገቡ፣ ብዙ ተማሪዎች በተላመዱት ሱስ የተነሳ ክፍል ውስጥ ተረጋግተው ትምህርት መስማት እንደማይችሉ እና ብዙ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ መፀዳጃ ክፍል ሲጋራ እና ሌሎች አደንዛዥ እፆችን ሲጠቀሙ እንደሚያዙ፣ በሚያሳዩት ባሕሪ የተነሳ ከመምህራኖቻቸው ጋር እስከ ድብድብ የደረሰ ጠብ ውስጥ የገቡ ተማሪዎች መኖራቸውን፣ አንዳንድ ተማሪዎችም በሱስ የተነሳ ትምህርት እስከ ማቋረጥ ብሎም ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ እስከመሆን እንደደረሱ ወዘተ ነግሮኝ ነበር።

በእርግጥም እነዚህ በትምህርት ቤቶች ዙሪያ ያሉ አዋኪ ተቋማት በተማሪዎች ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም፡፡ ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች መካከል የተወሰኑትን ብንጠቅስ አንደኛው በተማሪዎች ላይ የውጤት ማሽቆልቆል፣ ከትምህርት ቤት መቅረትና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ አለመሆን እንዲሁም ትምህርት ማቋረጥ በሱስ ውስጥ ያሉ ወጣቶች የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ናቸው፡፡ ሁለተኛው ጉዳት የአካላዊ ጤና መዛባት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በከተሞች አካባቢ የሚታዩት አደጋዎች ለምሳሌ ያህል የመኪና አደጋ እንዲሁም እንደ ኤች አይ ቪ ኤድስ ያሉ ተላላፊ በሽታዎች በወጣቶች ላይ የሚከሰቱት በሱስና አደንዛዥ ዕፅ ምክንያት የሚከሰቱ የጤና እክሎች ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ በሱስ የተጠመዱ ወጣቶች ከሱስ ነፃ ከሆኑ ወጣቶች ጋር ሲነጻጸሩ ለተለያዩ የአዕምሮ በሽታዎች የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ድብት፣ አስቸጋሪ ጠባይ፣ የስብዕና መቃወስ፣ እራስን ለማጥፋት ማሰብና መሞከር እንዲሁም ማጥፋት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ጉዳቱን በማኅበራዊ መልኩ ስናየው ደግሞ ወጣቶቹ የሚያገኙትን ገንዘብ ሁሉ ሱሳቸውን ለማስታገስ የሚጠቀሙበት ሲሆን ያን ማድረግ ካልቻሉ ደግሞ ወደ ወንጀል ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልን በትምህርት ቤት ዙሪያ ያሉ መጠጥ ቤቶች ልጆችን ለምን አይነት ችግር እንደሚጋብዙ መዘርዘር እንችላለን፡፡

ስለዚህም ዘላቂው መፍትሔ በትምህርት ቤት ዙሪያ ያሉ አዋኪ ተቋማትን ማፅዳት መሆን አለበት፡፡ ከዚህም ባለፈ ግን በዚህ ዙሪያ ለተማሪም ለወላጅም ለሌላውም ግንዛቤ መፍጠር እና በጋራ እንዲሠሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አዋኪ ነገሮችን የማፅዳት ሥራው የሌሎችን ሰርቶ የመኖር መብት የማይጋፋ እንዳይሆን፣ እንቅስቃሴውም ትምህርት ቤትን ብቻ ሳይሆን መኖሪያ አካባቢዎችን ያማከለ እንዲሆን ማድረግ ስለሚስፈልግ ሥራው በሕግ የተቃኘ፣ በስትራቴጂ የሚመራ እና ዘለቄታ ያለው ሆኖ መሥራትም አለበት፡፡

## ዓለም አቀፍ

# እሥራኤል ሊባኖስ የሚገኙ 100 የሄዝቦላህ የሮኬት ማስወንጨፊያዎች ማውደሟን አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እሥራኤል ሊባኖስ የሚገኙ 100 የሄዝቦላህ የሮኬት ማስወንጨፊያዎች እና ሌሎች "የሽብር ቦታዎች" እንዲሁም የመሣሪያ ማከማቻዎችን መምታቷን አስታወቀች።

የእሥራኤል መከላከያ ኃይል እንዳለው ወደ እሥራኤል ለመላክ ዝግጅት ላይ የነበሩ ማስወንጨፊያዎች ናቸው የወደሙት። እስካሁን በጥቃቱ የሞተ ሰው ስለመኖሩ አልተዘገበም።

በመንግሥት የሚተዳደረው የሊባኖሱ ናሽናል ኒውስ ኤጀንሲ ሐሙስ አመሻሹን እስራኤል በደቡባዊ ሊባኖስ 52 የአየር ጥቃቶች ማድረጓን አስታውቆ ሊባኖስ ደግሞ ሰሜን እሥራኤል የሚገኙ ወታደራዊ ቦታዎችን መትታለች ብሏል።

የሄዝቦላህ መሪ ሐሰን ናስራላህ በያዝነው ሳምንት በሀገሪቱ በተለያዩ ሥፍራዎች የደረሱ ፍንዳታዎችን ተከትሎ ጥቃቶቹ "ቀይ መስመር ጥሰዋል" በማለት እሥራኤል ጦርነት ማወጇን ተናግረዋል።

እሥራኤል ከሰሞኑ በጥቃቅን የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ሊባኖስ ውስጥ ለደረሱት ጥቃቶች ኃላፊነት አልወሰደችም።

ማክሰኞ እና ረቡዕ በደረሱት ጥቃቶች 'ፔጀሮች' እና 'ዎኪ ቶኪዎች' በተመሳሳይ ሰዓት ፈንድተው 37 ሰዎች ሲሞቱ 3 ሺህ ገደማ ደግሞ መቁሰላቸውን የሊባኖስ ባለሥልጣናት አስታውቀዋል።



የእሥራኤሉ መከላከያ ሚኒስትር ዮዋቭ ጋላንት ሀገራቸው በተለይ በሰሜኑ ክፍል በማተኮር "አዲስ የጦርነት ሂደት" መጀመሯን ተናግረዋል።

የሐማስ ታጣቂዎች በአውሮፓውያኑ ጥቅምት 7፣ 2023 በእሥራኤል ላይ ጥቃት ባደረሱ በማግስቱ ነው ሄዝቦላህ እና እሥራኤል ድንበር አካባቢ የተኩስ ልውውጥ ያደረጉት።

ከዚህ በኋላ በተደረጉ የተለያዩ የተኩስ ልውውጦች በመቶዎች የሚቆጠሩ የሄዝቦላህ ታጣቂዎች ሲገደሉ ድንበር አካባቢ የሚገኙ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሊባኖሳውያንና እሥራኤላውያን መኖሪያቸውን ጥለው ለመሸሽ ተገደዋል።

ሄዝቦላህ ጥቃቱን የሚፈፅመው ለፍልስጤሙ ታጣቂ ቡድን ሐማስ ያለውን አጋርነት ለማሳየት እንደሆነ ይገልፃል። በእሥራኤል፣ ዩኬ እና ሌሎች ሀገራት ሽብርተኛ ተብለው የተፈረጁት ሁለቱ ታጣቂ ቡድኖች በኢራን ይደገፋሉ።

ሐሙስ አመሻሹን መግለጫ ያወጣው የእሥራኤል መከላከያ ኃይል የጦር አውሮፕላኖቹ "100 ገደማ ማስወንጨፊያዎችን እና ሌሎች የሽብር መሠረተ ልማቶችን ጨምሮ የተለያዩ ቁሳቁሶችን አውድሟል" ይላል።

ሮይተርስ የዜና ወኪል እና ኒው ዮርክ ታይምስ የሊባኖስ ፀጥታ ኃይሎችን ዋቢ አድርገው እንደዘገቡት እስራኤል ሐሙስ ዕለት የፈፀመችው ጥቃት ከጋዛው ጦርነት በኋላ እጅግ ከባዱ ነው።

ሐሙስ ንጋት ደቡባዊ ሊባኖስ የሚገኙ የሄዝቦላህ ተዋጊዎች ሁለት ፀረ-ታንክ ሚሳዔሎችን እና ድሮኖችን ወደ ድንበር ተኩሰዋል።

የእስራል መከላከያ ኃይል ሁለት እሥራኤላውያን መገደላቸውን እንዲሁም አንድ ወታደር ክፉኛ መቁሰሉን አስታውቋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# የስኬት አስተሳሰብ

አስናቀ ፀጋዬ

ስኬትን እንዴት እንገልፃለን? በሕይወት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን ብዙ የተለያዩ ስልቶች አሉ። ነገር ግን ለእርስዎ በጣም የሚስማማው ስልት በስኬት እይታዎ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል። አብዛኛዎቻችን በሥራ ላይ ጥሩ መሥራት ወይም ከፍተኛ ደመወዝ እንደምናገኝ እናስባለን። ሆኖም ይህ ብቻውን ስኬት አይደለም፡፡

ስኬት ምን ማለት እንደሆነ ለመገለጽ ከተፈለገ እንደየግለሰቦች አተያይና አመለካከት ይለያያል፡፡ ስኬታማ ለመሆን ወጥና ትክክለኛ መንገድ የለም። ለእርስዎ የሚስማማው ለሌላ ሰው ላይሰራ ይችላል። ስኬትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ፍጹም የተዋሃዱ ንጥረ ነገሮች ጥምረት ላይኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን በሕይወትዎ፣ በፍቅርዎ፣ በሥራዎ ወይም ለእርስዎ አስፈላጊ በሚሆንበት ማንኛውም ነገር ውስጥ ስኬታማ የመሆን እድሎችን ሊያሻሽሉ የሚችሉ አንዳንድ መሠረታዊ ደረጃዎች አሉ።

### 1ኛ. የእድገት አስተሳሰብ ይገንቡ / Build a Growth Mindset/

የሥነ ልቦና ባለሙያ ካሮል ድዌክ ምርምር እንደሚያመለክተው ሰዎች ስለራሳቸው እና ስለ ችሎታቸው እንዴት እንደሚያስቡ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁለት መሠረታዊ አዕምሮዎች እንዳሉ ይገልፃል፡፡ እነዚህም ቋሚ አስተሳሰብ እና የእድገት አስተሳሰብ ናቸው ይላል፡፡

ቋሚ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች እንደ የማሰብ ችሎታ ያሉ ነገሮች የማይንቀሳቀሱ እና የማይለወጡ እንደሆኑ ያምናሉ። ቋሚ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ደግሞ ስኬት በጠንካራ ሥራ ውጤት አይደለም ብለው ያምናሉ፡፡ ይህ የተፈጥሮ ተሰጥኦ ውጤት ነው፡፡

ምክንያቱም እንዲህ ያሉ ተሰጥኦዎችን ሰዎች የተወለዱበት ወይም ያለተወለዱበት ነገር ነው ብለው ስለሚያምኑ ፈታኝ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው በቀላሉ የመተው አዝማሚያ ስለሚያሳዩ ነው። የላቀ ለመሆን የሚያስፈልገው ክህሎት ስለሚጎድላቸው በሥራ ገበታቸው ላይ አይገኙም ሥራቸውንም ሊያቋርጡ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል የእድገት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች በጥረት መለወጥ ፣ ማደግ እና መማር እንደሚችሉ ይሰማቸዋል። የማደግ ችሎታ አለን ብለው የሚያምኑ ሰዎች ስኬታማ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ ነው። ነገሮች ሲከብዱ፣ ክህሎቶቻቸውን ለማሻሻል እና ለስኬት መሥራታቸውን የሚቀጥሉበትን መንገዶች ይፈልጋሉ። ሕይወታቸውን መቆጣጠር እንዳለባቸው ያምናሉ፡፡ በተቃራኒው ቋሚ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ነገሮች ከቁጥጥራቸው ውጭ እንደሆኑ ይሰማቸዋል፡፡

ስለዚህ የእድገት አስተሳሰብን ለመገንባት ጥረቶችዎ አስፈላጊ እንደሆኑ ይመኑ፡፡ የእድገት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ችሎታቸው ተስተካክሏል ብለው ከማሰብ ይልቅ ጥረት እና ጠንክሮ መሥራት ትርጉም ያለው እድገት ሊያመጣ እንደሚችል ይወቁ፡፡ አዳዲስ ክህሎቶችን ይማሩ። ፈታኝ ሁኔታ ሲያጋጥምዎ ፈተናውን ለመወጣት የሚያስፈልግዎን ዕውቀት እና ክህሎት ለማዳበር መንገዶችን ይፈልጉ፡፡

ውድቀቶችዎን እንደ መማሪያና ልምድ መቅሰሚያ ይመልከቷቸው። ምክንያቱም የእድገት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ውድቀት የችሎታቸው ነፀብራቅ ነው ብለው አያምኑም። ይልቁንም እነሱ ውድቀትን ለመማሪያና ለማሻሻያ ጠቃሚ የልምድ ምንጭ አድርገው ይመለከቱታልና።

### 2ኛ. ስሜታዊ የማሰብ ችሎታዎን ያሻሽሉ /Improve Your Emotional Intelligence/

አጠቃላይ የማሰብ ችሎታ በተለያዩ የሕይወት ዘርፎች ውስጥ ለስኬት አስተዋጽኦ የሚያደርግ



አንድ ምክንያት እንደሆነ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ይታመን ነበር፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ባለሙያዎች የስሜታዊነት ብልህነት የበለጠ አስፈላጊ ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ። ስሜታዊ ብልህነት በስሜቶች የመረዳትን፣ የመጠቀምን እና የማመዛዘን ችሎታን ያመለክታል። በስሜታቸው ብልህ የሆኑ ሰዎች የራሳቸውን ስሜቶች ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም መረዳት ይችላሉ።

ስለዚህ እርስዎም ስሜታዊ የማሰብ ችሎታዎን ለማሻሻል ለራስዎ ስሜቶች ትኩረት ይስጡ። የሚሰማዎትን እና እነዚያን ስሜቶች የሚያመጣውን ለመለየት ይሞክሩ፡፡ ስሜትዎን ይቆጣጠሩ። ወደ ኋላ ይመለሱ እና ነገሮችን በገለልተኛ ዓይን ለማየት ይሞክሩ። ስሜትዎን ከመጨፍለቅ ወይም ከመጨቆን ይቆጠቡ። የሚሰማዎትን ስሜት ለመቋቋም ጤናማ እና ተገቢ መንገዶችን ይፈልጉ፤ሌሎችንም ያዳምጡ።

### 3ኛ. የአዕምሮ ጥንካሬን ማዳበር /Develop Mental Toughness/

የአዕምሮ ጥንካሬ ያላቸው ሰዎች ተግዳሮቶችን እንደ ዕድሎች ይመለከታሉ። በተጨማሪም የራሳቸውን ዕጣ ፈንታ የመቆ ጣጠር፣ በስኬት ችሎታቸው የሚተማመኑ፣ የጀመሩትን ለመጨረስ ቁርጠኛ እንደሆኑ ይሰማቸዋል። እርስዎም የአእምሮ ጥንካሬዎን ለማሻሻል እና በሕይወት ውስጥ ስኬታማ የመሆን እድሎችን ለመጨመር በራስዎ ይተማመኑ፡፡ አሉታዊ የራስ-ንግግርን ይቁረጡና አዎንታዊና ራስዎን የሚያበረታቱበትን መንገዶች ይፈልጉ።

ይህን ሙከራዎን አያቋርጡ፡፡ ነገሮች የማይቻሉ ከመሰለዎ ወይም መሰናክሎች እርስዎን ወደኋላ ከያዘዎት ችሎታዎን ማዳበር እና ወደፊት መጓዝ በሚችሉባቸው ላይ ያተኩሩ። ከተሳካላቸው ሰዎች ቁልፍ ልምዶች አንዱ ሁልጊዜ መሰናክሎችን ወይም ውድቀቶችን እንደ የመማር ዕድሎች መመልከት ነው። አላማ ይኑርዎ፡፡ ነገሮችን ለብቻ ማድረግ ከባድ ሊሆን ይችላልና ድጋፍ ለማግኘት ይሞክሩ፡፡

ነገር ግን ጠንካራ የድጋፍ ሥርዓት መኖሩ ነገሮችን ቀላል ሊያደርግ ይችላል። አማካሪዎች፣ ጓደኞች፣ የሥራ ባልደረቦች እና የቤተሰብ አባላት ነገሮች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ እርስዎን ማበረታታት ይችላሉ፡፡ አልፎ ተርፎም ለስኬት እድሎችዎን ለማሻሻል የሚረዳ ምክር እና ድጋፍ ይሰጣሉ።

### 4ኛ. ፈቃደኝነትዎን ያጠናክሩ / Strengthen Your Willpower/

ለረጅም ጊዜ በተካሄደ ጥናት የሥነ ልቦና ባለሙያዎች በአስተማሪዎቻቸው ተለይተው የሚታወቁትን የልጆች ቡድን ተከተሉ። እነዚህ ልጆች በልጅነት እና በአዋቂነት እንዴት እንደነበሩ ሲያወዳድሩ፣ ተመራማሪዎች በመጨረሻ በሕይወት ውስጥ በጣም ስኬታማ የሆኑት ጽናት ፍቃደኝነታቸውን ጨምሮ አንዳንድ ቁልፍ ባህሪያት አካፍለዋል። እነዚህ ባህሪዎች የልጆቹ አጠቃላይ ስብዕና አካል ናቸው፡፡

ነገር ግን እርስዎም ሊያሻሽሉት የሚችሉት ነገር ነው፡፡ የዘገየ እርካታ፣ ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ መኖርን መማር እና የድካምን ሽልማት መጠበቅ ብዙውን ጊዜ በሕይወት ውስጥ የስኬት ቁልፍ ሊሆን ይችላል። ፈቃደኝነትዎን ለማሻሻል ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸው ስልቶች አሉ፡፡ እነዚህም መዘናጋት፡- ለምሳሌ፣ ክብደት ለመቀነስ እየሞከሩ ከሆነ ግን ከሚወዷቸው መክሰስ ለመራቅ አስቸጋሪ ጊዜ እያጋጠመዎት ከሆነ ፣ በድክመቶችዎ ወቅት እራስዎን ማዘናጋት ለፈተና ላለመሸነፍ ውጤታማ መንገድ ሊሆን ይችላል።

ልምምድ፡- ፈቃደኝነት እርስዎ ሊገነቡ የሚችሉት ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ጊዜ እና ጥረት ይጠይቃል። እንደ ስኳርና መክሰስ መራቅን የመሳሰሉ ለማሳካት ኃይልን የሚሹ ትናንሽ ምግቦችን መመገብ ይጀምሩ። እንደነዚህ ያሉትን ትናንሽ ምግቦች ለመመገብ የፍቃድ ኃይልዎን የመጠቀም ችሎታዎን ሲገነቡ፣ በጣም ትልቅ ግቦች ላይ ሲሰሩ ፈቃደኝነትዎ የበለጠ ጠንካራ ሊሆን ይችላል።

### 5ኛ. ውስጣዊ ተነሳሽነት ላይ ያተኩሩ /Focus on Intrinsic Motivations/

በጣም የሚያነሳሳዎት ነገር ምንድነው? ሽልማቶችና ተስፋዎች ግቦችዎ ላይ እንዲደርሱ የሚያደርግዎት ሆኖ ያገኙታል፡፡ ወይም የበለጠ ተነሳሽነት እንዲሰማዎት የሚያደርግዎት የበለጠ የግል ፣ ውስጣዊ ተነሳሽነት ነው? ለምሳሌ እንደ ገንዘብ፣ ሽልማቶች እና ውዳሴ ያሉ ውጫዊ ሽልማቶች ጠቃሚ ሊሆኑ ቢችሉም ብዙ ሰዎች ነገሮችን ለግል እርካታ በሚያደርጉበት ጊዜ በጣም የሚገፋፉ ሆነው ያገኙታል።

ነገሮችን ስለሚያደርጉት፣ ስለሚደሰቱባቸው፣ ትርጉም ስላገኙዎት፣ ወይም የሥራዎን ውጤት በማየት ስለሚደሰቱ፣ ውስጣዊ ተነሳሽነት ይገፋፋዎታል። ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሚጀምሩት ውጫዊ አነቃቂዎችን ቢሆኑም፣ እነዚያን አዲስ ባህሪዎች ለመጠበቅ ሰዎች እንዲገቡ እና እንዲቀጥሉ የሚያደርጉት ውስጣዊ አነቃቂዎች ናቸው።

ውስጣዊ ተነሳሽነት ስሜትዎን ለማሳደግ እራስዎን ይፈትኑ። ሊደረስበት የሚችል ግብን መከተል ግን ሊሆን አይችልም፡፡ ሆኖም ለስኬት መነሳሳትን ለማሳደግ ጥሩ መንገድ ነው። ተግዳሮቶች በአንድ ተግባር ላይ ፍላጎት እንዲያድርብዎት፣ ለራስዎ ያለዎትን ግምት እንዲያሻሽሉ እና ሊያሻሽሏቸው በሚችሏቸው አካባቢዎች ላይ ግብረመልስ ለማግኘት ያስችልዎታል፡፡ ትንሽ ፈታኝ የሆነ ተግባር መምረጥ ለመጀመር እርስዎን ለማነሳሳት ይረዳዎታል ፡፡

የማወቅ ጉጉት ይኑርዎት። የእርስዎን ትኩረት የሚስቡ እና የበለጠ ለማወቅ የሚፈልጓቸውን ነገሮች ይፈልጉ። ራስዎን ይቆጣጠሩ፡፡ በውጤቱ ላይ ምንም ዓይነት እውነተኛ ተጽዕኖ እንደሌለዎት ከተሰማዎት ግብን ለማሳካት ውስጣዊ ተነሳሽነት መኖር ከባድ ሊሆን ይችላል። ንቁ ሚና የሚጫወቱባቸውን መንገዶች ይፈልጉ። ውድድርን አይፍሩ። እንደ እርስዎ ተመሳሳይ ግቦች ላይ ለመድረስ የሚሞክሩ ሌሎች ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ተስፋ መቁረጥ አለብዎት ማለት አይደለም። እድገትዎን ወይም ጉዞዎን ከማንም ጋር አያወዳድሩ።

### 6ኛ. ከፍ ወዳለ እምቅ ችሎታ ጋር የተገናኙ ባህሪያትን ይንከባከቡ / Nurture Traits Linked to High Potential/

በሕይወት ውስጥ እንዴት ስኬታማ ለመሆን ለመማር እየሞከሩ ከሆነ እነዚህን ቁልፍ ባህሪዎች ለማሳደግ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ያስቡበት፡፡ ህሊና ያላቸው ሰዎች የድርጊታቸውን ውጤት ያስባሉ። እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ምን እንደሚሰማቸው ያስባሉ። ይህንን ባሕርይ ለማሳደግ ድርጊቶች ስለሚያስከትሏቸው ውጤቶች ማሰብ፣ የሌሎች ሰዎችን አመለካከት ግምት ውስጥ ማስገባት፣ አሻሚነትን መቀበል ያስፈልጋል፡፡

ሕይወት ሁልጊዜ ግልፅ ባልሆኑ ሁኔታዎች የተሞላ ነው። ትልቅ የስኬት አቅም ያላቸው ሰዎች ይህንን አሻሚነት በተሻለ ሁኔታ ለመቀበል ይችላሉ። ግትር እና የማይለዋወጥ ከመሆን ይልቅ ያልጠበቁት ነገር ሲመጣባቸው ለመላመድ ዝግጁ ናቸው። አሻሚነትን መቀበልን ለመማር አመለካከቶችዎን መፈታተን እና ከራስዎ ውጭ አስተያየቶችን እና ሃሳቦችን ማገናዘብ ይኖርብዎታል፡፡ የማይታወቁትን አልፈራም ይበሉ፡፡ ለመለወጥ ፈቃደኛ ይሁኑ፡፡ ለልዩነት ዋጋ ይስጡ፡፡ የማስተካከል ችሎታ ያዳብሩ፡፡

አሻሚነትን ከመቀበል በተጨማሪ ስኬት ብዙውን ጊዜ በፍጥነት ለመለወጥ ባለው ችሎታ ላይ የተመሠረተ ነው። ይህንን የማስተካከል ችሎታ ለመኖር እና እንቅፋት ከመሆን ይልቅ ለመማር እና ለማደግ እንደ አጋጣሚዎች በማየት አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እንደገና ማረም ለለውጥ ክፍት በመሆን ማሳደግ ይቻላል፡፡ ዕቅዶች ወይም ሁኔታዎች ሲለወጡ ደግሞ ወደ ኋላ ይመለሱ እና ለመቋቋም የሚያስችሉ መንገዶችን ይመልከቱ፡፡ ደፋር ይሁኑ፡፡

በጣም ስኬታማ ሰዎች ሊወድቅ በሚችል ውድቀት ውስጥ እንኳን አደጋዎችን ለመውሰድ ፈቃደኞች ናቸው። አሉታዊ ስሜቶችን ማሸነፍ እና በበለጠ አዎንታዊ ስሜቶች ላይ ማተኮር አደጋን ከተለመደው አስተሳሰብ ጋር ማመጣጠን ፤ እንደ ሁኔታው ጠንቃቃ እና ተግባራዊ መሆንም ያስፈልጋል፡፡ ስኬታማ የሆኑ ሰዎች በዙሪያቸው ስላለው ዓለም የማወቅ ጉጉት አላቸው። አዲስ እውቀትን እና ክህሎቶችን ጨምሮ የበለጠ ለማወቅ ሁል ጊዜ ይጓጓሉ።

እርስዎም የማወቅ ጉጉትዎን ተግባሮችን ከፍላጎቶችዎ ጋር በማዛመድ፣ ቀልጣፋ መንገ ዶችን በመፈለግ፣ አዳዲስ ነገሮችን በመማር፣ ተወዳዳሪነት በመጨመር ማሳደግ ይችላሉ፡፡ ስኬታማ ሰዎች ለማነሳሳት ውድድርን መጠቀም ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በቅናት ከመያዝ ይቆጠቡ። ጤናማ የውድድር ስሜትን ይፍጠሩ፡፡ በራስዎ ማሻሻያዎች ላይ ያተኩሩ፡፡ በአንድ ነገር ላይ ምርጥ ስለመሆን ከመጨነቅ ይልቅ ለእድገትዎ ትኩረት ይስጡ ሌሎች ሲሳካላቸው ደስተኛ ይሁኑ፡፡

በሕይወት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን አንድም የስኬት መለኪያ የለም፡፡ በርግጠኝነት አንድ መልስ የለም። ሆኖም አንዳንድ የተሳካላቸው ሰዎችን ልምዶች በመመልከት በእራስዎ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ለመተግበር አዲስ ዘዴዎችን እና ስልቶችን መማር ይችላሉ። እነዚህን ችሎታዎች ያዳብሩ እና ያሳድጉ፡፡ ከጊዜ በኋላ ግቦችዎ ላይ ለመድረስ እና በሕይወት ውስጥ የሚፈልጉትን ስኬት ለማሳካት በተሻለ ሁኔታ ሊረዳዎት ይችላሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከጥፋት አጀንዳ የሚገኝ ብሔራዊ ጥቅም የለም!

በቀደመው ዘመን፤ ብሔራዊ ጥቅሞችን የማስጠበቅ እና የማስቀጠል ጉዳይ፤ ዓለም አቀፋዊ የተቃርኖ አጀንዳ ሆኖ ዓለምን በአንድም ይሁን በሌላ ብዙ ዋጋ አስከፍሏል፤ ወዳልተገባ ግጭት እና አለመረጋጋት ውስጥም ከቷል። ባለንበትም ዘመን ፍትሐዊነት የሌላቸውን ብሔራዊ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ የሚደረጉ ጥረቶች፤ ዓለምን ዳግም ወዳልተገባ አለመተማመን እየወሰዱ ነው ።

ፍትሐዊነት ዓለም አቀፍ መርሕ እንዲሆን በቀደሙት ዘመናት ዓለም ብዙ ዋጋ ከፍላለች። አምባገነኖች በኃይል፤ ሴረኞች በሴራ ፍትሐዊ ያልሆኑ ጥቅሞቻቸውን እውን ለማድረግ የሄዱበት ያልተገባ መንገድ፣ መላውን ዓለም ብዙ ዋጋ አስከፍሏል ፤ የሀገራት ሕዝቦችን ለተለያዩ ደም አፋሳሽ የርስ በርስ ግጭቶች እና ጦርነቶች ዳርጓል።

በሴራ እና በኃይል ጥቅሞችን ለማስጠበቅ የተደረጉ ጥረቶች፣ ከዚህም ባለፈ ዓለምን በተለያዩ ጎራዎች ለይቶ ጠላትነትን በመፍጠር፣ ዓለም ከመቼውም ጊዜ በላይ የሕልውና ስጋት ውስጥ እንድትወድቅ አድርጓል፤ ለዚህም በቀዝቃዛውን ጦርነት ወቅት ዓለም ገብታበት የነበረውን አጣብቂኝ ማስታወስ የችግሩን ስፋት እና ጥልቀት አመላካች ነው።

ችግሩ እንደ ሀገር እኛን ኢትዮጵያውያንን የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለን የአደባባይ ሚስጥር ነው፣ ዛሬ ላይ በመሠረታዊነት ሀገራዊ ፈተና የሆኑብን ችግሮቻችን በአንድም ይሁን በሌላ የዚሁ የትናንት ዓለም አቀፋዊ እውነታ ጥላ ስለመሆናቸው የስድስት አስርት ሀገራዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ትርክቶቻችን ተጨባጭ ማሳያዎች ናቸው።

ከነበርንበት እና ዛሬም ካለንበት ስትራቴጂክ ጂኦ ፖለቲካል አካባቢ አኳያ፣ በየዘመኑ የተነሱ ኃይሎች ትኩረት እንደነበርን፣ እነሱ ፍትሐዊ ያልሆኑ ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ከሄዱባቸው የጥፋት መንገዶች የተነሳ በግጭት አዙሪት ውስጥ ለመኖር የመገደዳችን እውነታ ለማንም የተሰወረ አይደለም።

ይህ ራሳቸውን ሁሌም ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጨምሮ በአካባቢው ብሔራዊ ጥቅሞች አሉን የሚሉ የተለያዩ ኃይሎች፣ አለን የሚሉትን ጥቅሞቻችውን በተለመደው የሴራ መንገድ ለማስጠበቅ የሚሄዱባቸው መንገዶች፣ ከኢትዮጵያ አልፎ በአካባቢው ሕዝቦች የመልማት መብት ላይ ትልቅ ፈተና ሆኗል።

ችግሩ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦችን ለከፋ ድህነት እና ኋላ ቀርነት ዳርጓል። የዕጣ ፈንታቸውን ያህል ተደርጎ የሚወሰደው ድህነት እና ኋላ ቀርነታቸው በራሱ ግጭቶችን በማስፋት እና ለግጭቶች ተጨማሪ ጉልበት በመሆን የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ሠላም እና መረጋጋት እንዳይኖራቸው አድርጓል።

የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች በዘላቂነት ለሠላማቸው እና ለልማታቸው የሚያደርጓቸው ጥረቶች፣ በውጪ ሴራ ትርጉም ያለው ፍሬ እንዳያፈራ ተደርጓል። ከዚህም አልፎ የአንድ ቤተሰብ አባል የሆኑ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ቤተሰብነታቸውን እያጡ የራሳቸው ባልሆኑ የተቃርኖ አጀንዳዎች ጠላት ሆነው የሚተያዩበትን ሁኔታ ሲፈጥር ቆይቷል።

የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦችን ፍትሐዊ የጋራ ተጠቃሚነት ማስቀጠል የሚያስችሉ አስተሳሰቦች እንዳይሰፉ፣ ከዚህ ይልቅ የልዩነት እና የጠላትነት ትርክቶችን በማስፋት አካባቢው ከግጭት አዙሪት እንዳይወጣ የሚደረጉ ጣልቃ ገብነቶች በብሔራዊ ጥቅም ስም ሲዘመሩ መስማት ዛሬም ድረስ የተለመደ ሆኗል።

ይህ ችግር አሁን ላይ እንደ ሀገር ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው በመወሰን ከድህነት እና ከኋላቀርነት ለመውጣት የሚያደርጉትን ትግል፣ እንደ ሀገር የጀመሩት ድህነትን ታሪክ የማድረግ መነቃቃት በሁለንተናዊ መልኩ እየፈተነ ነው። እንደ ትናንቱ የአካባቢውን ሀገራት አብሮ የማደግ ተፈጥሯዊ የለውጥ ጉዞም እየተገዳደረ ነው።

ፍትሐዊነት ዓለም አቀፍ መርሕ በሆነበት በዚህ ዘመን ኢትዮጵያውያን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ፣ ከራሳቸው ተርፎ ለአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ተስፋ የሚሆን የለውጥ ንቅናቄ ውስጥ መገኘታቸው ዘላቂ ለሆነ የጋራ ተጠቃሚነት እና አብሮ የማደግ መነሳሳት መንገድ መሆኑ ታውቆ ሊበረታታ እንጂ በተቃርኖ እሳቤ ሊፈተን የሚገባ አልነበረም።

ይህን ታሪካዊ እውነታ ከማንም ይልቅ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች በአግባቡ ሊረዱት እና ከራሳቸው ቀጣይ ብሩህ ዕጣ ፈንታ ጋር አስተሳስረው ሊያጤኑት ያስፈልጋል። ትናንት ከውጪ ጣልቃገብነት ጋር በተያያዘ እንደ አንድ ቤተሰብ ለራሳችን ላልሆነ አጀንዳ ከከፈልነው ያልተገባ ዋጋ አኳያ አሁናዊ መንገዳችንን ልንመረምረው ይገባል።

የአካባቢው ሀገራት ብሔራዊ ጥቅሞች በአንድም ይሁን በሌላ የተሳሰሩ ናቸው፣ አንዳችን የሌላችን ብሔራዊ ጥቅም አካል ነን። እነዚህን ጥቅሞች ማስከበር የጋራ ኃላፊነታችን ነው። የቀጣናው ሀገራት ሕዝቦች የመልማት ፍላጎት እውን ሊሆን የሚችለው ይህን እውነታ በአግባቡ መገንዘብ ስንችል እና ለተግባራዊነቱ ቁርጠኛ ስንሆን ብቻ ነው ።

ከዚህ ውጪ የውጪ ኃይሎችን የጥፋት አጀንዳ ተሸክሞ በመሄድ የሚገኝ ትርፍ/ብሔራዊ ጥቅም አለ ብሎ ማሰብ ከብዙ ትናንቶች ስህተት ለመማር ፈቃደኛ አለመሆን እና ከአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች የዘመናት የመልማት ፍላጎት በተቃርኖ መቆም ነው። ከግጭት አዙሪት ወጥተው የራሳቸውን እድል በራሳቸው እንዳይወስኑ የማድረግ የጠላትነት ተልዕኮም ነው!

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ጭፍን ከሆኑ አስተሳሰቦች እንራቅ

አዶኒስ (ከሲኤምሲ)

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ መውጣትን ተከትሎ በርካታ አወዳሽ እና አውጋዥ አስተያየቶች ተሰምተዋል፤ ጨለማና አስፈሪ ሃሳቦችም ተደምጠዋል። ሀገርንና ሕዝብን በሚጠቅም መልኩ ለውጦችን ማምጫ፤ በሂደትም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያበለፅግ ገጸ በረከት ነው ተብሏል።

ተመሳሳይ የፖለቲካ ማሻሻያ ያደረጉ ሀገራትን በመጥቀስ የማሻሻያውን አስፈላጊነት በተጨባጭ ምሳሌ አስረግጠው ለማስረዳት የሞከሩ ጥቂት አይደሉም። ብርሃንን የምናይበት ነው፤ ለውጥ እናመጣለን፤ ለውጡንም በጋራ እናጣጥማለን ያሉ እና የሚሉ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች በርካታ ናቸው።

አንዳንዱ ደግሞ ምንም ሳይገባው ፖለቲካውን ስለደገፈ እና ስለተቃወመ ብቻ በአሉታዊ እና አዎንታዊ መልኩ ብዙ ብዙ ብለውበታል። እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል። የፖሊሲ ማሻሻያው ጉዳይ አንድን ፓርቲ (መሪ) ስለደገፍነውም ስለነቀፍነውም አስተያየት የምንሰጥበት ሳይሆን እውቀት የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ ነው።

አስተያየቶች በተቻለው መጠን ሁሉ ሙያዊ እውቀት ላይ ተመስርተን መሆን አለባቸው። ዋናው ጥያቄ ሀገርን ይጠቅማል? ሕዝብን ከስደት፣ ከረሃብና ጥም ያድናል? ኢኮኖሚው ላይ ጠብ የሚል የሚታይ ነገር ያተርፋል? ዳዴው ቆሞ ወደ መራመድ ፤ ከዛም ሮጦ ድህነትን ወደ ማምለጥ ያሸጋግራል ወይ? የሚለው ነው ጥያቄ መሆን ያለበት።

ወደ ጉዳዩ ልመለስ እና በፖሊሲ ማሻሻያው ዙሪያ የሚነሱ ሀሳቦችን በሁለት መልኩ ማየት ይገባል። አንደኛው ከፖለቲካ ሥርዓቱ ጋር ካለው ተቃርኖ አኳያ ማሻሻያውን እያጥላላ ያለ ቡድን ነው፤ ሌላው ደግሞ ፖሊሲው ቢተገበር ጥቅም አለው ሆኖም ግን አብረው የሚመጡ ስጋቶች አሉ የሚለው ነው።

የፖሊሲ ማሻሻያውን በአግባቡ መምራት ካልተቻለም በዚህ መንገድ ሄደው ያልተሳካላቸው ሀገሮች ወደገቡበት ቀውስ እንገባለን ከሚል ሙያዊ አስተሳሰብ ይመነጫል። እዚህ ላይ መታየት ያለበት አስተያየቱ ምንም ይሁን ምን ሀገርን ለመጥቀም ከማሰብ የሚሰነዘር ከሆነ እሰይ ይበል የሚያሰኝ ነው።

ምክንያቱም ስጋቱን የሚተነትነው አካል እስከ መፍትሔው ያክላል፤ የመውጫ መንገዱን ያመላክታል። ቀዳዳውን የመድፈኛ መላዎችንም ያመጣል። ይተነትናል። ይሄ ገንቢ አስተያየት ነው። መሆንም ያለበት ነው።

ከዚህ ውጪ እውነታውን ሙያዊ ባልሆነ፤ በእውቀት እና በመረጃ ባልታገዘ ሁኔታ ሕዝብን ግራ በማጋባት፤ በማሻሻያው ተስፋ እንዳይኖረው፤ ሕዝብ ውስጥ ስጋት በመፍጠር፣ በሀገር ላይ መአት የመጣ ያክል እንዲሰማው የሚያደርጉም በስፋት እየተስተዋሉ ነው።

ስለ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ከመናገር ይልቅ ቀድሞ ማሻሻያው ሲደረግ ዋናው ዓላማ ምንድነው ብሎ በቀናነት ማንሳት ያስፈልጋል። ዋናው ዓላማውም በሕጋዊ ምንዛሪና በጥቁር ገበያ መካከል ያለውን ልዩነት ማጥበብና ሕገወጥነትን ማስቀረት ነው። ተዘግቶ የነበረውን ኢኮኖሚ በመክፈት ዓለምን መቀላቀል ነው።

ሀገራት ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያላቸውን ጥገኝነት ለመቀነስ እና የሀገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ ተኪ ምርቶች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ተኪ ምርት ለሀገራዊ ምርትና ኢኮኖሚ እድገት ተስፋ የሚሰጥ ቢሆንም አንድምታው ውስብስብ እና ዘርፈ ብዙ ነው። ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስገባው እና ወደ ውጭ የምትልከው ምርት መጠን የተመጣጠነ አይደለም።

ከውጭ ምርቶችን ለማስገባት 18 ቢሊዮን ዶላር ስናወጣ ወደ ውጭ በመላክ ደግሞ የሚገኘው ገቢ ከአራት ቢሊዮን ዶላር የዘለለ አይደለም። ይሄንን ወጪና ገቢ ምርትን ወደ ማጣጋጋትና የሚታዩ ክፍተቶችን ለመድፈን መሥራት አንድ ጉዳይ ነው።

ሌላው ሀገርና ሕዝብ ተጠቃሚ የሚሆነው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ደሃን በሚጠቅም መንገድ ሲመራ ነው። ዛሬ በትልቅ ስጋትነት በባለ ሙያዎች የሚነሳው መንግሥትም የሚያምንበትና ችግሩን ለመከላከል የሚሠራው በተለይ አነስተኛ ገቢ ባላቸው የመንግሥት ሠራተኞችና በዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ባሉ ዜጎች ላይ ነው።

የኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረግ አስገዳጅ የሆነበት ሌላው ምክንያት ኢንቨስትመንት በሚፈለገው ደረጃ አለማደግ፣ በቂ መሠረተ ልማት አለመኖር፣ የተቋማት ተልዕኮ የመፈጸም ውስንነት ነው። ሀገራዊ እዳ ጫናው የሚፈለገውን ያህል እድገት ማምጣት አላስቻለም። በመሆኑም የፖሊሲ ለውጡ አንዳንድ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እንደሚሉት ዘግይቶ ሊሆን ይችላል።

መታሰብ ያለበት በቀጣይ ለሀገራችን እድገትና ብልጽግና ማረጋገጥ የሚያስችለን እንዲሆን እንዴት አድርገን እንጠቀምበት? የትኛው ቦታ ላይ ምን መሠራት አለበት? መንግሥት ያላየው ክፍተትስ የት ነው ያለው? የሚለውን ወደፊት ማምጣትና በዛ ለመጠቀም መሞከር ነው ።

በአሁኑ ወቅት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው እንደአንድ ስጋት ሆኖ የሚቆጠረው መንግሥት ሠራተኞች፣ አርሶ አደሮችና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ በሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ጫና ያሳድራል፤ የኑሮ ውድነትን ያባብሳል በሚል ነው። ለዚህ ደግሞ መንግሥት መፍትሔ ያላቸውን ሀሳቦች አቅርቧል። እየሠራበትም ይገኛል። ሌሎች ሀገሮች ያልተጠቀሙበትን ደሀውን የኅብረተሰብ ክፍል በመደጎም የኑሮ ውድነቱን እንዲሸከመው ማድረግ መሆኑን አሳውቋል።

ለዚህም እንደ መንግሥት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በነዳጅ፣ በመድኃኒት፣ በማዳበሪያ የሚያደርጋቸው ድጎማዎች እንዲሁም ዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ ለሆኑ የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ማሻሻያ ማድረግ ነው። በከተማ ለሚኖሩ ዝቅተኛ ኢኮኖሚ ያላቸው ዜጎችም በሴፍትኔት የሚደገፉበት ፕሮግራም ይኖራል። ነዳጅም ማኅበረሰቡ ሕይወት ላይ ጫና እንዳያደርስም መንግሥት ለድጎማ 100 ቢሊዮን ብር ለማውጣት ዝግጁነቱን አስታውቋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው ሥራ ሲሠራ የቆየው በጥቁር ገበያ ነው። ደላላና ጥቁር ገበያ የመሪነትን ቦታ ይዘው ሕገወጥነት ተስፋፍቶ ቆይቷል። የጥቁር ገበያ የዶላር ምንዛሪ በአደባባይ የሚቸበቸብበት ሀገር ተፈጥሯል። አሁን ኢኮኖሚው ክፍት ሲደረግ ብዙ የሚያሳስቡ፣ ያልተጠበቁና የሚያስደነግጡ ነገሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ይሄንን አስቀድሞ ትንተና በመሥራት አደጋው የሚቀንስበትን መንገድ ማስተካከል ይገባል።

ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ወጪ ምርትን መጨመርና ተገቢውን የገቢ ግብር መሰብሰብ በእነዚህና በመሳሰሉት ገቢ አመንጪ ነገሮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ከተቻለ ስጋቱ ቢያጋጥም እንኳን አስደንጋጭ አደጋ ሆኖ አይቀጥልም ። በጊዜ ሂደት እየሳሳና እየመነመነ ሄዶ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲው እዳ ሳይሆን ምንዳ ሆኖ ይቀጥላል ።

ለሁሉም ግን አንድን ነገር በጭፍኑ አይቶ ከማጣጣልና ጭራቅ አድርጎ ከመሳል ይልቅ መልካሙን አስፍቶ ወደፊት በቅንነት መራመድ ይገባል። ጭፍን ከሆነው አስተሳሰብና አመለካከት መውጣት በቀዳሚነት የምናስባትን ሀገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ያግዛል። ለዚህ ጭፍን ሳንሆን መሥራትን ይጠይቃል።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ጎሽ ለልጇ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የዓመታት ትዳሯን ሞት ከፈታው ወዲህ ወይዘሮዋ የብቸኝነት ሕይወት ወርሷታል፡፡ አራት ልጆቿን ያለአባት ማሳደግ፣ ቤቷን ያለአባወራ መምራት ለእሷ ቀላል አልሆነም። እሷ ባትማርም በተቻላት አቅም ልጆቿን ታስተምራለች፡፡ ሁሉም ሴቶች ናቸውና በምክንያት ቤት እንዲውሉ አትሻም።

ልጆቹ አስቀድሞ ሕይወት የገባቸው ይመስላል። ለትምህርት የሰጡት ትኩረት ለየት ያለ ነው። ሁሉም ትምህርት ቤት ውለው ሲመለሱ የነገውን ዓለም ያስባሉ፡፡ ትናንት እንደእነሱ የተማሩ ወድቀው እንዳልቀሩ ሰምተዋል፡፡ አብዛኞቹ ጥሩ ደረጃ ላይ ናቸው፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ በመማራቸው፣ ቀለም በመለየታቸው ነው፡፡ ይህ እውነት በተለይ ለሴት ልጆች ትርጉሙ ይለያል፡፡

ወይዘሮ ካንቺ ወዲያ ዘውዱ ኑሮና ሕይወቷ ምስራቅ ጎጃም ሉማሜ ከተማ ነው፡፡ ቀደም ሲል በተወለደችበት የገጠር ቀበሌ ልጅነቷን አሳልፋለች፡፡ ከዓመታት ወዲህ ወደከተማው ዘልቃ ትዳር ይዛ ልጆች ከወለደች ወዲህ ሕይወቷ በዚሁ አካባቢ ሆኗል፡፡

ካንቺ ወዲያ ባለቤቷ በሞት ከተለያት በኋላ ጥቂት ጊዜያትን በብቸኝነት ቆየች፡፡ ውሎ አድሮ ግን የትዳር አጋር የሚሆናት ሰው ለጋብቻ አሰባት፡፡ እንዲህ መሆኑን አልጠላችውም። በብቸኝነት መኖር ለሴት ልጅ በእጅጉ ከባድ ነው፡፡ በብዙ ይፈትናል። በትዳር መሰብሰቧ ያኮራታል፣ ያስከብራታል፡፡ አራት ልጆች ቢኖሯትም ብቸኝነትን ለማምለጥ፣ ተከብራ ለመኖር ስትል ሁለተኛውን ጋብቻ መሠረተች፡፡

### የስለት ልጅ...

የመጀመሪያዎቹ የጥምረት ጊዜያት መልካም ሆነው ተጓዙ። አባወራው ከትዳሩ ልጅ ማግኘትን ይፈልጋል፡፡ ይህ ፍላጎት



**ወይዘሮ ካንቺ ወዲያ ዘውዱ፣**

ደግሞ የእሱ ብቻ አልሆነም፡፡ እሷም ብትሆን ወንድ ልጅ ለመውለድ ስትመኝ፣ በየታቦቱም ስትሳል ቆይታለች፡፡ ከአሁኑ ባሏ ወንድ ልጅ ብታገኝ ደስታዋ ነው፡፡ በስለቷ የልቧ ሞልቶ ፈጣሪዋን የምታመሰግንበት ቀን ይናፍቃታል፡፡

ካንቺ ወዲያና ባለቤቷ በትዳር ያቆሙት ጎጆ ከጥቂት ቆይታ በኋላ የምሥራችን አበሰረ፡፡ እንደታሰበው ሆኖ ወይዘሮዋ ነፍሰጡር ሆናለች፡፡ ይህ ከታወቀ ጀምሮ በጥንዶቹ መሐል መተሳሳቡ ጨምሯል፡፡ እሷ ለዓመታት የወንድ ልጅ ናፍቆት ሲያሳሳት ኖሯል፡፡ አሁን ግን ስለቷ ሰምሮ የልቧ ሞልቷል፡፡

ወይዘሮዋ እንደማንኛዋም ነፍሰጡር ከሕክምና ትሄዳለች። የክትትል ቀጠሮ በኖራት ጊዜ በተሻለ ሆስፒታል መገኘት ልማዷ ነው፡፡ እንዲህ መሆኑ ጤናዋን አስጠብቆ ልጇን በሠላም ያሳቅፋታል፡፡

### ከዘጠኝ ወር በኋላ ...

አሁን ወይዘሮዋ የመውለጃ ጊዜዋ ደርሷል፡፡ ይህ እንደታወቀ ለአራሷ የሚበጅ ቤት ያፈራው ሁሉ ሲዘጋጅ ቆይቷል፡፡ ለመውለድ የመጀመሪያዋ አይደለምና የምጡን ስቃይ አልፈራችም፡፡ አባወራው በበኩሉ የሚወለድለትን አቅፎ ሊስም ፣ እንደአባትም ልጁ ሊያደርገው ጓጉቷል። ጊዜው ደርሶ ከቀናት በአንዱ ወይዘሮዋ ከሆስፒታል ተገኘች፡፡ ማለዳውን የጀመራት ምጥ በዋዛ አልተዋትም። እያንቆራጠጠ፣ እያስጨነቀ ሰዓታትን አስቆጥሯል፡፡

የቆይታው ብዛት አዋላጆቹን ከአንድ ውሳኔ ያደረሳቸው ይመስላል፡፡ ለመወለድ ከጫፍ ደርሶ «መጣሁ» የሚለውን ጨቅላ በመሣሪያ ታግዘው ለማውጣት ተዘጋጅተዋል፡፡ እንዳሰቡት ሆኖ ሕጻኑን ከእናትዬው ማሕፀን ጎትተው አወጡ። የጨቅላው ለቅሶና የእናቲቱ እፎይታ በአንድ ተጋመደ፡፡ እናት ፈጥና ምጧን ረሳች፡፡ በፈገግታ ልጇን አንስታ ታቀፈች ፡፡

እንዲህ በሆነ ጥቂት ግዜ በኋላ እሷን ጨምሮ ባለቤቷ ያዩት እውነታ ከድንጋጤ ጣላቸው፡፡ የእነሱ ልጅ ጭንቅላት እንደሌሎች ሕጻናት አይደለም፡፡ መሐሉ ተሰርጉዶ፣ ግንባሩ ጥግ ተሰብሯል፡፡ እጆቹ እንደልብ አይታዘዙም፣ ወገብና እግሩ እንዳሻው አይሆንም፡፡ እንዴትና ለምን ማለታቸው አልቀረም።

ውሎ አድሮ ጉዳዩ በውል ተረጋገጠ፡፡ በወሊድ ጊዜ ልጁን ከማሕፀን ለማውጣት በነበረው ትግል በአዋላጆቹ ስህተት ሕፃኑ ከፍ ያለ ጉዳት አጋጥሞታል፡፡ ወላጆቹ ችግሩን በቅርብ ላሉ ባለሙዎች አሳይተው ይህንኑ አረጋግጠዋል። መፍትሔውን ሲጠይቁ ደግሞ ከጥቂቶቹ ያገኙት ምላሽ አስደንጋጭና ተስፋ አስቆራጭ ነበር፡፡

አንዳንዶቹ የልጁ ጉዳት ከጭንቅላቱ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ፈጽሞ እንደማይድን ነገሯቸው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ተስፋ ሳይቆርጡ ከፍወዳለ ሕክምና ቢወስዱት እንደሚድን ነገሯቸው። መልካም ነገር ያሏቸውን ሀሳብ ይዘው ሐኪም ፊት ቀረቡ፡፡ ሐኪሞች የሀሳባቸውን አልነሷቸውም፡፡ ተገቢውን የሕክምና ማስረጃ ጽፈው ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አመላከቷቸው፡፡

### ‹‹ለሚሞት ልጅ አትድከሚ››

ወይዘሮዋ ውላ አላደረችም፡፡ በስንት ስለት ያገኘችው ወንድ ልጇ ተሰናክሎ መቅረቱ ከኀዘን ያለፈ ቁጭት አሳድሮባታል፡፡ እሷ ከትንፋሽ በቀር አንዳች ምልክት ባልነበረው ጨቅላ ፈጽሞ ተስፋ መቁረጥ አትፈልግም፡፡ እንደልጅ እየሳቀ፣ ባያጫውታትም፣ ዓይኗን እያየ ባይለያትም ለእሷ የአካሏ ክፋይ ተወዳጅ ልጇ ነው፡፡ የገባችበት ገብታ ጤናውን ትሻለች፡፡

ጨቅላ ልጇን አዝላ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ስትነሳ አንድም ሰው «በቸር ግቢ» ያላት የለም፡፡ ስለሕክምናው ለመሄድ መቁረጧን ያስተዋሉ ብዘዎች ከዳር ቆመው አሽሟጠጧት፣ አነወሯት፡፡ ለማይድን ልጅ አገር ቆርጣ የመሄዷ ጉዳይ አናዷቸው፣ ሊመልሷት፣ ሞከሩ፡፡ ሁሉም እየተነሳ ይፈረድባት፣ ይቆጣት ያዘ፡፡ እሷ ግን በፈጣሪዋ ተስፋ አልቆረጠችም፡፡ በስለት ለምና ያገኘችው ብቸኛ ወንድ ልጇ መሆኑን አስባ መንገዷን

.. ወደ ገጽ 17 ዞሯል



ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ጎሽ ...

**ከ16ኛው ገጽ የዞረ**

ቀጠለች፡፡

ካንቺ ወዲያ አዲስ አበባን በስም ካልሆነ አይታት አታውቅም፡፡ እሷ ትውልድ ዕድገቷ ገጠር ላይ ነው። ዛሬ ግን ከማታውቀው ሰፊ የከተማ ባሕር ልትሰምጥ ግድ ሆኗል። እሷ ማንበብ መጻፍ ይሉትን አታውቅም፡፡ ስልክ መደወል አትችልም፡፡ ጉዞ በጀመረች ጊዜ አብሯት የመጣ፣ የተከተላት ወዳጅ ዘመድ ጎኗ የለም፡፡ ይህ ሁሉ ጎዶሎ ከእሷ ጋር መሆኑን ታውቃለች፡፡ እንዲያም ሆኖ ችግሩ ሰበብ አልሆናትም፡፡ ልጇን ከጀርባዋ እንዳዘለች መሐል አዲስ አበባ ገብታለች፡፡

**አዲስ አበባ ላይ ...**

ስፍራው ስትደርስ ካገሯ መነሳቷን ያወቀ አንድ ሰው ከመናኸሪያው ቆሞ ጠበቃት፡፡ ይህ ሰው የድሮው ሟች ባለቤቷ ታናሽ ወንድም ነው፡፡ ባገኘችው ጊዜ ደስታዋ ወሰን አጣ፡፡ በምስጋና ፈጣሪዋንና እሱን ደጋግማ አመሰገነች፡፡ መልካሙ ሰው የደረሰባትን ችግር ሰምቷል። ቤቱ መውሰድ ባይችልም ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሊያደርሳት፣ ጉዳይዋን ሊፈጽምላት ተዘጋጅቷል፡፡

አሁን ሁኔታዎች ተመቻችተው መስመር ይዘዋል። ከሆስፒታሉ የደረሰችው ወይዘሮ ለልጇ ሕክምና ልታገኝ፣ የልቧም ሀሳብ ሊሞላ ነው፡፡ ከሆስፒታሉ ግቢ እንደደረሱ ማረፊያ የሚሆን ቦታ አላጣችም፡፡ በቀጣይ ቀናት ሕጻኑ በቂ ምርመራ አግኝቶ ጉሉኮስ ተሰጠው።ለተከታታይ ቀናት ጤናውን እያዩ በእጃቸው ያቆዩት ሐኪሞች እንደሌሎቹ ተስፋዋን አልነጠቋትም።ውሎ አድሮ በልጇ ላይ ያየችው ለውጥ ተስፋዋን አለመለመው፡፡ ወደውስጥ የታጠፈው ምላሱ ተዘርግቶ በወጉ ምግብ መቅመስ፣ ጡት መጥባት ጀመረ፡፡ የተቆለመመ አንገቱ ተመለሰ፡፡ የታሰሩ እጆቹ ተፍታቱ፣ የላመው አጥንቱ በአካል እንቅስቃሴ ጠንክሮ ቀና ለማለት ሞከረ፡፡ እንዲህ አይነቱ ለውጥ ለእናት ካንቺ ወዲያ ከተስፋ በላይ ሆኖ አከረማት፡፡

ከአንድ ወር ላላነሰ ግዜ በአዲስ አበባ የቆየችው ወይዘሮ ለዳግም ቀጠሮ እንድትመለስ ተነገራት። ይህን ጊዜ ሀገሯ መግባት ነበረባትና ልጇን አዝላ ወደቤቷ አቀናች፡፡ መንደሯ ስትደርስ ግን ማናቸውም የልጁን ለውጥ አይተው ማረጋገጥ አልፈለጉም፡፡ ሁሉም የትናንትና ችግሩን እያስታወሱ ዳግመኛ ይዛው እንዳትመለስ በቁጣና ማስጠንቀቂያ አሳሰቧት፡፡

ካንቺ ወዲያ የሰማችው እያቆሰላት፣ በተናገሯት ክፉ ሀሳብ ተክዛ ሰነበተች፡፡ ወይዘሮዋ የሌሎቹ ሲገርማት የባለቤቷ ባሕርይ መለወጥ ደግሞ ይበልጥ አስከፍቶ አንገቷን አሰደፋት፡፡ ገና ስትመጣ አንስቶ ፊት ነስቷታል። እሱም ለማይድንና ተስፋ ለማይጣልበት ልጅ ሀገር አቋርጣ መሄዷን አላመነበትም፡፡

ሚስት ሀሳቡን ስትረዳ ለምን ብላ ጠየቀችው። የልጅ አባት፣ ባለቤቷ ለምላሹ አልዘገየም፡፡ ልጁን ለለማኝ፣ አልያም ለመንግሥት ሰጥታ ሠላማዊ ኑሯቸውን እንዲቀጥሉ ቁርጥ ባለ ቃል አረጋገጠላት፡፡ የሰማችውን ማመን ባትፈልግም የሆነው ሁሉ እውነት ነበር፡፡ አባወራው ከዚህ በኋላ ለእንዲህ አይነቱ ልጅ ወላጅ አባቱ መባልን አይፈልግም፡፡

**ፈተና ...**

አሁን የጥንዶቹ አዲስ ትዳር መፈረካከስ ይዟል። የሁለቱ ሀሳብ መለያየት ጎጇቸውን እያቆመው አይደለም፡፡ ካንቺ ወዲያ ስለልጇ ጉዳት የሚያጽናናት አንድ ሰው እንኳን ጎኗ የለም፡፡ ‹‹አይዞሽ›› የሚሏት አባቷን በሞት ካጣች ቀናት ተቆጥረዋል፡፡ ዳግመኛ ለቀጠሮ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ስትዘጋጅ አንዳች ሳንቲም ከእጇ አልነበረም፡፡ ባሏን ስትጠይቅ ፊቱን ያዞርባታል። ሌሎችን ስታማክር ጉዞዋ ለሌላ ጥቅምና በልጁ ለመለመን መሆኑን እያወሱ ያነውሯታል፡፡ ይህን ሁሉ ፈተና የያዘችው ወይዘሮ ከመንገዷ አልታቀበችም፡፡ በቤቷ የምታረባቸውን ዶሮዎች በሙሉ ሸጣ ልጇን አዝላ ዓባይን ተሻገረች፡፡

ተመልሳ ከሆስፒታሉ ሕክምናውን ስትቀጥል በውስጧ ካለው ተስፋ በቀር ማንም ጎኗ አልነበረም፡፡ የቀድሞ ባሏ ወንድምም የአቅሙን ያህል አድርጎ ወደራሱ ሥራ ሄዷል፡፡ ወይዘሮዋ ስለእሱ ያላት ምሥጋናና ክብር ለየት ይላል፡፡ እሱ ሰው ሁሉ ባነወራት ጊዜ በክፉ ቀን የደረሰላት ባለውለታዋ ነው፡፡

ካንቺ ወዲያ አሁን የአዲስ አበባን ሕይወት ለብቻዋ መጋፈጥ ይዛለች፡፡ ማንበብ መጻፍ የማትችለው ወይዘሮ በሌሎች እገዛ የተጻፈውን እያስነበበች ስትሮጥ ትውላለች። ተስፋ አለው በተባለው የሦስት ዓመት ልጇ ላይ ዕምነቷ እንደጸና ነው፡፡ ለጊዜው በሆስፒታሉ ማረፊያና ምግብ ተሰጥቷታል፡፡ በየጊዜው በሐኪሞች የታዘዘለትን ሕክምና በትኩረት ትፈጽማለች፡፡

**‹‹እህል ውሃችን አለቀ በቃ ! ››**

ከወር በኋላ ሀገሯ ስትመለስ አባወራውን ለትራንስፖርት ጥቂት እንዲያግዛት ተማጸነችው፡፡ ያለውን ይሰጠኛል በሚል ተስፋ አድርጋ ነበር፡፡ እሱ ግን በተቃራኒው ቁርጥ ሀሳቡን አሳወቃት፡፡ ከዚህ በኋላ ከእሷ ጋር ትዳር እንደማይቀጥል፣ ልጁም የሚበጅ ባለመሆኑ እንደማይፈልገው ነገራት፡፡ በዚህ መነሻ እህል ውሃቸው አልቆ ትዳራቸው ተፈታ፡፡ ወይዘሮዋ የፈረሰ ጎጇዋን በልቧ፣ የታመመ ልጇን በጀርባዋ አዝላ ዳግም ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተመለሰች፡፡

ቁጭ ብላ በተከዘች ቁጥር ባሏ በገዛ ልጁ ላይ የተናገረውን ታብሰለስላለች፡፡ በጊዜው ልጁ የገንዘባችን መጨረሻ፣ የጉልበታችን ማድከሚያ ነው ይላት ነበር፡፡ ለእነሱ ስለማይበጅም እንደ ዕቃ አውጥታ እንድትጥለው ሲያሳስባትም ቆይቷል፡፡ እሷ ግን ‹‹ልጄን አልጥልም፣ በሕይወት እስካለ አስታምመዋለሁ ከሞተ ደግሞ እቀብረዋለሁ›› በሚል አቋም ቤት ትዳሯን ፈታለች፡፡ አራት ሴት ልጆቿን በትናለች፡፡ እንዲህ በማድረጓ ደግሞ ተቆጭታ፣ ተጸጽታ አታውቅም፡፡

‹‹አዲስ መዝገብ›› ስትል የሰየመችውን የስለት ልጇን ጠጋ ብዬ አስተዋልኩት፡፡ መልኩ በእጅጉ ያምራል። ለመንካት የሚያሳሱ እጆቹን በጥንቃቄ ዳሰስኳቸው። ይለሰልሳሉ፡፡ በወጉ ግን እየሠሩ አይደለም፡፡ ወገቡና አንገቱ አይንቀሳቀስም። እናት ባሻት አቅጣጫ ስታዞረው እንዳለችው ይሆናል፡፡ ሁኔታው በእጅጉ ውስጥን የሚፈትን፣ አንጀትን የሚበላ ነው። ሕጻን አዲስ እንደ ዕድሜ እኩዮቹ አያለቅስም፣ አይረብሽም፣ አይስቅም፡፡

እናቱ ለማስተኛት፣ ለማዘልና ለማቀፍ ተመችቷት አያውቅም። ገና በእጇ ሲገባ እንደወረቀት እጥፍጥፍ ይልባታል፡፡ እሷም ሆነች እሱ ተቀምጠው አያውቁም፡፡ ምግብ በፈለገ ጊዜ አንጀቱ ሲታጠፍ አይታ ያላትን ታጎርሰዋለች። በደመነፍስ እንደማላመጥ ብሎ ከአፉ ደጃፍ ይተወዋል፡፡ በእሷ እገዛ እንደምንም ለሆዱ እንዲደርስ ታደርጋለች፡፡

የሕጻኑ ሁኔታ አስገርሞኝ በሀሳብ ተውጬ ፈዘዝኩ። ፊቴን ያየችው እናት የሚንከባለሉ ዓይኖቹን እየጠቆመች አንዳች ምልክት እንድሰጠው ጠየቀችኝ። እንዳለችኝ ለማድረግ እጆቼን በዓይኖቹ ዙሪያ ደጋግሜ አመላለስኳቸው፡፡ ዓይኖቹ እጆቼን አይተው አልተከተሉም፡፡ እንደነበሩ ናቸው፡፡ ደነገጥኩ፡፡ ሁኔታውን በዝርዝር ከመጠየቄ በፊት እናት ግልጹን ነገረችኝ፡፡ ሕጻኑ ሲወለድ አንስቶ እስካዛሬ ድረስ ሁለቱም ዓይኖቹ አይተውለት አያውቁም፡፡ እውነቱን ከእሷ ሳውቀው ደግሞ ይበልጥ ውስጤ ተረበሸ፡፡ እሷ ግን ተስፋ አልቆረጠችም። የዓይኑ ሕክምና በምኒሊክ ሆስፒታል ሐኪሞች እየታየለት መሆኑን ነገረችኝ፡፡ ተስፋዋ ልቤን ሞላው፣ ጥንካሬዋ አበረታኝ።

**ልጅን ያለ ...**

አራት ልጆቿ በሕጻኑ ሕመም ምክንያት ከአንድ ቤት አልኖሩም፡፡ እናት ጎጆዋን ዘግታ ከወጣች ወዲህ ኑሯቸው በተለያየ ዓለም ሆኗል፡፡ አስቀድማ እነሱን ማስተማሯ በጅቷታል፡፡ ትልቋ ልጇ የጤና ባለሙያ ሆናለች፡፡ ሁለተኛዋ አስራ ሁለተኛን ጨርሳ አዲስ አበባ ሰው ቤት ተቀጥራለች። ሌላዋ ደግሞ እዛው ሉማሜ ተቀምጣ የእናቷን መምጣት እየጠበቀች ነው፡፡ በደረጃ ታልፍ የነበረችው የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ደግሞ ትምህርቷን አቋርጣ ከእናቷ ጋር መንከራተት ይዛለች፡፡

እኔና ወይዘሮዋ የተገናኘነው ሆፕ.ኤስ.ኤች በተባለው ግብረሠናይ ድርጅት ውስጥ አዲስ ዓመትን ለመቀበል በተደረገው የወላጆችን የሕጻናት ዝግጅት ላይ ነበር፡፡ ሆፕ እንደ ሕጻን አዲስ መዝገቡ ላሉ ሕጻናትና ወላጆቻቸው ድጋፍ፣ ምክርና ሕክምና የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

ወይዘሮ ካንቺ ወዲያ ልጁን ለሕክምና ካገሯ ይዛ በወጣችበት አጋጣሚ በአካባቢው የሠላም እጦት ምክንያት መንገድ በመዘጋቱ የዚህ ድርጅት እንግዳ ሆናለች፡፡ ዛሬም በሀሳቧ የተዘጋ ጎጆዋ የተበተኑ ልጆቿ ይታዩዋታል፡፡ ዘወትር አንገቷን ደፍታ መንገዷን ታስባለች፡፡

ብዙ የተባለችበት ልጇ አልዳነላትም፡፡ ዛሬም ከሕመሙ ጋር ቀጥሏል፡፡‹‹ ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች›› እንዲሉ ሆኖባት ወይዘሮዋ ስለትንሹ ፍሬዋ ብዙ ዋጋ ከፍላለች፡፡ እንዲያም ሆኖ ነገን በተስፋ እየጠበቀች ነው፡፡ መልካም ልቦች ያላቸውን ካገኘች፣ ለትራንስፖርት አታጣም፡፡ ሀገሯ ሠላም ሆኖ መንገዱ ከተከፈተ ለቤቷ ትበቃለች፤ ለልጆቿ ትደርሳለች መንፈሰ ብርቱዋ ወይዘሮ ካንቺ ወዲያ ዘውዱ፡፡


# ድጋሚ የወጣ የሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ

ስማቸው ከዚህ በታች የተጠቀሱት ተበዳሪ ከቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ የወሰዱትን ብድር ባለመክፈላቸው ተቋሙ ከዚህ በታች የተመለከተውን በዋስትና የተያዘ ቤት ባለበት ሁኔታ በጨረታ ይሸጣል።

| ተ.ቁ | የተበዳሪው ስም | የዋሱ ስም | ብድር የወሰዱበት ቅርንጫፍ | የሚሸጠው ንብረት | ንብረቱ የሚገኝበት አድራሻ | የንብረቱ ዓይነት | የካርታ ቁ እና የቦታ ስፋት | የጨረታው መነሻ ዋጋ | የጨረታ ሽያጭ ቀን | ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ቅድሰት ጌታቸዉ | አቶ ዘላለም ማቱሳላ | አዋሳ ቅርንጫፍ | ቤት | አዋሳ | ቤት | የካርታ ቁጥር 00017/04 የቦታ ስፋት 250 ካ.ሜ | 2,000,000 ሁለት ሚሊዮን | ጥቅምት 12/2017 ዓ.ም | ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት |
| 2 | ፖል የተዘጋጁ የቆዳ ውጤቶች ማህበር | ፍሰሃ ኤሌሉ | አዋሳ ቅርንጫፍ | ቤት | አዋሳ | ቤት | የም/ወቁ ቁጥር 2333 የቦታ ስፋት 199.8 | 3,000,000 ሦስት ሚሊዮን | ጥቅምት 12/2017 ዓ.ም | ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት |

**ማሳሰቢያ፡-**

1- ማንኛውም ተጫራች ወይም ህጋዊ ወኪሉ 1/4ኛውን በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ክፍያ ማዘዣ /ሲፒኦ/ በማስያዝ መጫረት ይችላል።

2- አሸናፊው ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ በ15 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ መክፈል ያለበት ሲሆን ካልከፈለ ለጨረታ መነሻ ያስያዘው ገንዘብ ተመላሽ አይደረግም፡፡

3- ቤቱ ያለበትን ሁኔታ ለማየት ከቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ ሃዋሳ ቅርንጫፍ አማካኝነት ጽ/ቤት በመቅረብ ከጨረታ በፊት ባሉ የስራ ቀናት እና የጨረታው ቀን በቦታው በመገኘት መመልከት ይቻላል፡፡

4- በንብረቱ ላይ ከመንግስት የሚፈለጉ ግብሮችን፤ቫት፣ የስም ማዛወሪያ እና ሌሎች ወጪዎችን የጨረታ አሸናፊው ይሸፍናል።

5- ተቋሙ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለተጨማሪ መረጃ፡-**

**በስልክ ቁጥሮች 09-19-76-16-07 መደወል ይችላሉ።**

# ቪዥን ፈንድ አ.ማ

# የተንጠልጣይ ድልድይ ግንባታ - ለገጠሩ ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትስስር መጎልበት

በኃይሉ አበራ

ከሀገሪቱ የገጠር ሕዝብ በርካታ የሚባሉት በተራራማ አካባቢዎች እና በወንዞች መብዛት ምክንያት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴያቸው የተገደበ ስለመሆኑ ይገለጻል፡፡ እነዚህ ማህበረሰቦች ለማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽ ካለመሆናቸውም በተጨማሪ ምርቶቻቸውን ገበያ አውጥተው ለመሸጥና የግብርናና የመሳሰሉትን ግብአቶችን ለማግኘት በእጅጉ ይቸገራሉ፡፡

ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የግድ በሆነ ጊዜ ዙሪያ ጥምጥም መጓዝ ይገደዳሉ፤ በዚህም የጊዜ ብክነትና እንግልት ይደርስባቸዋል፡፡ በአንዳንድ አስቸጋሪ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጦች ሲያልፉም እስከ ህይወት ማጣት ለሚደርሱ አደጋዎች የሚጋለጡበት ሁኔታ እንዳለም መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ይህን አይነቱን ችግር ለመፍታት በሚል በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ባለፉት ዓመታት የተንጠልጣይ ድልድዮች ግንባታዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል፡፡ የድልድዮቹ መገንባትም ድልድይ ባለነበረባቸው ጊዜያት በአካባቢዎቹ በሰዎች ላይ ይደርሱ የነበሩ አደጋዎችን ማስቀረት ችሏል።

የተንጠልጣይ ድልድይ ግንባታ የማህበረሰብ ትስስሮችን ከማጠናከሩም በላይ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለመስጠት ወይም ለማግኘት በሚደረጉ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ወቅት ጊዜን፣ ወጪን ከመቆጠብ አኳያም የጎላ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይታመናል፡፡

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ የመሰረተ ልማት ዘርፍ አማካሪ መሀመድአሚን አደም በገጠር ትስስር እና ተደራሽነት ፕሮግራም ደግሞ አስተባባሪ ናቸው። እሳቸው እንደሚገልጹት፤ የገጠር ትሰስር እና ተደራሽነት ፕሮግራም የመንግሥት የ10 ዓመት የልማት እቅድ አንድ አካል ነው።

ህብረተሰቡ ከዋና መንገድ ጋር ባለመተሳሰሩ ሳቢያ ከፍተኛ የተደራሽነት ጥያቄ ሲያነሳ መቆየቱን ጠቅሰው፤ በዚህም የተነሳ ከፍተኛ ምርት ወደ ገበያ ባለመድረሱ በተለይ የገጠሩ ህብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እየቀነሰ መጥቷል ይላሉ። ይሄንንም ችግር ለመፍታት ከዓለም ባንክ ጋር በመሆን የገጠር ትሰስር እና ተደራሽነት ፕሮግራም መዘጋጀቱን አስታውቀዋል። ፕሮግራሙ በዓለም ባንክ ፈንድ የሚደረግለትና ለአምስት ዓመት የሚካሄድ መሆኑን ጠቁመው፣ በተለይ በገጠሩ የህብረተሰብ ክፍል ላይ አተኩሮ እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ምክንያት ማህበረሰብ ከማህበረሰብ ጋር የማይገናኝበት፤ የገጠሩ ማህበረሰብ ከገበያ ማዕከላት ጋር የማይገናኝበት ሁኔታ ይታያል። የጤናና የትምህርት ተቋማትም እንዲሁ በቀላሉ ማግኘት አይቻልም፡፡ ይህን ችግር በመቅረፍ እና የማህበረሰብ ግንኙነት ለመፍጠር የተንጠልጣይ ድልድይ ማስፈለጉን አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በዚህም ረጅም እና አጭር የተንጠልጣይ ድልድይ አሰራር ማኑዋል የተዘጋጀ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ እስካሁን የረጅም ድልድይ (ሎንግ ስፓን) ስራው ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ ይህንንም በቀጣይ ተግባራዊ ለማድረግ ይሄንን ባካተተ መልኩ ማኑዋል እየተዘጋጀለት ነው።

አሁን የሚሰሩት አጭር የሚባሉት አይነት ሲሆኑ፤ የራሳቸው ዲዛይን፣ ቅርፅ አላቸው። የአገልግሎት ጊዜያቸው፣ የሚጠቀሙባቸው ማህበረሰብ እና የእንቅስቃሴው ብዛት ጥናትም ይደረግበታል።

በዚህ ጥናት መሰረትም እንስሳትን እስከማሻገር፣ ሞተር ሳይክል፣ ብስክሌት እና አልፎ አልፎም ባጃጆችን ጨምሮ ማሳለፍ የሚችሉ ተንጠልጣይ ድልድዮች የሚገነቡ ይሆናል፡ ፡ በቀጣይም መለስ ያሉ ተሽከርካሪዎችን ታሳቢ በማድረግ ድልድዮቹን ለመስራት ጥናት እየተደረገ ነው።

እሳቸው እንዳሉት፤ እስካሁን ባለው ሂደትም እንስሳትን እና ሰውን ማሻገር የሚችሉ ተንጠልጣይ ድልድዮች እየተገነቡ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ የገጠር ትስስር ፕሮግራም በዲዛይንም ሆነ በአገልግሎት ከዚህ ቀደም ሲሰሩ ከነበሩት ተንጠልጣይ ድልድዮች በተሻለ መልኩ ለመስራት ፕሮግራም ተይዟል።

በተለይም ተራራማ በሆኑ የገጠር አካባቢዎች ህብረተሰቡ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚቸገርበት ሁኔታ እንዳለ አማካሪው ገልጸው፤ በግንባታው ረጅም ርቀት ተጉዘው ትምህርት፣ ጤና የመሳሰሉ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የማግኘት ተግዳሮትን ለመቅረፍ ትኩረት ተሰጥቷል ብለዋል።



ቆላማ በሚባሉ አካባቢዎችም ተንጠልጣይ ድልድይ ባለመኖሩ የተነሳ ጎርፍ በመጣ ቁጥር ሰዎች ለአደጋ ሰለባ እየሆኑ መሆናቸውን አስታውቀው፤ በተደረገው ጥናትም በሁሉም ክልሎች ድልድዮቹ እንዲገነቡ ከፍተኛ ፍላጎት እንደሚታይ ጠቅሰው፤ በጥቅሉ ከ10 ሺህ በላይ የተንጠልጣይ ድልድዮች ፍላጎት እንዳለ ተረጋግጧል ብለዋል።

በዚህ ፕሮግራምም 373 ተንጠልጣይ ድልድዮችን በሁሉም ክልሎች እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ለመስራት በዓለም ባንክ ፕሮግራም ተካቶ ይሰራል ያሉት አማካሪው፣ ክልሎቹም አምስት መስፈርቶች ተልኮላቸው በመረጡት አካባቢ ግንባታው የሚከናወን ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል።

አማካሪው ‹‹ሄልቬታስ ኢትዮጵያ› በአማራ እና ኦሮሚያ ክልል የተንጠልጣይ ድልድይ ስራዎችን እየሰራ መምጣቱን ጠቅሰው፤ ግንባታው አሁንም ከክልል መንግሥታት ጋር በመሆን 20 በመቶውን ወጪ እሱ እየሸፈነ፣ ቀሪውን 80 በመቶ ክልሎች እየሸፈኑ በአምስት ክልሎች ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

አማካሪው እንዳብራሩት፤ በዚህ የገጠር ትስስርና ተደራሽነት ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረገው የአዲስ መንገድ ጥርጊያ፣ የነበሩትን መንገዶች ጠግኖ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣ ድልድይ በሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች ውሃ ማሳለፍ እንዲችሉ ተደርገው ድልድዮች ይሰራሉ፤ የመዳረሻ መንገድ ይሰራል፤ የተንጠልጣይ ድልድዮች ይገነባሉ።

ግንባታው ከዚህ ቀደም የገጠር መንገድ ፕሮጀክት /ዩራፕ/ ሲሰራበት በነበረው ሳይሆን፣ ወይም በቀጥታ ለግለሰቦች ተሰጥቶ ግንባታዎች የሚካሄዱበት ሳይሆን ውድድርንና ውድድርን መሰረተ ያደረገ ነው። ለዚህም በየክልሉ በፌዴራል ደረጃ የተመዘገቡ በርካታ ኮንትራክተሮች፣ የስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል። ፕሮግራሙ በቀጥታና በተዘዋዋሪ 560 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል የሚፈጠርበት እንደሆነም አስታውሰዋል።

የሄልቬታስ ኢትዮጵያ አስተባባሪ ወይዘሮ ፀሐይ ፀጋዬ በበኩላቸው እንዳሉት፤ ‹‹ሄልቬታስ›› በኢትዮጵያ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ አንዱ ከማህበረሰቡ ጋር በመሆን የተንጠልጣይ ድልድዮችን በመስራት ህብረተሰቡ እርስበርስ እንዲገናኝ እና የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ማድረግ ነው። በዚህም ለሀገራዊ የድህነት ቅነሳ ስራ የራሱን በጎ ሚና እየተወጣ ነው።

በኢትዮጵያ መንግሥት የተንጠልጣይ ድልድዮች ግንባታ በገጠር መንገዶች ትስስር እና ተደራሽነት ፕሮግራም ውስጥ መካተቱ ትክክለኛ እርምጃ ነው፡፡ ከተንጠልጣይ ድልድይ አስተዋፅኦ መካከል ድልድዩ ተገልለው ለቆዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ይሰጣል፤ በሕይወት ላይ አደጋ በሚያስከትሉ አስቸጋሪ ቦታዎች ላይ ድልድዩ ይገነባል፡፡ ለኢኮኖሚ፣ ለጤና እና ለተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦቶችን ያመቻቻል።

ሄልቬታስ በኢትዮጵያ በፓይለት ደረጃ መንቀሳቀስ ከጀመረ 20 አመታት ማስቆጠሩን አስታውሰው፣ አሁን ደረጃውን በማሻሻል በስፋት እየተንቀሳቀሰ ነው ይላሉ። በኢትዮጵያ እያስተዋወቀ ያለው ሶስት ዓይነት ተንጠልጣይ ድልድይ መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ እስከ 120 ሜትር ርዝመትና አጭር ቋሚ /ሾርት ስታንድ/ ያለው ተንጠልጣይ ድልድይ አንዱ ሲሆን፤ ከ120 ሜትር በላይም የሚረዝሙ ድልድዮች አሉ። እነዚህ ሎንግ ስፓን የሚባሉ ተንጠልጣይ ደልድዮች በሌላው ዓለምም ይሰራባቸዋል።

በኢትዮጵያ ማኑዋል ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው እስከ 120 ሜትር የሚረዝመው ወይም አጭር የሚባለው አይነት ተንጠልጣይ ድልድይ መሆኑን ገልጸዋል። በዚህ መሰረት ከ32 ሜትር በታች የሆኑትን እንዲሁም እንደ መሬቱ አቀማመጥ እየታየ እስከ 120 ሜትር ያለው ተግባራዊ ተደርጓል ሲሉ አብራርተው፣ በኢትዮጵያ ረጅም የተንጠልጣይ ድልድይ አይነት ፍላጎት እንዳለም አመላክተዋል።

ወይዘሮ ጸሀይ እንዳሉት፤ ቀደም ሲል ሄልቬታስ ከክልል መንገዶች አስተዳደር ጋር በመተባበር እና ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ጋር በመሆን ለ15 ዓመታት የተንጠልጣይ ድልድይ ፕሮጀክቶችን የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት በሚል በስድስት ክልሎች ላይ ተግባራዊ አድርጓል።

ሄልቬታስ በፓይለቱ ወቅት በደረሰበት ውጤት ላይ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እና ከትራንስፖርት ሚኒስቴር ጋር ተወያይቷል። በውይይቱም ዘላቂ እና ደረጃው የተሻሻለ የተንጠልጣይ ድልድይ ስራዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው እና የተሰሩትም አገልግሎታቸውን በመጠበቅ በቂ ጥገናዎችን ማከናወን ላይ ተግዳሮት መኖሩ ተመላክቷል።

ሄልቬታስ የማስተባበር ሚናውን እንዲጫወት ጠቅሰው፣ የእውቀት ሽግግሩን በማስፋት ላይ የአቅጣጫ ለውጥ ተደርጓል ሲሉ አስተባባሪዋ ተናግረዋል። መንግሥትም ይሄንን አቅጣጫ በመከተል ከዚያ በኋላ ዲዛይን የተደረጉ “ፈርስት ማይል” የሚባለው ፕሮጀክት በአማራ ክልል ላይ ሙከራ (ፓይለት) መደረጉን ጠቅሰው፣ በዚህም የአማራ ክልል 80 በመቶውን፣ ሄልቬታስ 20 በመቶውን (በይበልጥ በአቅም ግንባታ ስራ፣ በስልጠና እና በማስተባበር፣ ከውጭ በሚገቡ ቴክኖሎጂ አቅርቦት) ላይ ተሳትፎ አድርጓል ብለዋል።

በአማራ ክልል ይህ ስኬታማ መሆኑ በመታየቱ ወደ ሌሎች ክልሎች የማስፋት እንቅስቃሴ ተጀምራል ሲሉ ጠቅሰው፤ ይህም ስድስት ክልሎች ላይ ለመፈፀም ታቅዶ እንደነበር ተናግረዋል፡፡ አምስት ክልሎች ላይ ፕሮጀክቱ በስኬታማነት መተግበሩን ጠቅሰው፣ በዚህ አሰራር ሄልሜታስ የመንገድ ቢሮ ባለሙያዎችን አቅም የማጎልበት ስራ ከተለያዩ ባለድርሻዎች ጋር በመሆን ለአማካሪዎች፣ ተቋራጮች፣ አምራቾች እና ክልሉ በሚመርጣቸው መሰረት ስልጠና መስጠቱን አስታውቀዋል።

በዚህም የኮንትራት አስተዳደሩን ክልሎች እንደሰሩትና የሀገር ውስጥ ኮንትራክተሮች፣ አማካሪዎች እና አምራቾች የሀገር ውስጥ መሀንዲሶችም ክህሎቱን ማግኘት መቻላቸውን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሶስት ዓመቱ ፕሮጀክትም ወደ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍሎችን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። ቀደም ሲል የተገነቡት ተንጠልጣይ ድልድዮች ከዚያ በላይ የማህበረሰብ ክፍሎች እየተጠቀሙባቸው ነው። ፕሮጀክቱ በተሰራባቸው አካባቢዎች በአማካይ አንዱ ድልድይ 20 ሺህ ሰዎችን እያገለገለ ስለመሆኑ ሪፖርት መደረጉን አስተባባሪዋ ጠቁመዋል።

ሄልቬታስ ከአሜሪካው ብሪጅስ ፎር ፕሮስፒሪቲ ጋር በመሆን በሶስት ዓመት ውስጥ የሚያስገነባው 10 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በጀት የተመደበለት ሲሆን፣ በአምስቱ ክልሎች (አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ሲዳማ) በዲዛይን፣ በግንባታ እና በፋብሪኬሽኑ ላይ ተሳትፈዋል፡፡ ከፕሮጀክቱ ሶስት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ የሆነው የአቅም ግንባታ ተፈጥሮበታል።

ከወጪ አኳያም በትንሽ ወጪ ብዙ ውጤቶች ያሉት ስራ ነው ያሉት አስተባባሪዋ፣ በአማራ ክልል በአንደኛው ዓመት ከተሰሩ ተንጠልጣይ ድልድዮች ሥራ በኋላ በተሰራ ጥናት መሰረት በአማካይ በ53 ደቂቃ የማህበረሰቡን የጉዞ ሰዓት ማሳጠር መቻሉንም ጠቁመዋል። ይህም ጊዜን መቆጠብ ብቻ ሳይሆን ብዙ አደጋዎችን እንደሚያስቀርም ተናግረዋል፡፡

ሄልቬታስ በሶስት ዓመት ውስጥ ወደ 150 ተንጠልጣይ ድልድዮችን ለመገንባት ዕቅድ መያዙን ጠቅሰው፣ ከእነዚህም መካከል የ48ቱ ግንባታ የተጠናቀቀ ሲሆን የ35ቱ ግንባታ በሂደት ላይ መሆኑን አስታውቋል፡፡ እንደ ሀገር በሺዎች የሚቆጠሩ ድልድዮች እንደሚያስፈልጉ ገልጸዋል።

የአማራ ክልል መንገድ ቢሮ ኃላፊ ጋሻው አወቀ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በሀገር ደረጃ የገጠር ትስስር እና ተደራሽነት ለምግብ ዋስትና ፕሮግራም በተለይ ከምርትና ምርታማነት ከግብርና ልማት ጋር ተያይዞ የሚሰራ ነው። በተለይ የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር እና በአጠቃላይ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማትን በመደገፍ የጎላ ፋይዳ አለው ።

ከአማራ ክልል አኳያ ሲታይ ቀደም ሲል በገጠር መንገድ ፕሮጀክት/ዩራፕ/ የተሰሩ መንገዶች የማቅረብ እንጂ የተሟላ የድልድይ እና መሰል ስራዎችን ያሟሉ አልነበሩም። መንገዶቹ የነበራቸውን የጥራት፣ የተሟላ አገልግሎት አለመስጠት ችግር አሁን ያለው የገጠር ተደራሽነት እና ትስስር ፕሮግራም ይፈታዋል ተብሎ ይገመታል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እንደ ኃላፊው፤ የክልሉ ማህበረሰብ በጥሬ ገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ በሀሳብ እና በጉልበት ባለቤትም ተሳታፊም ሆኖ በመስራት የተሻለ ልምድ አካብቷል። ፕሮግራሙ በክልሉ ተግባራዊ የሚደረገው የወረዳዎችን የቆዳ ሽፋንና የሕዝብ ብዛት ታሳቢ በማድረግ ነው።

የመንገድ ሽፋን ዝቅተኛ የሆነባቸውን ወይም ያልተቀራረበባቸውን ወረዳዎች ታሳቢ ያደረገ ነው። በየወረዳው የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት በመንግሥት እና በግል ደረጃ የተወሰነ ተቋማት ተሟልተው ከግብአት፣ ከፋይናንስ እና ከቴክኖሎጂ አቅርቦት ጋር የተያያዙ ተቋማት ያሉበትን ታሳቢ ባደረገ መስፈርት መሰረት ወረዳዎቹ ተመርጠዋል።

በዚህ መሰረት በክልሉ በሁሉም ዞኖች ሁለት ወረዳዎች በድምሩ 28 ወረዳዎች ላይ ፕሮግራሙ ተግባራዊ እንደሚደረግ ጠቁመዋል። በቀጣይም ፕሮግራሙ በእነዚህ ወረዳዎች ውጤቱ ታይቶ ወደ ሌሎች ወረዳዎች ሊሰፋ እንደሚችል አመልክተው፣ ይህም እንደ ሀገር እንደሚወሰን ገልጸዋል።

# ስፖርት





## የፕሪሚየር ሊጉ ክለቦች ትርፍ ክፍፍል እና የኮከቦች ሽልማት

ዓለማየሁ ግዛው




የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አክስዮን ማኅበር የ2016 ዓም ውድድር ዘመን የክለቦች ዓመታዊ ትርፍ ክፍፍል ተከናውኗል። በየዘርፉ የዓመቱ ኮከቦችን ሽልማት መርሐግብር አከናውኖም ለክለቦች፣ አሠልጣኞች፣ ተጫዋቾች፣ ዳኞች እንዲሁም አስተናጋጅ ከተሞች የገንዝብ ሽልማት እና እውቅና ተበርክቶላቸዋል፡፡

አዲሱ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ዓመት ትናንት በድሬዳዋ ስታዲየም በተካሄዱ ጨዋታዎች ተጀምሯል፡፡ ከውድድር ዓመቱ መጀመር አስቀድሞ ያለፈው ዓመት ኮከቦች ምርጫ፣ የክለቦች ዓመታዊ የትርፍ ክፍፍል፣ የማጠቃለያ እንዲሁም የ2017 ዓም ውድድር ማስጀመሪያ መርሐግብር ተከናውኗል፡፡ በሥነ ሥርዓቱም ላይ ለክለቦች እንደየደረጃቸውና ድርሻቸው የገንዘብ ክፍፍል ተደርጎላቸዋል፡፡

16ቱ የፕሪምየር ሊግ ክለቦች የውድድር ዓመቱን በፈጸሙት ደረጃቸው መሠረት የገንዘብ ክፍፍል ሲደረግላቸው፤ ሻምፒዮኑ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተጨማሪ የገንዘብ ሽልማት አግኝቷል፡፡ ከቴሌቪዥን መብት ሽያጭ እና ከሌሎች ገቢዎችም የሊጉ ተሳታፊ ለሆኑት 16ት ክለቦች 195 ሚሊዮን ብር የትርፍ ክፍፍል መደረጉ ተገልጿል፡፡ በዚህም የውድድሩ አሸናፊ የሆነው ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 9 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብርን ጨምሮ በአጠቃላይ 18 ሚሊዮን ብር ተበርክቶለታል፡፡ በብርቱ ተፎካካሪነት ሁለተኛ ሆኖ ያጠናቀቀው መቻል 17 ሚሊዮን ብር አግኝቷል። የኢትዮጵያ ዋንጫ ሻምፒዮኖቹ ኢትዮጵያ ቡናዎች 16 ሚሊዮን ብር ሲያገኙ፤ ወራጆቹ ሻሸመኔ ከተማ እና ሀምበርቾ ዱራሜ እያንዳንዳቸው 8 ሚሊዮን ብር የትርፍ ተካፋይ ሆነዋል፡፡ ከአራተኛ እስከ 14ኛ የተቀመጡት ክለቦችም ከ15 ሚሊዮን እስከ 9 ሚሊዮን ብር ወደ ካዝናቸው አስገብተዋል፡፡

በ7 ዘርፎች የዓመቱ ኮከቦች ሽልማት የተከናወነ ሲሆን፤ የዓመቱ ኮከብ እግር ኳስ ተጫዋቾች፣ አሠልጣኞችና ዳኞችም ከፍተኛ የሆነ የማበረታቻ ገንዘብ ተሸልመዋል፡፡ የሊጉ ሻምፒዮን ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዓመቱ የኮከቦች ሽልማት በሦስት ዘርፎች አሸናፊ ሊሆን ችሏል። የዓመቱ ኮከብ ተጫዋች፣ ከፍተኛ ግብ አስቆጣሪ፣ ተስፈኛ ወጣት ተጫዋች እና የዓመቱ ኮከብ በረኛ በሚልም ሽልማቱ ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት በዓመቱ ኮከብ ተጫዋችነት ጋናዊው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመሐል ሜዳ ተጫዋች ባሲሩ ኡመር የ210 ሺ ብር ተሸላሚ ሆኗል፡፡ የአዳማ ከተማው ቢኒያም አይተን የዓመቱ ወጣት ኮከብ ተጫዋች ሆኖ በመመረጥ 105 ሺ ብር ተበርክቶለታል፡፡ በ2015 ዓም ዮሴፍ ታረቀኝ የሊጉ ወጣት ኮከብ ተጫዋች በመሆን ከተመረጠ በኋላ ቢንያም አይተን ሁለተኛው የአዳማ ከተማ ተሸላሚ ወጣት ተጫዋች ሆኗል፡፡ የ2016 ዓም የሊጉ ከፍተኛ ጎል አስቆጣሪ በመሆን ማጠናቀቅ የቻለው ኤርትራዊው የሃዋሳ ከነማ ተጫዋች አሊ ሱሌማን ደግሞ 200 ሺ ብር ተሸልሟል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ግብ ጠባቂ ፍሬው ጌታሁን የዓመቱ ኮከብ ግብ ጠባቂና የ150 ሺ ብር ተሸላሚ መሆኑም ተረጋግጧል፡፡

ኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ከከፍተኛ ሊግ በማሳደግ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ዋንጫ ያበቃው አሠልጣኝ በፀሎት ልዑልሰገድ ኮከብ አሠልጣኝ ሆኖ ተመርጧል፡፡ ክለቡ የመጀመሪያውን የፕሪምየር ሊግ ዋንጫ እንዲያነሳና የአፍሪካ ሻምፒዮንስ ሊግ ተሳታፊ ያደረገው አሠልጣኝ በፀሎት 200 ሺ ብርም ተሸልሟል። ምስጉን ረዳት ዳኛ ፋሲካ የኋላሸት እንዲሁም ኢንተርናሽናል ዳኛ ባምላክ ተሰማ ምርጥ ዋና ዳኛ በመሆን እያንዳንዳቸው 105 ሺ ብር መሸለም ችለዋል፡፡

የ2016 ዓም የውድድር ዓመት መዝጊያ እና የ2017 ዓም የውድድር ዘመን ማብሰሪያ በድሬዳዋ ከተማ የተካሄደውም የከተማ አስተዳደሩ ለስታዲየም ግንባታ የሰጠውን ትኩረት ለማበረታታት እና እውቅና ለመስጠት እንደሆነም የአክስዮን ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ አቶ ክፍሌ ሰይፈ ተናግረዋል። በዚህም ባለፈው የውድድር ዓመት የሊጉን ጨዋታዎች ያስተናገዱት አዳማ፣ ሃዋሳና ድሬዳዋ ከተሞች 10 ሚሊዮን ብር እንደሚከፋፈሉም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

19 ክለቦች የሚፋለሙበትና አምስት ክለቦች የሚወርዱበት የ2017 የሊጉ መርሐግብር ትናንት ሁለት ጨዋታዎችን በማስተናገድ ተጀምሯል። ውድድሩ ዛሬም በሁለት ጨዋታዎች ቀጥሎ ሲካሄድ እሁድ እና ሰኞም በተመሳሳይ ሁለት ሁለት ጨዋታዎች ይካሄዳሉ፡፡ የዘንድሮው የሊጉ ቆይታ 38 ሳምንታት የሚፈጅ ሲሆን 342 ጨዋታዎች ይደረጋሉ፡፡ በቀን ሦስት ጨዋታዎች እየተካሄዱ አንድ አራፊ ቡድን ሆኖ በተመረጡት ከተሞች እስከ ዓመቱ ማጠናቀቂያ የሚቀጥልም ይሆናል፡፡

## ኦሮሚያ ክልል

አመልካች ወ/ሮ ሜላት አብዱ ተጠሪ አቶ ያሬድ ተሾመ መካከል ባለው የጋብቻ መፍረስ አስመልክቶ ተጠሪ በቀጠሮው ቀን 4/2/2017 በ4፡00 ሰዓት በጨለለቃ ክ/ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ቤተሰብ እና ህፃናት ችሎት እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በጨለለቃ ክ/ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የቤተሰብ እና ህፃናት ችሎት ቡድን**

## ሐረሪ ክልል

የፍ/ባለመብት አለማየሁ አየለ እና የፍ/ባለዕዳ ፍቃዱ ሐብታሙ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ 20/1/2017 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ 1ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

## ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል

ከሳሽ ፀሐይነሽ ባሻ እና በተከሳሽ የለም መካከል ስላለው ትዕዛዝ መስጫ ክስ ክርክር ጉዳይ ለ18/2/2017 ዓ.ም የተቀጠረ በመሆኑ ተከሳሽ ወደ ሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪየ ደረጃ ፍ/ቤት በቀጠሮ ቀን እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ተሰምቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በሀዲያ ዞን የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

## የደቡብ/ምዕ ኢትዮጵያ ክልል

በአመልካች የደቡብ ኢት/ያ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ እና በተጠሪ አቶ ማሙሽ ፍቅሩ መካከል ባለው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ክስ ክርክር ጉዳያቸው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እየታየ በመሆኑ ችሎቱም በ03/10/2016 ዓ.ም በዋለው የችሎት ውሎ በሰጠው ትዕዛዝ አቶ ማሙሽ ፍቅሩ የተባሉት ተጠሪ ለ13/02/2017 ዓ/ም ለተያዘው ቀጠሮ ዲላ ከተማ ለሚያስችለው የሰበር ተዘዋዋሪ ችሎት ቀርበው - ለቀረበባቸው ክስ መልሳቸውን እንዲሰጡ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ታይቶ እንደሚወሰን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አዟል፡፡

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

ከሳሾች እነ አቶ ፉአድ ሳሊ አባሲመል እና ተከሳሽ/ሾች 1ኛ አቶ ብርሃኔ መዝገቡ አረጋዊ፣ 2ኛ አቶ መሀሪ መዝገቡ አረጋዊ፣ 3ኛ አቶ አታክልቲ አረጋዊ መካከል ስላለው ፍታብሔር ክስ ጉዳይ ተከሳሾች በ4/2/2017 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለሚ ኩራ ምድብ 8ኛ ፍታብሔር ችሎት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ ወ/ሪት ሰባት አሊ ሙሃመድ እና በተከሳሽ አቶ ዮናስ ገበየሁ ካሳ መካከል ስላለው የፍታብሄር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ አቶ ዮናስ ገበየሁ ካሳ ለ21/01/2017 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ እንዲቀርቡ ሲል የአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤ/ት ን/ስ/ላ ምድብ ችሎት አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንፋስ ስልክ ላፍቶ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ዮናስ ፍቅሬ ገ/ህይወት የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-32939 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር 82013 ሞዴል H603RS የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0235829 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 3/1/2017 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳውን ወድቆ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጅ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ አ.ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-67992 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNDFA100767 ሞዴል ZZ3257N3247A የሊብሬ ቁጥር 0051918 የሞተር ቁጥር WD615-69*150907013127* ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 3/1/2017 ዓ.ም አመልክተዋል።

ሠሌዳውን ወድቆ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጅ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

ይግባኝ ባይ አቶ መጅድ ያሲን መሀመድ እና በመልስ ሰጪ እነ ንጉስ ጌታቸው ከዳነማሪያም መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ መልስ ሰጪ አቶ ገነነው ሌንጃሳ በዳኔ ለጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፤00 ሰዓት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 2ኛ ፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ተወልደብርሃን ለይኩን ታዬ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B28528 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10-3300428 የሞተር ቁጥር 1SZ-0917089 ሞዴል TA-SCP10-AHPNK-D የሊብሬ ቁጥር 359235 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር / ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 2/13/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ን/ስ/ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/ግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-99663 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNB6HN283988 ሞዴል ZZ3257N3447A የሞተር ቁጥር WD615-69*170817028477* የሊብሬ ቁጥር 0206660 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 28/12/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳውን ወድቆ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጅ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዳንኤል ጎንፋ ሒርጳሳ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B42936 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JT132LN9009003616 የሞተር ቁጥር 21-3268192 ሞዴል LN90L-CRMDSW የሊብሬ ቁጥር 007435 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 10/12/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጅ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አራዳ ቅ/ጽ/ቤት**